# ትምህርት ሦስት

## የመጀመሪያ ቀን ሮሜ 9-11

> 1ኛ ጥያቄ፦ ሀ) በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ «ደኅንነት» የሚለው ቃል የሚያስተላልፋቸውን ፍቺዎች በሙሉ ዘርዝር። ለ) እግዚአብሔር አንተን ያደነባቸውን የተለያዩ መንገዶች ዘርዝር።

ደኅንነት! በሁሉም ቋንቋዎች ውስጥ ከሚገኙ ውድ ቃላት አንዱ ደኅንነት ነው። ቃሉ በብዙ የተለያዩ መንገዶች ያገለግላል። አንድ ሰው ከአደጋ በሚተርፍበት ጊዜ ድኗል እንላለን። አንዲት ሴት በጠና በታመመች ጊዜ የታዘዘላት መድኃኒት ካሻላት አድኖአታል ማለት ነው። ይህን ቃል ባለማቋረጥ ከምንጠቀምባቸው መንገዶች ጥቂቶቹ እነዚህ ሁለቱ ናቸው።

ነገር ግን ከሌሎች ሁሉ የበለጠ ጠቀሜታ ያለው አንድ የደኅንነት ዓይነት አለ። ይህም እግዚአብሔር እኛን ከኃጢአታችን የሚያድንበት ነው። (ጳውሎስ ዛሬ ብዙ ሰዎች አጽንኦት በሚሰጡበት ከበሽታ ወይም ከድህነት የመዳን ጉዳይ ላይ ምን ያህል አነስተኛ ትኩረት እንደሰጠ ተመልከት።) በሮሜ መጽሐፍ ውስጥ፥ ጳውሎስ ስለ ደኅንነት ሲያብራራ ነበር። ጳውሎስ ደኅንነት አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያት በመግለጽ ነበር የጀመረው። ሰዎች፥ የየትኛውም ነገድ አባል ይሁኑ፥ ሃይማኖተኞች ይሁኑ ወይም አይሁኑ፥ ጥሩ ሥነ ምግባራዊ ሕይወት ይኑራቸው ወይም አይኑራቸው፥ በቅዱስ አምላክ ፊት ኃጢአትን ስለፈጸሙ ጥፋተኛ ናቸው። ይህም ማለት ከእግዚአብሔር ቁጣ ሥር በመሆናቸው እግዚአብሔር በሞት ይቀጣቸዋል ማለት ነው። በኃጢአታችን ምክንያት የእግዚአብሔር የሞት ቅጣት እንደሚገባን

እስካላወቅን ድረስ የደኅንነትን ትርጉም እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ ልንረዳው አንችልም።

ጳውሎስ ሰዎች ወደ ክርስቶስ ተመልሰው በመስቀል ላይ እንደሞተላቸው ሲያምኑ እግዚአብሔር ስለሚሰጣቸው ደኅንነት አብራርቷል። ጳውሎስ ማብራሪያውን የጀመረው ከኃላፊ ጊዜ ነው። በሰው ልጆች ሁሉ ላይ የተወሰነው የኃጢአት ጥፋተኝነት «ጥፋተኛ አይደለህም» በሚል እንዲለውጥ እግዚአብሔር ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን የኃጢአት መሥዋዕት ወይም የቁጣው ማብረጃ አድርጎ መላኩ ብቻ በቂ አይሆንም። እያንዳንዱ ግለሰብ በክርስቶስ ለማመን የግል ውሳኔ ማድረግ ይኖርበታል። ያንን የእምነት ውሳኔ ካደረገ በኋላ፥ ጻድቅ የሆነው አምላክ «ጥፋተኛ አይደለህም» ወይም «ጻድቅ ነህ» ሲል ወደ ቤተሰቡ ይቀበለዋል። ይህ የአንድ ጊዜ ውሳኔ ሰዎችን ከዘላለማዊ የሲኦል ፍርድ ያድናቸዋል።

ጳውሎስ በመቀጠል <u>ስለ አሁኑ</u> የደኅንነት ገጽታ ያብራራል። ይህም ከኃጢአት ቁጥጥር ነፃ ወጥተን ክርስቶስን ለመምሰል በየቀኑ በቅድስና የምናድግበት ነው። የክርስቶስ መስቀል ከአማኞች ሕይወት የኃጢአትን ተፈጥሮ አጥፍቷል። በሕይወታችን ውስጥ ባለው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ምክንያት ከኃጢአት ርቀን ለእግዚአብሔር ሕግጋት ልንታዘዝ እንችላለን።

ከዚያም ጳውሎስ <u>ስለ ወደፊቱ</u> የደኅንነት ገጽታ ያብራራል። ጳውሎስ እያንዳንዱ አማኝ ከክርስቶስ ጋር የሚከብርበትን የወደፊት ዘመን አሻግሮ ያያል። ሕይወት በምድር ላይ ብዙ ኀዘንና መከራ የሚበዛበት ሊሆን ይችላል። ሆኖም ምንም ነገር ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንደማይችል ክርስቲያኖች ሊገነዘቡ ይገባል። ሁሉም ነገር ለልጆቹ ጥቅም ይውል ዘንድ እግዚአብሔር ወደ መንግሥተ ሰማይ ሊያደርሰንና ሙሉ ለሙሉ በሕይወታችን ዙሪያ የሚከሰቱትን ነገሮች ለመቆጣጠር ቆርጧል።

ጳውሎስ የወደፊቱን የደኅንነት ገጽታ በሚመለከትበት ጊዜ እያንዳንዱ ክርስቲያን የሚያገኘውን ደኅንነትና ክብር ብቻ አይጠቅስም። ነገር ግን ደኅንነት ሌሎች ሁለት ዐበይት ነገሮችን እንደሚያጠቃልል ያስረዳል። በአዳምና ሔዋን ኃጢአት የተጀመረው ጥፋት (ረሃብ፥ በሽታ፥ የመሬት መንቀጥቀጥ፥ ድርቅ) ይወገድና ፍጥረት ሁሉ ይድናል። እግዚአብሔር መጀመሪያ ሲፈጥር የነበረውንም መልክ ይይዛል። የመጨረሻው ደኅንነት የብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ የነበሩትን አይሁዶችም ይነካል። በዚያን ጊዜ እነርሱም ደኅንነትን ያገኛሉ።

---

2ኛ ጥያቄ፦ ሀ) በዚህ የወደፊት ደኅንነት እግዚአብሔር ፍጥረትንና ዓለምን በሚያድንበት ጊዜ ይለወጣሉ የምትላቸው አንዳንድ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ለ) ዛሬ በኃጢአት በቆሸሸች ዓለም ውስጥ በምንሠቃይበት ጊዜ ወደፊት የሚለወጡትን ነገሮች በትክክል መገንዘባችን የሚያጽናናን እንዴት ነው?

---

## ወንጌሉ፥ አይሁዶችና አሕዛብ (ሮሜ 9-11)

1. የእስራኤላውያን ያለማመናቸው መሠረቱ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ከመቀበል ይልቅ በራሳቸው ጥረት ሊጸድቁ ስለፈለጉ ነው (ሮሜ 9-10)።

3ኛ ጥያቄ፦ ሮሜ 9–10 አንብብ። ሀ) ጳውሎስ አይሁዶች ወደ ክርስቶስ እንዲመለሱ የነበረውን ጥልቅ ፍላጎት የገለጸው እንዴት ነው? ለ) አይሁዶች የተቀበሏቸው በረከቶች ምን ምንድን ናቸው? ሐ) በእነዚህ በረከቶች አሁን የማይደሰቱበት ለምንድን ነው? መ) ጳውሎስ ከአይሁድ ዘር መወለድ በቂ እንዳልሆነና ሰዎች የአብርሃም መንፈሳዊ ልጆች ሆነው መወለድ እንዳለባቸው የሚያስረዳው እንዴት ነው? ሠ) ጳውሎስ አይሁዶችንና ያልዳኑበትን ምክንያት የገለጸው እንዴት ነው? ረ) ለሰዎች ሁሉ የተዘጋጀውን የደኅንነት መንገድ ጠቅለል አድርጎ የገለጸው እንዴት ነው? ሰ) ሮሜ 10፡9–10ን በቃልህ አጥና። ይህ ክፍል ሰዎች የእግዚአብሔር ልጆች የሚሆኑበትን መንገድ በአጭሩ የገለጸው እንዴት ነው?

የሥነ መለኮት ምሁራንን ከሚያስቸግራቸው ጥያቄዎች አንዱ የእግዚአብሔር ታሪካዊ ሕዝብ የሆኑት አይሁዶች ስፍራ ምን ይሆን? የሚለው ነው። አሁን በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ምን ድርሻ አላቸው? በብሉይ ኪዳን ዘመን በምድር ላይ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ መካከል እግዚአብሔር የራሱ ልዩ ሕዝብ አድርጎ መርጧቸው ነበር። ልዩ ቃል ኪዳኖችንና የተስፋ ቃሎችንም ሰጥቷቸዋል። የሰጣቸውን ሕግጋት በማይታዘዙበት ጊዜም ባለማቋረጥ ይቀጣቸው ነበር። እንግዲህ እግዚአብሔር ከአይሁዶች ጋር የነበረውን ግንኙነት አጠናቅቆ ወደ ቤተ ክርስቲያን ፊቱን መልሷል ማለት ነው? በሮም የነበሩት አይሁዳውያን ክርስቲያኖችም በዚህ አሳብ ግራ ሳይጋቡ አልቀሩም። አይሁዶችና አሕዛብ አሁን እኩል ከሆኑና ወደ እግዚአብሔር መንፈሳዊ ቤተሰብ የሚመጡት በክርስቶስ በማመን ብቻ ከሆነ፥ አይሁዳዊ መሆን ምን ታሪካዊ ጥቅም አለው? የአይሁዶች የወደፊት ተስፋስ ምንድን ነው? እግዚአብሔር ለአይሁዶች የሰጣቸው የብሉይ ኪዳን የተስፋ ቃሎችስ? ከእንግዲህ በሥጋ አይሁዳውያን ለሆኑት ወገኖች አያገለግሉም ማለት ነው?

ብዙ ክርስቲያኖች ለእነዚህ ጥያቄዎች የሚሰጡት መልስ እግዚአብሔር ከእንግዲህ ወዲህ ለአይሁዶች የተለየ ትኩረት አይሰጥም የሚል ነው። አሁን የእግዚአብሔር ዕቅድ የአብርሃም መንፈሳዊ ዝርያዎች በሆኑት ክርስቲያኖች ላይ ነው፥ የብሉይ ኪዳን የተስፋ ቃሎችም በተምሳሌታዊ መልኩ በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸሙ እንጂ እግዚአብሔር በሆነ መንገድ ወደፊት ከአይሁዶች ጋር የሚካሄደውን ተግባር የሚያሳዩ አይደሉም ይላሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር ለእስራኤልና ለአይሁድ ሕዝብ አሁንም የተለየ ዕቅድ እንዳለው የሚያምኑ ክርስቲያኖች ደግሞ አሉ። እግዚአብሔር ለአይሁዶች የሰጣቸው የተስፋ ቃሎች በብሉይ ኪዳን ውስጥ በተጠቀሰው መልክ ይፈጸማሉ። በዮሐንስ ራእይ ጥናታችን፥ ለዚህ ጥያቄ በምንሰጠው መልስ የትንቢትና የመጨረሻው ዘመን ግንዛቤያችንን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚለውጥ እንመለከታለን።

በሮሜ 9–11፥ ጳውሎስ የአይሁድ ክርስቲያኖች የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሯል። ጳውሎስ ፀረ አይሁዳዊ ነው የሚል ክስ ቀርቦበት ነበር። ጳውሎስ ይህን መልእክት ጽፎ ከጨረሰ ከጥቂት ወራት በኋላ ኢየሩሳሌም ውስጥ ነበር። በዚያም የአይሁድ ክርስቲያኖች በሐዋርያት መሪነት ጳውሎስ ወደ ቤተ መቅደሱ ገብቶ አንዳንድ የአይሁድ የመንጻት ሥርዓቶችን በመፈጸም ፀረ–አይሁዳዊ አቋም እንደሌለው እንዲያረጋግጥ

ጠይቀውታል። ጳውሎስ ራሱን ዝቅ አድርጎ የተጠየቀውን ሁሉ በመፈጸም ለአይሁዶች የነበረውን ፍቅር አሳይቷል (የሐዋ. 21፡21–26)። ከዚህም የተነሣ ወደ እስር ቤት ወርዶ ለአራት ዓመታት ማቅቋል። በሮሜ 9–11፥ ጳውሎስ የብሉይ ኪዳን የተስፋ ቃሎች በአይሁዶች መካከል ስላልተፈጸሙበት ምክንያት፥ በአሕዛብና አይሁዶች መካከል ስላለው ግንኙነትና እግዚአብሔር ለአይሁዶች ያለው የመጨረሻ ዕቅድ ምን እንደሚሆን በማብራራት ለእነርሱ የነበረውን ፍቅር ገልጧል።

1. <u>ጳውሎስ ለአይሁዶች የነበረውን ጥልቅ ፍቅር ገለጠ</u> (ሮሜ 9፡1–3)። እጅግ የምንወዳቸው የቤተሰባችን አባላት በክርስቶስ ለማመን በማይፈልጉበት ጊዜ ምን ያህል እንደምንጨነቅ ሁላችንም እናውቃለን። ወደ ሲኦል እንደሚሄዱ ስለምናውቅ እንጨነቃለን። በሰማይ እናገኛቸው ዘንድ ዘመዶቻችን በክርስቶስ የሚያምኑበትን ጊዜ በናፍቆት እንጠብቃለን። ጳውሎስም ወገኖቹ ስለሆኑት አይሁዶች ባሰበ ጊዜ እንዲህ ዓይነት የጭንቀት ስሜት ተሰምቶታል። ጳውሎስ የአይሁድን ሕዝብ ወደ ደኅንነት ለማምጣት የሚችል ቢሆን የራሱን ደኅንነት አጥቶ ስለ እነርሱ ወደ ሲኦል ቢወርድ ፈቃደኛ እንደሆነ ገልጾአል። ጳውሎስ አይሁዶችን በጣም ይወዳቸው ነበር እንጂ ፀረ–አይሁዳዊ አቋም አልነበረውም።

2. <u>ጳውሎስ አይሁዶች ያገኟቸውን ብዙ በረከቶች ይዘረዝራል</u> (ሮሜ 9፡4–5)። እግዚአብሔር አይሁዶችንና አሕዛብን በእኩል ሁኔታ ነበር ያስተናገደው? ጳውሎስ እግዚአብሔር ከአይሁዶች ጋር ታሪካዊ ግንኙነት ስለነበረው፥ አሕዛብ ያላገኟቸውን በረከቶች እንዳገኙ አብራርቷል።

ሀ. አይሁዶች ከእግዚአብሔር ጋር የአባትና የልጅ ዓይነት ልዩ ግንኙነት ነበራቸው። (ዘጸግ. 4፡22–23 አንብብ።)

ለ. «መለኮታዊ ክብር» ነበራቸው። ጳውሎስ ይህን ሲል በምድረ በዳ የነበረውን የክብር ደመና ለመግለጽ ብቻ ሳይሆን በቤተ መቅደስ ውስጥ የተገለጠውንም ለማመልከት ነበር (ዘጸ. 16፡7፤ 1ኛ ነገ. 8፡10–11)።

ሐ. አይሁዶች ከእግዚአብሔር ጋር ልዩ ቃል ኪዳኖችን አድርገዋል። በሲና ተራራ ላይ ከተሰጣቸው ቃል ኪዳን በተጨማሪ፥ ለሌዊ፥ ለዳዊት፥ ወዘተ… የተሰጡት ቃል ኪዳኖች ነበሯቸው።

መ. በሲና ተራራ የእግዚአብሔርን ሕግ ተቀብለዋል። ይህም እግዚአብሔር እንዴት ሊኖሩና እርሱን ሊያከብሩ እንደሚገባቸው የገለጠበት መመሪያ ነበር። በዚህ መልኩ የእግዚአብሔርን ቃል የተቀበለ ሌላ ነገድ የለም።

ሠ. አይሁዶች በእግዚአብሔር የተሠራ የቤተ መቅደስ አምልኮ ያካሂዱ ነበር። ይህም በሰዎች አሳብ ሳይሆን በእግዚአብሔር የታቀደ ነበር።

ረ. እግዚአብሔር በቃሉ ተስፋ ሰጥቷቸው ነበር። ከእነዚህ የተስፋ ቃሎች አብዛኛዎቹ በትንቢት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፥ ከአይሁዶች የወደፊት በረከቶች ጋር የሚያያዙ ነበሩ።

ሰ. እንደ አብርሃም፥ ያዕቆብና ይስሐቅ ያሉት የአይሁድ የእምነት አባቶች ከእግዚአብሔር ጋር ልዩ ግንኙነት የነበራቸው ሲሆን፥ እግዚአብሔር በእነርሱ ተጠቅሞ ልዩ የሆነውን የአይሁድ ሕዝብ መሥርቷል።

ሸ. እግዚአብሔር መሢሑ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ዓለም ያመጣው በአይሁዶች በኩል ነበር። ስለሆነም፥ ጳውሎስ አይሁዳዊነት ከፍተኛ ታሪካዊ ጠቀሜታ እንደነበረው አስረድቷል። የቀድሞ ታሪካቸው ሊዘከር የሚገባው ነበር።

| |
|---|
| 4ኛ ጥያቄ፡- የሚያምኑ ሰዎች ያላገኟቸውንና አንተ እንደ እግዚአብሔር ልጅ የምትደሰትባቸውን አንዳንድ በረከቶች ዘርዝር። እግዚአብሔርን ስለ እነዚህ በረከቶች ለማመስገን ጥቂት ጊዜ ውሰድ። |

<u>3. ጳውሎስ እግዚአብሔር አጽንኦት የሚሰጠው ከሥጋዊ አይሁዳዊነት ይልቅ ለመንፈሳዊ አይሁዳዊነት እንደሆነ ገልጾአል</u> (ሮሜ 9፡6–29)።

በዚያን ጊዜ የአይሁድ ክርስቲያኖች ጳውሎስን የሚጠይቁት ሌላም ጥያቄ ነበራቸው። ክርስቶስ የአይሁዶችን የኃጢአት ችግር የሚቀርፍና የብሉይ ኪዳን ተስፋዎች ፍጻሜ የሆነው መሢሕ ከሆነ፥ ብዙ አይሁዶች ያላመኑበት ለምንድን ነው? ይህ ክርስቶስ መሢሕ አለመሆኑን አያረጋግጥም? ጳውሎስ ለዚህ ጥያቄ በሰጠው ምላሽ የሚከተሉትን አሳቦች ትኩረት ሰጥቶ አብራርቷል።

ሀ. በትውልድ አይሁዳዊ የሆነ ሁሉ እውነተኛ አይሁዳዊ አይደለም (ሮሜ 9፡6–13)። እስማኤልንና ሌሎችንም ጨምሮ አብርሃም ብዙ ልጆች ነበሩት (ዘፍጥ. 25፡1–4)። ከእነዚህ ልጆች መካከል የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያመለክተውና የተስፋ ቃል ፍጻሜ የሆነው ይስሐቅ ብቻ ነበር። ርብቃ ሁለት ልጆች ወልዳለች። ዔሣው ታላቅ በመሆኑ፥ እንደ ደንቡ ከሆነ በአይሁዶችና በያዕቆብ የዘር ሐረግ ውስጥ መግባት ነበረበት። ነገር ግን አንዱ የተሻለ ወይም የከፋ በመሆኑ ሳይሆን እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ ስለመረጠው ያዕቆብ የተስፋ ልጅ ሆኗል። በተመሳሳይ መንገድ፥ ሥጋዊ አይሁዳዊ የሆነ ሁሉ መንፈሳዊ አይሁዳዊ አይደለም። ምክንያቱም የአብርሃምን ዓይነት መንፈሳዊ እምነት ያልያዙ አይሁዶች ሁሉ እውነተኛ አይሁዶች ስላይደሉ እነዚህ እንደ ይስሐቅና እንደ ያዕቆብ ሳይሆኑ፥ እንደ እስማኤልና ዔሣው ነበሩ።

ለ. ደኅንነት የሚወሰነው በእግዚአብሔር ምርጫ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመረዳት እጅግ ከሚያስቸግሩ አሳቦች አንዱ እግዚአብሔር ለደኅንነት ሰውን በሚመርጥበትና ሰው እግዚአብሔርን በሚመርጥበት ተግባር መካከል ያለው ግንኙነት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሚድኑትን እንደሚመርጥ፥ የእግዚአብሔር የደኅንነት ስጦታ ለሰዎች ሁሉ ክፍት እንደሆነና ምላሽ የሚሰጡት እንደሚቀበሉ ያስተምራል። በሰብአዊ ደረጃ እነዚህ ሁለት እውነቶች እንዴት አብረው እንደሚሠሩ አናውቅም። በዚህ ስፍራ ጳውሎስ እግዚአብሔር የሚድኑትን እንደሚመርጥና እንደሚወስን ገልጾአል። ይህ እውነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚከተለው መልኩ ቀርቧል።

1. እግዚአብሔር ሁለቱም ከመወለዳቸው በፊት ዔሳውን ሳይሆን ያዕቆብን መርጦታል።

2. እግዚአብሔር ለወደደው ምሕረቱን እንደሚያሳይና በጠላው ላይ ደግሞ ፍርዱን እንደሚያወርድ ለሙሴ ነግሮታል።

3. እግዚአብሔር ፈርዖንን ወደ ሥልጣን እንዳመጣውና አይሁዶችን ላለመልቀቅ እንዲወስን እንዳደረገው ገልጾአል። ይህንንም ያደረገው በአሥሩ መቅሠፍቶችና በአይሁዶች ነፃ መውጣት ክብሩ በዓለም ላይ እንዲገን በመፈለጉ ነበር።

ሐ. እግዚአብሔር አንዳንዶችን ለደኅንነት በመምረጡ አድልዎ አልፈጸምም (ሮሜ 9፡19–29)። እግዚአብሔር አንዳንዶችን ለደኅንነት መምረጡና ሌሎችን መተዉ ፍትሐዊ አይደለም ብለን ከማጉረምረማችን በፊት፥ ጳውሎስ በሮሜ 1–3 የገለጸውን አሳብ ማስታወስ አለብን። ይህ አንዳንድ ሰዎች ለመዳን ጥረት እያደረጉ ሳለ እግዚአብሔር በሰማይ ላይ ተቀምጦ ዕጣ እያወጣ «አትድንም» ሲል የከለከለበትን ሁኔታ የሚያሳይ አይደለም። ወይም ደግሞ አንዳንዶች ለመዳን ሳይፈልጉ እግዚአብሔር አስገድዶ እንዳሳመናቸው የሚያሳይ አይደለም። ይልቁንስ ጳውሎስ ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ሆነው በእግዚአብሔር ላይ እንዳመፁ አብራርቷል። ሰዎች ሊድኑ የሚችሉበት ብቸኛው መንገድ በእግዚአብሔር ምሕረት አማካኝነት ነው። ስለሆነም፥ እግዚአብሔር ለአንድ ሰው ምሕረትንና ደኅንነትን ለመስጠት መምረጡና ይህንኑ ተመሳሳይ ተግባር ለሌላው ሰው አለመፈጸሙ አድልዎአዊ ነው አያስብለውም።

ጳውሎስ እግዚአብሔር አንድን ሰው እየመረጠ ሌላውን መተዉ ፍትሐዊ አይደለም ለሚሉ ሰዎች በሰጠው ምላሽ፥ የሚከተሉትን እውነቶች እንዲገነዘቡ ያሳስባቸዋል።

1. እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው፥ እኛ ሰዎች ግን ማንን ሊመርጥ እንደሚችልና እንደማይችል የመናገር መብት የለንም። እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ እግዚአብሔር ሊሆን የሚገባውንና የማይገባውን፥ ፍትሐዊ የሆነውንና ያልሆነውን የሚወስን የመጨረሻው ባለሥልጣን መሆኑን እንደዘነጋን ያሳያል።

2. አንድ ሸክላ ሠሪ የተለያዩ ዓይነት የሸክላ ዕቃዎችን የመሥራት መብት አለው። አንዳንድ ዕቃዎች (ወጭቶች) ለምግብ ማቅረቢያ አምረው ሲሠሩ፥ ሌሎች ደግሞ ለውኃ ማምጫ ይውላሉ። እነዚህ ሸክላዎች የማጉረምረም መብት እንደሌላቸው ሁሉ፥ መለኮታዊ ሸክላ ሠሪ የፈጠራቸው ሰዎችም በእግዚአብሔር ውሳኔዎች ላይ የማጉረምረም መብት የላቸውም።

3. ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ቁጣ የሚገባቸው ኃጢአተኞች ናቸው። የማናችንም ደኅንነት የእግዚአብሔርን ምሕረት እንጂ እኛ ከሌሎች ሰዎች የተሻልን መሆናችንን የሚያሳይ አይደለም። እግዚአብሔር ደግሞ አይሁዶችም ሆኑ አሕዛብ እንዲድኑና በመንግሥተ ሰማይ እንዲከብሩ

መርጧቸዋል። የሰው ልጆች ማን እንደተመረጠና እንዳልተመረጠ አስቀድሞ የማወቅ ችሎታ እንደሌላቸው መገንዘቡ ጠቃሚ ነው። አንድ ሰው «እኔ በክርስቶስ ለማመን ብፈልግም፥ እግዚአብሔር አልጠራኝም» ሊል አይችልም። ወይም ደግሞ «እገሌ ክርስቲያን ያልሆነው እግዚአብሔር ስላልመረጠው ነው» ልንል አንችልም። ልናውቅ የምንችለው ነገር ቢኖር፥ ሀ) የእግዚአብሔር የደኅንነት ስጦታ ለማመን ለሚፈልጉ ሁሉ ክፍት እንደሆነና «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን ትድንማለህ» ብሎ የመስበክ ኃላፊነት ነው ያለብን። ለ) ከልባቸው የሚያምኑ ሰዎች በእግዚአብሔር እንደተመረጡ ነው። ይህ ግን የግል ውሳኔያቸው ብቻ አይደለም።

4. በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር፥ ሀ) በታሪክ ሕዝቡ ያልነበሩትን እንደሚመርጥ፥ ለ) የአይሁድን ቅሬታ ብቻ እንደሚያድንና በሌሎቹ ላይ እንደሚፈርድ፥ ሐ) እግዚአብሔር ከምሕረቱ የተነሣ ሁሉንም እንደ ሰዶምና ገሞራ ከማጥፋት ይልቅ አንዳንዶችን እንዳዳነ ተናግሯል።

| |
|---|
| 5ኛ ጥያቄ፦ ጳውሎስ ደኅንነት የእግዚአብሔርም የሰውም ምርጫ እንደሆነ ያብራራበትን ሁኔታ በራስህ አገላለጽ ጠቅለል አድርገህ ጻፍ። |

4. <u>ብዙ አይሁዶች እግዚአብሔር የማይቀበለውን የደኅንነት መንገድ በመከተላቸው ምክንያት አልዳኑም</u> (ሮሜ 9፡30–33)። «አይሁዶች በኢየሱስ የማያምኑት ለምንድን ነው? ይህ ክርስቶስ መሢሕ አለመሆኑን አያሳይምን?» በማለት ሰዎች ጳውሎስን ይጠይቁት ነበር። ጳውሎስ ላለማመናቸው ምክንያቱ የክርስቶስ መሢሕ አለመሆን ሳይሆን አይሁዶች ደኅንነትን (ጽድቅን) በተሳሳተ መንገድ መፈለጋቸው እንደሆነ አብራርቷል። አይሁዶች ከእግዚአብሔር ዘንድ ደኅንነትና ማረጋገጫ ለመቀበል የፈለጉት በውርሳቸው፥ በግርዛታቸውና በመልካም ሥራቸው አማካኝነት ነበር። እግዚአብሔር ያዘጋጀው የደኅንነት መንገድ ግን ይሄ አልነበረም። በድንጋዩ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ በመሰናከላቸው ምክንያት ደኅንነትን ሊያገኙ አልቻሉም። ታሪካዊ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዳልሆኑና የእግዚአብሔርን ምሕረት ለመቀበል በክርስቶስ ሞት ማመን እንደሚያስፈልጋቸው የተገነዘቡት አሕዛብ ግን ደኅንነትን አግኝተዋል። አሕዛብ የራሳቸውን ጽድቅ ከመመልከት ይልቅ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ተቀበሉ።

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፦ አማኞች ነን የሚሉትን ጨምሮ ሃይማኖተኛ ሰዎች እግዚአብሔር ከሚሰጠው ጽድቅ በላይ በራሳቸው ጽድቅ ላይ በማተኮራቸው ምክንያት ዛሬ የደኅንነትን መንገድ ለማግኘት የሚቸገሩት እንዴት ነው? |

ጳውሎስ አይሁዶች ስላልዳኑበት ሁኔታ ማብራራቱን ይቀጥላል። በዚህ ጊዜ ጳውሎስ በደኅንነት ውስጥ እግዚአብሔር ከሚያበረክተው ድርሻ ይልቅ በሰዎች ድርሻ ላይ ያተኩራል።

5. <u>አይሁዶች የእግዚአብሔርን የደኅንነት ዕቅድ አልተገነዘቡም</u> (ሮሜ 10፡1–4)። አይሁዶች የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን በቅንዓት ቢጠብቁም፥ ቅንዓታቸው ደኅንነትን ሊያስገኝላቸው አልቻለም። ብዙ ጊዜ አንድ ሰው ቀናተኛና ሃይማኖተኛ ሆኖ እምነቱን የሚከተል ከሆነ እግዚአብሔር ይቀበለዋል ብለን እናስባለን። ነገር ግን ቡድሂስቶች፥ ሙስሊሞችም ሆኑ

ሌሎች ሕዝቦች ለሃይማኖታቸው ቀናተኞች እንደሆኑ መገንዘብ ይኖርብናል። ቅንዓት አንድን ነገር ትክክል ሊያደርግ አይችልም። አንድ ሰው ስለ አንድ ነገር ቀናተኛ ሊሆንና የተሳሳተ ሊሆን ይችላል። ቅንዓት ከትክክለኛ እውቀት ጋር መዋሃድ አለበት። አይሁዶች ያላገኙትም የደኅንነትን መንገድ ትክክለኛ ግንዛቤ ነበር። የእግዚአብሔር አቀባበሉ፥ ጽድቁ፥ «ጥፋተኛ አይደለህም» የሚለው እወጃው እንዴት በስጦታ መልክ እንደሚመጡ አላውቁም ነበር። ይህ በራሳቸው ጥረት የሚያገኙት ነገር አይደለም። መሢሐቸው ክርስቶስ በፖለቲካዊ ጠላቶቻቸው ላይ ድልን እንደሚነሣ ንጉሥ ሳይሆን እንደ የኃጢአት መሥዋዕት መምጣቱን ሊገነዘቡ አልቻሉም።

6. <u>ደኅንነት ወይም «ጻድቅ ነህ» የሚል እወጃ የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ የሚቀበሉት እንጂ የማይቻል ነገር አይደለም</u> (ሮሜ 10፡5-13)። ጳውሎስ ሁለት የደኅንነት መንገዶችን ለማነጻጸር ሲል ብሉይ ኪዳንን ይጠቀማል። የመጀመሪያው፥ አይሁዶች ደኅንነትን ለማግኘት የሚያስችል በጎነት ለመቀዳጀት ያደረጉት ጥረት ነው። ዘሌዋውያን 18፡5 እንደሚለው፥ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ሕግጋቱን ሙሉ በሙሉ መፈጸም ያስፈልጋቸው ነበር። ነገር ግን ይህ ለሁሉም ኃጢአት የሚሠራ አለመሆኑን ጳውሎስ ቀደም ብሎ አመልክቷል። ስለሆነም፥ መንፈሳዊ ሕይወት ሕግጋትን ከመከተል ሊገኝ አይችልም።

የእግዚአብሔር የሆነው ሁለተኛው የደኅንነት መንገድ ግን ከፍተኛ ብርታትንና ተአምራትን አይጠይቅም። ወደ ቅዱስ ስፍራዎች የሚደረጉ ረዣዥም ጉዞዎች ለደኅንነት የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ አይኖርም። የእግዚአብሔር ደኅንነት ሰዎች ሁሉ ይቀበሉት ዘንድ በአጠገባቸው አለ። ደኅንነትን ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት ከማድረግ ይልቅ ማመን እንደሚያስፈልግ ጳውሎስ አብራርቷል። ክርስቶስ የኃጢአታችንን ቅጣት የከፈለ የግል መሥዋዕታችን እንደሆነ ከልባችን ማመን አለብን። እንዲሁም ክርስቶስን እንደ ጌታችን ለመከተል ቆራጥ ውሳኔ ማድረግ አለብን። ይህ ውስጣዊ ተግባር በኃፍረት ተሸማቅቀን ከሰዎች የምንደብቀው ዓይነት ሳይሆን፥ በይፋ የሚታወጅ ነው። አንድ አይሁዳዊ ወይም አሕዛብ ይህን ቀላልና ነገር ግን ሕይወት ለዋጭ ውሳኔ በሚያደርግበት ጊዜ የእግዚአብሔር ጽድቅና በረከት ሕይወቱን ይሞላዋል።

8ኛ ጥያቄ፦ ብዙውን ጊዜ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች አንድ ሰው ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ መቀበል እንዳለበት በሚያስረዳው እውነት ላይ ቢያተኩሩም፥ ግለሰቡ ክርስቶስን እንደ ጌታውም አድርጎ መቀበል እንዳለበት አያብራሩም። ሀ) ይህ ሚዛናዊ አስተምህሮ ይመስልሃል? ለ) አንድ ሰው ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ለመቀበልና በጌትነቱ ሥር ለመኖር ቃል መግባት ያለበት ለምን እንደሆነ አብራራ? ሐ) ሮሜ 10፡9-10ን በቃልህ አጥና።

7. <u>ሰዎች ለማመን ወንጌሉን መስማት አለባቸው</u> (ሮሜ 10፡14-15)። እግዚአብሔር ስለ ክርስቶስ ባልሰሙት ሰዎች ላይ አይፈርድም የሚሉ አንዳንድ ምዕራባውያን ክርስቲያኖች አሉ። ምንም እንኳ ጳውሎስ በዚህ ጉዳይ ላይ ባያተኩርም፥ ቀደም ሲል ወንጌልን ያልሰሙትን ጨምሮ አሕዛብ ሁሉ እግዚአብሔር በልባቸው ውስጥ ያስቀመጠውንና በተፈጥሮ

የገለጣቸውን እውነቶች ሆን ብለው ስላላከበሩ ኃጢአተኞች መሆናቸውን ገልጾአል። በክርስቶስ ላይ ያለ እምነት ሊፈጠር የሚችለው እንደ ጳውሎስ ብርቱ ትምህርት ሲሰማና ሲያምን ብቻ ነው። ለዚህም ነበር ምንም ወንጌል ወዳልተሰበከበት የስፔይን አገር ለመሄድ የፈለገው። እግዚአብሔር ሰዎችን ወደ ደኅንነት የሚያመጣበት መንገድ የእግዚአብሔር ልጆች የማመን ዕድል ያገኙ ዘንድ ወንጌሉን ላልሰሙት ሰዎች በሚሰብኩበት ጊዜ ነው። ጳውሎስ ይህ የሐዋርያ፥ የወንጌላዊ ወይም የሚሲዮናዊ ኃላፊነት ብቻ እንዳልሆነ አመልክቷል። ነገር ግን ጠቅላላይቱ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር መልእክተኞቹ እንዲሆኑ የመረጣቸውን ሰዎች የመላክ ኃላፊነት አለባት። ጳውሎስ የሮም ክርስቲያኖች በስፔይን ወንጌልን በመሰብክ ሥራው ላይ እንዲተባበሩት አበረታቷቸዋል።

ይህ በጣም አስፈላጊ አገልግሎት በመሆኑ፥ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ጥሪ ሰምተው ወንጌሉን ወዳልሰሙት ወገኖች የሚያደርሱ ሰዎች ያማረ እግር እንዳላቸው አመልክቷል። ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ለመማርና ጥሩ ሥራ ለመያዝ ወይም የራሳቸውን «ቢዝነስ» ለመክፈት ይፈልጋሉ። ጳውሎስ ግን ሥራቸውን በእግዚአብሔር እይታ እንዲመለከቱ ያበረታታቸዋል። ሰዎች ወንጌልን መስበክ ጊዜ ማጥፋትና ላልተማሩትና ሌላ ሥራ ሊያገኙ ለማይችሉ ሰዎች ሥራ መፍጠሪያ ነው ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። በእግዚአብሔር ዓይኖች ግን ይህ እጅግ ውብ የሆነ ሥራ ነው።

> 9ኛ ጥያቄ፦ ሀ) በኢትዮጵያ ብዙ አማኞች የሌሉባቸውን ጎሳዎች ዘርዝር። ለ) አምነው ይድኑ ዘንድ ወንጌልን በማድረሱ በኩል እግዚአብሔር ከአንተና ከቤተ ክርስቲያንህ ምን የሚፈልግ ይመስልሃል? ሐ) ጥቂት ወጣቶች ለጠፉት ወንጌል መስበክን እንደተከበረ ሙያ የሚያዩት ለምን ይመስልሃል? በሕይወት ጠቃሚ ስለሆነው ነገር የእግዚአብሔርን እይታ በተሳሳተ መንገድ የተገነዘቡት እንዴት ነው?

8. <u>ጳውሎስ አይሁዶች የእግዚአብሔርን የደኅንነት ጥሪ እንዴት እንደተቃወሙ ያብራራል</u> (ሮሜ 10፡ 16-21)። በጳውሎስ ዘመን፥ በቀድሞዪቱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለውጦች ተካሂደዋል። እስከዚህ ጊዜ ድረስ፥ ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም የተማከለች ስትሆን፥ ብዙ አይሁዶች ክርስቶስን እንደ መሢሐቸው ተቀብለውት ነበር። አሁን ግን ቤተ ክርስቲያን በአሕዛብ መካከል በፍጥነት በመስፋፋቷና በኢየሩሳሌም ብሔርተኝነት እያደገ በመምጣቱ፥ ብዙ አይሁዶች በክርስቶስ ላለማመን ወሰኑ። በዚህ ጊዜ በፍልስጥኤም በአሕዛብ ላይ ፖለቲካዊ ጠላትነት እያደገ ከመምጣቱም በላይ፥ የሮምም ጭቆና ተጠናክሮ ነበር። ከዚህም የተነሣ በክርስቶስ የሚያምኑ አይሁዶች በቁጥር እየቀነሱ ሄዱ። ቀደም ሲል ያመኑትም በክርስቶስ ላይ የነበራቸውን እምነት ትተው ወደ ቀደመው የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት እንዲመለሱ ግፊት ተደረገባቸው። የዕብራውያን መጽሐፍ እምነታቸውን ለመተው በተፈተኑት በእነዚህ አይሁዶች ላይ ትኩረት ያደርጋል።

ጳውሎስ በክርስቶስ ያመኑ ብዙ አይሁዶች እንዳሉ ቢያምንም፥ አንዳንዶች በክርስቶስ ላይ የተቃዋሚነት አቋም ይዘው ነበር። ይህ ግን ጳውሎስን አላስደነቀውም። በብሉይ ኪዳን ውስጥ አይሁዶች የእግዚአብሔርን መልእክት እንደማይቀበሉ የሚገልጸውን ሰፊ ጭብጥ ተመለከተ። ኢሳይያስ

ምንም እንኳ እግዚአብሔር እጆቹን ዘርግቶ ወደ እርሱ እንዲመለሱ ቢጠይቃቸውም፥ አይሁዶች በእግዚአብሔር መልእክት ለማመን አለመፈለጋቸውን መስክሯል። ነገር ግን ታሪካዊ የእግዚአብሔር ሕዝብ ያልነበሩት አሕዛብ ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ደኅንነትን ያገኙ ነበር። ይህም ሙሴ እግዚአብሔር አንድ ቀን አይሁዶችን ለማስቀጣት ሲል አይሁዶች ባልሆኑት ሰዎች መካከል እንደሚሠራ የተነበየው ትንቢት ነበር።

2. ምንም እንኳ ሁልጊዜም ለደኅንነታቸው በክርስቶስ የሚያምኑ የአይሁድ ቅሬታዎች ቢኖሩም፥ እስራኤላውያን ሁሉ የሚድኑበት ጊዜ ይመጣል (ሮሜ 11)።

---

10ኛ ጥያቄ፡- ሮሜ 11ን አንብብ። ሀ) ጳውሎስ እግዚአብሔር ከአይሁዶች ጋር ስለሚያደርገው የአሁንና የወደፊት ግንኙነት ምን አለ? ለ) ጳውሎስ ለአሕዛብ ክርስቲያኖች የሰጣቸው ማስጠንቀቂያ ምን ነበር?

---

አይሁዶች እንደ ሕዝብ የእግዚአብሔርን የደኅንነት መንገድ ለመቀበል ስላለመፈለጋቸው ጳውሎስ የሚሰጠውን ትንታኔ የሚሰማ አይሁዳዊ ክርስቲያን፥ «ይህ ማለት እግዚአብሔር ከእንግዲህ ለአይሁዶች ልዩ ዕቅድ የለውም ማለት ነው?» የሚል ጥያቄ ማንሣቱ የማይቀር ነው። ጳውሎስ ለዚህ ጉዳይ በሦስት መንገዶች ምላሽ ሰጥቷል።

1. በታሪክ ሁሉ እግዚአብሔር በእርሱ የሚያምኑ ቅሬታዎች አሉት (ሮሜ 11፡1-10)። ራሱ ጳውሎስና የአይሁድ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር አይሁዶችን ሙሉ ለሙሉ ላለመተዉ ማረጋገጫዎች ናቸው። እግዚአብሔር በጨለማው የእስራኤል ታሪክ እንዳሳየው፥ ኤልያስ ታማኝ የእግዚአብሔር ተከታይ እኔ ብቻ ነኝ በሚልበት ወቅት ሌሎች 7,000 ታማኝ ተከታዮች ነበሩት (1ኛ ነገ. 19)። አብዛኞቹ አይሁዶች «የመንፈስ ድንዛዜ» ቢደርስባቸውም፥ ታማኝ ቅሬታዎች የእግዚአብሔርን የደኅንነት መንገድ ተከትለው በክርስቶስ አምነዋል። በአሁኑ ጊዜ አይሁዶች ክርስቲያኖች ወገኖቻቸውን በወንጌል ለመድረስ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው። ብዙ አይሁዶችም ክርስቶስን ለማመን እንደ መሲሐቸው አድርገው ለመከተል እየወሰኑ ነው።

2. እግዚአብሔር «የአሕዛብን ዘመን» ዐቅዷል። ይህም ብዙ አሕዛብ በክርስቶስ የሚያምኑበትና ቀደም ሲል አይሁዶች ያገኙ የነበረውን በረከት የሚቀበሉበት ነው (ሮሜ 11፡11-24)። ጳውሎስ የአሕዛብ ክርስቲያኖች አሁን ከአይሁዶች ይልቅ እነርሱ የእግዚአብሔርን ሞገስ እንዳገኙ በማሰብ እንዳይታበዩ ሰግቶ ነበር። ስለሆነም፥ የእግዚአብሔርን ረዥም የደኅንነት ዕቅድ በሰፊው ያብራራል። ይህ ለአሕዛብ የተሰጠው ጸጋ ጊዜያዊ ይሆናል። ይህም እግዚአብሔር አይሁዶችን አስቆጥቶ ወደ ራሱ የሚመልስበት መንገድ ነበር። በእግዚአብሔር ዕቅድ፥ አይሁዶች የእግዚአብሔርን የደኅንነት መንገድ አለመቀበላቸው በአንድ ወቅት ከእግዚአብሔር ሕዝብ ተገልለው ለነበሩት አይሁዶች የደኅንነትን መንገድ ከፍቷል። ጳውሎስ አንድ ቀን አይሁዶች እንደ ሕዝብ በክርስቶስ የሚያምኑ ሲሆን፥ ደኅንነታቸውም ለዓለም የበለጠ በረከትን ያመጣል በማለት ተስፋውን ተናግሯል።

ጳውሎስ እግዚአብሔር እያደረገ የነበረውን ተግባር ለማብራራት አያሌ ምሳሌዎችን ተጠቅሟል።

ሀ. አይሁዶች ከመጀመሪያው የመከር እህል ያዘጋጁትን ሊጥ ለእግዚአብሔር ስለሚሠዉበት ሁኔታ ይገልጻል። ይህም ለእግዚአብሔር የተሠዋውን እርሾ ብቻ ሳይሆን የተቀረውንም ሊጥ በመቀደስ (በመለየት)፥ እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንደሚያሟላላቸው ያመለክታል። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ እግዚአብሔር የእምነት አባቶችን ልዩ ሕዝቡ አድርጎ ስለመረጣቸው፥ የተቀሩትም አይሁዶች ለእግዚአብሔር ልዩ ይሆናሉ። (በዚህ ክፍል «ቅዱስ» የሚለው ቃል ኃጢአት-አልባነትን ሳይሆን «መለየት»ን ያሳያል።)

ለ. ጳውሎስ በተጨማሪም የአይሁዶችንና የአሕዛብን ግንኙነት ከወይራ ዛፍ ጋር ያነጻጽረዋል። አይሁዳውያን ካሏቸው ዋና ዋና ተክሎች መካከል አንዱ የወይራ ዛፍ ነው። ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ልጆች በወይራ ዛፍ መስሏቸው ነበር። ዋነኞቹ የወይራ ዛፍ በልዩ ሁኔታ የተመረጡት የብሉይ ኪዳን ሕዝቦች አይሁዶች ነበሩ። አሕዛብ ክርስቲያኖች በዚያው የወይራ ዛፍ ላይ የተተከሉ የበረሃ ቅርንጫፎች ናቸው። (ብዙውን ጊዜ ሰው ጥሩ ቅርንጫፎችን በበረሃ ዛፍ ላይ ለማዳቀል ያጣብቃል እንጂ የማይጠቅም የሚመስለውን የበረሃ ቅርንጫፍ በጥሩ ዛፍ ላይ አያጣብቅም። የእግዚአብሔር ጸጋ ግን ኃጢአተኛ አሕዛብን ወደ ትውፊታዊ የእግዚአብሔር ቤተሰብ በማምጣት በዚህ መንገድ ይሠራል።) ክርስቶስን የተዉት የአይሁድ ሕዝብ ፍሬያማ ባለመሆናቸው ምክንያት ከዛፍ እንደተቀረጡ ቅርንጫፎች ናቸው። ነገር ግን የአሕዛብ ክርስቲያኖች መመካት እንደሌለባቸው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል። ወደ እግዚአብሔር የበረከት ዛፍ ለመግባት የሚያበቃ ምንም ዓይነት ተግባር አላከናወኑም። ይህ የእግዚአብሔር ምሕረት ያስገኘላቸው በረከት ነበር። ጳውሎስ አሕዛብ እንዲጠነቀቁ ያሳስባል። ካልታዘዙ እነርሱም ከእግዚአብሔር በረከት ሊቆረጡና ሊወገዱ ይችላሉ። ጳውሎስ እግዚአብሔር አንድ ቀን ተፈጥሯዊ ቅርንጫፎቹ የሆኑትን አይሁዶች ወደ በረከት ዛፍ መልሶ እንደሚተክላቸው ገልጾአል።

3. <u>አንድ ቀን እግዚአብሔር አይሁዶችን እንደ አንድ ሕዝብ ያድናቸዋል</u> (ሮሜ 11:25-32)። በዚህ ጊዜ አይሁዶች የአሕዛብ ክርስቲያኖችን ቢያሳድዱም፥ ይህ ማለት እግዚአብሔር አይሁዶችን ሙሉ ለሙሉ ከዕቅዶቹ ሠርዟቸዋል ማለት አልነበረም። «የአሕዛብ ሙላት ከተፈጸመ በኋላ» እግዚአብሔር አይሁዶችን እንደገና በመነቃቃት ብዙዎቹን ያድናቸዋል።

ጳውሎስ ይህን እውነት «ምሥጢር» ብሎ ይጠራዋል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ምሥጢር ለሌላ ሰው የማይነገር አሳብ ማለት ሳይሆን፥ በብሉይ ኪዳን ተሰውሮ የነበረና በአዲስ ኪዳን ግን እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገለጠው እውነት ነው።

የአሕዛብ ሙላት ማለት ምን ማለት ነው? «እስራኤል ሁሉ» በሚለው ውስጥ የተካተቱትስ እነማን ናቸው? በዚህ ጉዳይ ላይ የሚቀርቡ የተለያዩ አተረጓጎሞች ቢኖሩም፥ ጳውሎስ በዚህ የአሕዛብ ወይም የቤተ ክርስቲያን ዘመን እግዚአብሔር በአሕዛብ ደኅንነት ላይ ማተኮሩን ለማሳየት ይፈልጋል።

በቤተ ክርስቲያን ዘመን የተወሰነ ቁጥር ያላቸው አሕዛብና የተወሰነ የደኅንነት ጊዜ ስላለ፥ በዋናነት አሕዛብ ይድናሉ። የተመረጡት አሕዛብ በሙሉ ከዳኑ በኋላ፥ ታሪኩ አቅጣጫውን ይቀይራል። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር በአይሁዶች መካከል በመሥራት በክርስቶስ እንዲያምኑ ያደርጋል። ይህ ማለት ግን እያንዳንዱ አይሁዳዊ ደኅንነትን ያገኛል ማለት አይደለም። ነገር ግን እንደ አንድ ሕዝብ ብዙ አይሁዶች በክርስቶስ አምነው ይድናሉ። ከእንግዲህ አይሁዶች በጥረታቸው ደኅንነትን ለማግኘት መሞከራቸውን አቁመው እንደ አሕዛብ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ምሕረት ፊታቸውን ያዞራሉ። ጳውሎስ እግዚአብሔር ለስጦታዎቹና ለመጥራቱ አይጸጸትም ብሏል። በሌላ አገላለጽ፥ እግዚአብሔር ሊዋሽ ስለማይችል በብሉይ ኪዳን ለአብርሃምና ለአይሁዶች የሰጣቸው የተስፋ ቃሎች ይፈጸማሉ።

4. <u>ለእግዚአብሔር ታላቅ ጥበብ የቀረበ የምስጋና መዝሙር</u> (ሮሜ 11፡33–36)። እግዚአብሔር የአይሁዶችን አለመታዘዝ ተጠቅሞ አሕዛብን ማዳኑና በኋላም አይሁዶች በአሕዛብ ደኅንነት ቀንተው ወደ እርሱ እንዲመለሱ ማድረጉ አስደናቂ ነገር አይደለምን? ጳውሎስ የእግዚአብሔር መንገድ ከሰዎች ማስተዋል ይልቅ ምሥጢራዊ መሆኑን የሚገልጽ መዝሙር ተቀኝቷል። የደኅንነትና የበረከቶች ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር ነው። በረከቱን የሚያመጣልን እርሱ ሲሆን፥ ይህንንም ለክብሩ ይጠቀምበታል። ልናደርግ የምንችለው ነገር ቢኖር እርሱን ለዘላለም ማክበር ነው (ሮሜ 11፡33–36)።

ይህ የጳውሎስ መዝሙር እግዚአብሔር በአንድ ሁኔታ ውስጥ የሚያደርገውን ሁሉ እንገነዘባለን እንዳንል ሊያስጠነቅቀን ይገባል። «ኃጢአትን ስለሠራህ እግዚአብሔር እየፈረደብህ ነው። እግዚአብሔር ልጅ ያልሰጠህ የበለጠ እንድታምነው ነው። እግዚአብሔር በአገሪቱ ላይ ረሃብን ያመጣው ኃጢአተኞች ስለሆኑ ነው።» እነዚህ ሁሉ አሳቦች እግዚአብሔር በአንድ ሁኔታ ውስጥ ምን ዓላማ እንዳለው እናውቃለን ባይነታችንን ያሳያሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር የሚያደርገው ነገር በአብዛኛው ከእኛ የተሰወረ ምሥጢር ነው። ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር የሚሠራው እኛ ከምንጠብቀው መንገድ ውጭ ነው። እግዚአብሔር ክፉውን የኮሚዩኒዝም ዘመን ተጠቅሞ ቤተ ክርስቲያንን እንዲህ በፍጥነት ያሳድጋታል ብሎ ማን ያሰበ ነበር? ጳውሎስ እንደሚለው፥ የእግዚአብሔር መንገድ ከማስተዋል ያለፈ መሥጢራዊ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል። የእርሱ መንገዶች ሁልጊዜም አስደናቂዎች በመሆናቸው፥ ሁሉም ነገር ከእርሱ እንጂ ከአመክንዮአችን (Logic)፥ ከትምህርታችን፥ ከዘዴያችን፥ ከመዋቅራችን፥ ወዘተ... እንደማይመጡ ልንገነዘብ ይገባል።

11ኛ ጥያቄ፡– እግዚአብሔር ያደረገውና ምሥጢር የሆነብህን ነገር ዘርዝር? ለ) እግዚአብሔር ሰዎች ከሚያደርጉት መንገድ ፍጹም በተለየ ሁኔታ ያከናወነውንና ለእግዚአብሔር ታላቅ ክብር ያስገኘውን አንድ ነገር ጥቀስ። ሐ) አሁን ጊዜ ውሰድና እግዚአብሔርን ስለ ታላቅ ጥበቡና እውቀቱ፥ በማትገነዘብበት ጊዜ እንኳ ነገሮችን ሁሉ ስለ መቆጣጠሩ አመስግነው።

## ሁለተኛ ቀን፤ ሮሜ 12–13

ጥሩነሽ በቅርቡ በክርስቶስ አምናለች። መንፈስ ቅዱስ ኃጢአተኛ እንደሆነችና ይቅርታ ልታገኝ የምትችልበት ብቸኛው መንገድ ለኃጢአቷ በሞተው በክርስቶስ በማመን መሆኑን ለልቧ መስክሮላታል። ጥሩነሽም በኃጢአተኝነት ስሜት ተሞልታና እግዚአብሔር ለእርሷ ስላለው ፍቅር ተደንቃ ክርስቶስ ለኃጢአቷ የሞተ አዳኝዋና ጌታዋ እንደሆነ አመነች። በዚህ ጊዜ ሰላም ልቧን ሞላው። የእግዚአብሔር ልጅ ሆነች።

ነገር ግን ከዚህ በኋላ ማድረግ ያለባት ነገር ምንድን ነው? አሁን ልጁ ከሆነች በኋላ እግዚአብሔር ምን እንድታደርግ ይፈልጋል? ሕይወቷ እንዴት ሊለወጥ ይገባል? ክርስቲያኖችን ስትጠይቅ ሁሉም ከመጠጥ፥ ከሲጋራ፥ ከጫት፥ ከዘፈን ወደ ፊልም ቤት ከመሄድ፥ ወዘተ... መታቀብ እንዳለባት ይነግሯታል። ሌሎች ክርስቲያኖች ደግሞ ዋናው መዳኗ እንደሆነ በመግለጽ ደስ ያላትን ሁሉ ልታደርግ እንደምትችል ይነግሯታል። በእነዚህ የአሳብ ግጭቶች ግራ የተጋባችው ጥሩነሽ ብዙም ሳይቆይ ለእግዚአብሔር የነበራትን ፍቅር አጣች።

የወንጌሉ ተግባራዊ አካል የሆነውን ጉዳይ ብዙውን ጊዜ አናነሣውም። ይህም አዳዲስ ክርስቲያኖች እንደ እግዚአሔር ልጆች እንዴት መመላለስ እንዳለባቸው አለማብራራታችን ነው። ክርስቶስ እርሱን ለመከተል ከመወሰናችን በፊት የደቀ መዝሙርነትን ዋጋ መተመን እንዳለብን ተናግሯል (ሉቃስ 14፡25–33)። ነገር ግን እኛ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በክርስቶስ ለማመን የሚፈልጉ ሰዎች ካመኑ በኋላ ምን እንደሚጠበቅባቸው አናብራራላቸውም። ምናልባትም ብዙዎቹ አማኞቻችን ፈጥነው ወደ ዓለም ከሚመለሱባቸው ምክንያቶች አንዱ ይሄ ሳይሆን አይቀርም።

### ወንጌሉ የአማኞችን አኗኗር ይለውጣል (ሮሜ 12፡1–15፡13)።

ጳውሎስ የሮም ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ቁጣ ለመዳን ወይም መንግሥተ ሰማይ በሚደርሱበት ጊዜ የኋላ ኋላ ደኅንነትን እንደሚጎናጸፉ የተስፋ ቃል ለማግኘት ብቻ ሳይሆን፥ የዳኑት እግዚአብሔርን ለማገልገል እንደሆነ ገልጾአል። ሮሜ 12–16 በሮሜ ውስጥ ያለውን ሁለተኛ አጠቃላይ ክፍል ይይዛል። ሮሜ 1–11 የደኅንነትን ምንነት ያብራራል። ከሮሜ 12–16 ጳውሎስ ደኅንነት የአንድን ሰው አጠቃላይ ሕይወት እንዴት እንደሚለውጥና ተግባራዊ ለውጦችንም እንደሚያስከትል ያብራራል። ክርስቶስን የሕይወታችን ሁሉ ጌታ ማድረግ ማለት ምን ማለት ነው?

> 12ኛ ጥያቄ፡– ሀ) አማኝ ከሆንህበት ጊዜ ጀምሮ ሕይወትህ የተለወጠው እንዴት ነው? ለ) ሮሜ 12–13 አንብብ። ክርስቶስ የሕይወታችን ጌታ በሚሆንበት ጊዜ የሚለወጡትን ዐበይት የሕይወታችንን ክፍሎች ዘርዝር። ሐ) ሮሜ 12፡1–2ን በቃልህ አጥና። የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን በኋላ የሕይወታችን ዓላማ ምን እንደሚሆን አብራራ።

1. አማኞች ሙሉ ሕይወታቸውን እንደ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ያቀርባሉ (ሮሜ 12፡1–2)

ጳውሎስ ይህን የሮሜ መልእክት ሁለተኛ ክፍል የሚጀምረው «እንግዲህ» በማለት ነው። «እንግዲህ» የሚለው ቃል ቀደም ሲል በተነገረው አሳብ ላይ ተመሥርቶ ድምዳሜ የሚሰጥ ስለሆነ፥ ይህን ቃል በምንመለከትበት ጊዜ ሁሉ ምንን እንደሚያመለክት ለመረዳት መሞከር አለብን። በዚህ ስፍራ ጳውሎስ ከሮሜ 1-11 ያቀረበውን ትምህርት ለማመልከት የሚፈልግ ይመስላል። እግዚአብሔር በምሕረቱ ልጁ ለኃጢአታችን እንዲሞት በማድረግ፥ ከኃጢአት ኃይል ነፃ በማውጣት፥ የኋላ ኋላ ደኅንነታችንን በማረጋገጥ፥ እንዲሁም ምንም ነገር ከእርሱ ፍቅር ሊለየን እንደማይችል የተስፋ ቃል በመስጠት በሚያስደንቅ መንገድ ስላዳነን፥ ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር የሚኖረን ግንኙነት መለወጥ አለበት። አኗኗራችንም መለወጥ አለበት። ጳውሎስ በዚህ ክፍል ክርስቲያኖች ሊያደርጓቸው ስለሚገባቸው ወይም ስለማይገባቸው ነገሮች ብዙ መመሪያ አለመስጠቱ አስገራሚ ነው። ጳውሎስ ስለ መጠጥ፥ ዕጽ፥ ወዘተ... አይጠቅስም። ለእግዚአብሔር ስለሚኖሩን አመለካከቶችና በክርስቲያኖች መካከል የሚታዩትን ግንኙነቶች በመሳሰሉት ጥልቅ ጉዳዮች ላይ ነበር ትኩረት የሰጠው። ሕይወታችን የሚለወጠው እንዴት ነው? ጳውሎስ ልናደርጋቸው የሚገቡንን አያሌ ነገሮች ይጠቃቅሳል።

ሀ. *ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው፥ ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ።* እግዚአብሔር ልጁን እንደ መሥዋዕት ለእኛ ሰጥቶናል። እኛ ደግሞ ራሳችንን ለእግዚአብሔር መልሰን እንሰጠዋለን። በብሉይ ኪዳን የሚቃጠል መሥዋዕትንና የኃጢአት መሥዋዕትን የመሳሰሉ ብዙ የመሥዋዕት ዓይነቶች ነበሩ። ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ የመስጠትን አሳብ ለማመልከት እንስሳው ሙሉ በሙሉ ስለሚቃጠልበት የሚቃጠል መሥዋዕት ነበር የሚናገረው። ጳውሎስ ሁለንተናችንን ለእግዚአብሔር መልሰን መስጠት እንዳለብን ያስረዳል። ነገር ግን ለእግዚአብሔር የምናቀርበው መሥዋዕት ከኃጢአት የተለየ ቅዱስ መሆን አለበት። እግዚአብሔርን የምናስደስተው በዚህ መልኩ ነው። ለእግዚአብሔር የምናቀርበውን የመጨረሻ አምልኮ የምንገልጸው እንደዚህ ነው። ብዙውን ጊዜ ስለ አምልኮ ስናስብ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለምንዘምራቸው መዝሙሮች፥ የቃለ እግዚአብሔር ስብከት፥ ወዘተ... እናስባለን። ስሜታችንን በብዛት ካንጸባረቅን ፍሬያማ አምልኮ ያካሄድን ይመስለናል። ጳውሎስ ግን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ አምልኮ የሚጀምረው ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለእርሱ በመስጠት እንደሆነ ያስተምራል። ለእግዚአብሔር ክብር የተቀደሰ ሕይወት መኖር አለብን።

13ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እግዚአብሔርን በትክክል አምልኬአለሁ ብለህ ያሰብከው መቼ ነው? የዚያን ጊዜ አምልኮ ለአንተ ልዩ የሆነው በምን ምክንያት ነው? ለ) ለእግዚአብሔር የተሰጠና የተቀደሰ ሕይወት መምራት ለእውነተኛ አምልኮ ምን ያህል አስፈላጊ ነው? ሐ) ብዙ ክርስቲያኖች ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመምጣታቸው በፊት ስለዚህ በአምልኮ ውስጥ የመጀመሪያው እርምጃ ስለሆነው ጉዳይ የማያስቡት ለምንድን ነው? መ) ብዙ ክርስቲያኖች በዕለተ ሰንበት ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር አሳልፈው ሳይሰጡ ለማምለክ የሚፈልጉ ይመስልሃል? መልስህን አብራራ።

*ለ. በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።* ጳውሎስ እነዚህ ክርስቲያኖች ማንን መምሰል እንዳለባቸው ጥብቅ ውሳኔ እንዲያደርጉ ያዝዛቸዋል። በአንዱ በኩል ዓለም አለች። ዓለም ደግሞ የገንዘብን ዋስትና፥ ክብርን፥ ተወዳጅነትን፥ ለግል ጥቅም የሚውልን ትምህርት፥ ወዘተ... ትፈልጋለች። በሌላ በኩል፥ በሙሉ ልባቸው እግዚአብሔርን ለማስደሰት የሚፈልጉ ሰዎች አሉ። ይህ መንገድ ደግሞ ራስን የማዋረድ፥ እግዚአብሔርን የመታዘዝ፥ ሌሎችን የመውደድ፥ የመመስከር፥ ወዘተ... አቅጣጫ ነው። ጳውሎስ በየቀኑ አስተሳሰባችንን የተቆጣጠረው የዓለም መንገድ እንዲገዛን ከመፍቀዱ ይልቅ የእግዚአብሔርን መንገድ ልንመርጥ እንደሚገባ ገልጾአል። ሐዋርያው ዮሐንስም የዓለም አሳብ እንዲገዛን መፍቀድ እንደሌለብን አስተምሯል (1ኛ ዮሐ. 2፡15–17)።

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ከዓለም የሚመጡትንና ክርስቲያኖች ሊለውጧቸው የሚገባቸውን ነገሮች፥ በተለይም ዓለማዊ አመለካከቶች ዘርዝር። ለ) ቤተ ክርስቲያንህ አዳዲስ አማኞች እነዚህን አመለካከቶች እንዲቀይሩ የምታስተምረው እንዴት ነው? |

ነገር ግን እነዚህን ከዓለም የወረስናቸውን አመለካከቶች ልንለውጥ የምንችለው እንዴት ነው? ጳውሎስ ለውጡ የሚመጣው በጸሎት ወይም ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ብቻ እንዳልሆነ አመልክቷል። እነዚህ ነገሮች አስፈላጊዎች ቢሆኑም በዋናነት ለውጥ የሚመጣው አእምሯችንን በማደስ ነው። በአሳባችን ውስጥ ያለው ጉዳይ አስፈላጊ ነው ብለን ያሰብነው ነው። በሕይወታችን ተግባራዊ የምናደርገውም ይህንኑ የምናስበውን ጉዳይ ነው። ስለሆነም፥ አስተሳሰባችንን ብንለውጥና ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር ብናዛምድ፥ ተግባራችንም እንደሚለወጥ ጳውሎስ አብራርቷል።

ራሳችንን ለእግዚአብሔር ክብርና አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ስንሰጥና ወደ ተግባር የሚመራን አስተሳሰባችንን ስንለውጥ፥ ይህ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ወደ ማወቅ እንደሚመራን ጳውሎስ ገልጾአል። ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች፥ በተለይም ወጣቶች ለሕይወታቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ያስባሉ። ማንን ሊያገቡ፥ ምን ዓይነት ትምህርት ሊማሩ፥ ምን ዓይነት ሥራ ሊይዙ፥ የት አካባቢ ሊኖሩ፥ ወዘተ... እንደሚገባቸው ያብሰለስላሉ። እነዚህ ጠቃሚ ጥያቄዎች ቢሆኑም፥ ጳውሎስ ወደ ሁለተኛ ደረጃነት ዝቅ ያደርጋቸዋል። ከሁሉም የሚበልጠው ጥያቄና ለሁላችንም ግልጽ ሊሆን የሚገባው እጅግ ጠቃሚው የእግዚአብሔር ፈቃድ አካል፥ «ሕይወታችንን የምንመራው ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ተሰጥተን ነው ወይ?» የሚለው ሊሆን ይገባል። ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ራሳችንን ሰጥተን ስንኖር፥ ፍላጎቶቻችንና እሴቶቻችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተገለጹት ጋር አንድ ዓይነት ሲሆኑ፥ አእምሯችን፥ የምናስባቸው ነገሮችና ጠቃሚ ነው ብለን የምናስበው ሁሉ እግዚአብሔር ከሚፈልገው ነገር ጋር ሲጣጣሙ፥ ሌሎች የሚያሳስቡን ነገሮች ሁሉ ግልጽ ይሆኑልናል። ለእግዚአብሔር ክብር የሚኖር ሰው በእግዚአብሔር እየተመራ በሚያልፍበት ሁኔታ ውስጥ ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ መልካም፥ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም መሆኑን ይገነዘባል።

15ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ብዙ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የሚቸገሩባቸውን አንዳንድ ነገሮች ዘርዝር። ለ) ሰውነታችንን መሥዋዕት ማድረግ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የሚረዳን እንዴት ነው? ሐ) ለእግዚአብሔር ራስን ሙሉ በሙሉ አሳልፎ መስጠት የትዳር ጓደኛን መምረጥ የመሳሰሉትን ነገሮች በሕይወታችን ቀላል የሚያደርገው እንዴት ነው?

2. አማኞች እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያገለግላሉ (ሮሜ 12፡3–8)

ዛሬ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ከሚያጋጥማት ችግሮች አንዱ እግዚአብሔር በቀዳሚነት በእኛ ግለሳባዊ ሁኔታ ደስ ይሰኛል የሚል የራስ ወዳድነት ክርስትና ነው። በግል ደኅንነታችን፥ በጸጋ ስጦታዎቻችን፥ በአምልኮ ባርኮታችን፥ ወዘተ... ላይ እናተኩራለን። ጳውሎስ ግን ክርስቲያን በዋናነት ሊያተኩር የሚገባው በግል ጉዳይ ላይ ሳይሆን የክርስቶስ አካል በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ላይ ሊሆን እንደሚገባ አብራርቷል። ጳውሎስ የሚያስተምራቸው አብዛኞቹ ተግባራዊ ነገሮች እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ እንዴት አብረን ልንኖር እንደሚገባን የሚያሳዩ ናቸው። በዚህ ክፍል ጳውሎስ እያንዳንዱ ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለማገልገል ሊያስታውሳቸው የሚገባቸውን አራት መሠረታዊ ነገሮች ጠቃቅሷል።

ሀ. ከሌሎች ጋር መዛመድ ማለት የራሳችንን ትክክለኛ ማንነት መገንዘብ ማለት ነው። ከዓለም ከምንማራቸው ነገሮች አንዱ ራሳችንን ከሌሎች ጋር የማወዳደር ዝንባሌ ነው። ስለሆነም ራሳችንን እንደተሻልን (የበለጠ የተማርን፥ የበለጠ ስጦታ ያለን) አድርገን እንመለከታለን። የዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ከእግዚአብሔር ሳይሆን ዓለማዊ ነው። ጳውሎስ ማንነታችንንና ግንኙነታችንን እግዚአብሔር በሚያየን መንገድ መገንዘብ እንዳለብን ገልጾአል። በአንድ በኩል ይህ ማለት እግዚአብሔር ምን ያህል እንደወደደን፥ ለእርሱ ምን ያህል አስፈላጊዎች እንደሆንን፥ ከእርሱ ስጦታዎችን እንዳገኘንና ለእርሱ እንደምንጠቅም መገንዘብ ማለት ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክርስቲያኖች፥ በተለይም ያልተማሩ ወይም ሴቶች፥ «ለምንም የማልረባ ስለሆንሁ እዚያ ቁጭ ብዬ ልስማ። ለእግዚአብሔር እንደ እገሌና እገሌ አስፈላጊ አይደለሁም» ሊሉ አይችሉም። እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ለሁላችንም እንዲሞት ልጁን ለላከው እግዚአብሔር ስድብ ነው። ሁላችንም ለእግዚአብሔር አስፈላጊዎች ነን። ይህ እግዚአብሔር የሰጠንን ስጦታዎችና ችሎታዎች አውቀን ለሌሎች ጥቅም መገልገል እንዳለብን ያሳያል። በሌላ በኩል፥ እኛ ከማንም እንደማንሻል መገንዘብ አለብን። የምንኩራራበት ምንም ምክንያት የለንም። ሰዎች ሁሉ፥ ያልተማሩና የተማሩ፥ ወንዶችና ሴቶች፥ ወጣቶችና አረጋውያን ሁሉ በመስቀሉ ሥር እኩል ናቸው። ሁላችንም በጸጋ የዳንን ኃጢአተኞች ነን።

ለ. እያንዳንዱ ክርስቲያን የአንድ አካል ክፍል መሆኑን መገንዘብ ይኖርበታል። ሁላችንም የቤተ ክርስቲያን አካሎች ነን። ዛሬ እንደ ግለሰብ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተው የሚያመልኩ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ተመልሰው ተግባራቸውን ያከናውናሉ። የቤተ ክርስቲያን አካል ሆነው ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት ምንም አስተዋጽኦ አያበረክቱም። ይህ

ጳውሎስ ከሚያስተምረው አሳብ ተቃራኒ ነው። ጳውሎስ እያንዳንዱ ግለሰብ የቤተ ክርስቲያን አካል እንደሆነ ያስተምራል። እያንዳንዳችን መንፈስ ቅዱስ በሰጠን ስጦታ ወይም ስጦታዎች አማካኝነት ለአካሉ የምናበረክታቸው ድርሻዎች አሉን። ቤተ ክርስቲያን የሁሉም ክርስቲያን ነች። ሁሉም ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያን ሊሆን ይገባል። (መሪዎች ቤተ ክርስቲያንን ስለምናስተዳድር ወይም ስለምንመራ ንብረታችን ናት ብለን እንዳናስብ መጠንቀቅ አለብን። የቤተ ክርስቲያን ዋነኛው ባለቤት እግዚአብሔር ሲሆን፥ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ሁሉ እኩል ድምፅ አላቸው።)

ሐ. አንዳችን ሌላውን እናገለግል ዘንድ እግዚአብሔር ለአማኞች ሁሉ የተለያዩ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ሰጥቷል። ሁሉም ስጦታዎች ያሉት ክርስቲያን የለም። ነገር ግን እያንዳንዱ ክርስቲያን ቢያንስ አንድ ስጦታ ተሰጥቶታል። መንፈሳዊ ስጦታ በቀዳሚነት ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት የሚውል ችሎታ ነው። በዛሬው ዓለም ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ስናስብ አእምሯችን በፍጥነት የሚወነጨፈው እንደ ልሳን፥ ፈውስ፥ ትንቢት፥ ወዘተ... ወዳሉት አስደናቂ ስጦታዎች ነው። ብዙውን ጊዜ እነዚህን መንፈሳዊ ስጦታዎች የምንፈልገው ለራስ ወዳድነት ዓላማ፥ ማለትም ሰዎች በመንፈሳዊነታችን እንዲደነቁ ለማድረግ ነው። ጳውሎስ ግን ብዙ ዓይነት ስጦታዎችና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማገልገል የሚቻልባቸው ብዙ መንገዶች እንዳሉ ይነግረናል። ሁሉም አስፈላጊዎች ናቸው።

መ. ዋናው ነገር እግዚአብሔር ለአንድ ክርስቲያን መንፈሳዊ ስጦታ መስጠቱ ወይም ግለሰቡ ስጦታውን መጠቀሙ ብቻ አይደለም። ጳውሎስ ስጦታውን ከምንጠቀምበት ሁኔታ በስተጀርባ ያለው አመለካከታችን አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳል። ስለሆነም፥ ትንቢትን በምንናገርበት ጊዜ ከመንፈሳዊ የእምነት ደረጃችን ጋር በተስተካከለ ሁኔታ መሆን አለበት። በችግር ላይ ላሉት በምንሰጥበት ጊዜ በልግስና ልናደርገው ይገባል። አመራራችንም በትጋት የሚካኬድ ሊሆን ይገባዋል።

| |
|---|
| 16ኛ ጥያቄ፡- ሀ) መንፈሳዊ ስጦታዎችህ ምንድን ናቸው? ለ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ እንዴት እየተጠቀምህባቸው ነው? ሐ) አንድ መንፈሳዊ ስጦታ ጥቀስና ይህንኑ ስጦታ እንዴት በተሳሳተ አመለካከት መጠቀም እንደሚቻል ግለጽ። በትክክለኛ አመለካከት መጠቀም የሚቻለውስ እንዴት ነው? እግዚአብሔር ለእርሱ በምንሠራው ሥራ ላይ ብቻ ሳይሆን በሥራው ላይ በነበረን አመለካከት ላይም የሚገደው ለምን ይመስልሃል? መ) ብዙ ምእመናን በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደማገልገል ከቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን የሚዟዟሩት ለምን ይመስልሃል? ሠ) በቤተ ክርስቲያንህ ሰዎች መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን ተግባራዊ ሊያደርጉ የሚችሉባቸውን የአገልግሎት ዓይነቶች ዘርዝር። ሰዎች የበለጠ በአገልግሎት ውስጥ እንዲሳተፉ ልታደርግ የምትችለው እንዴት ነው? ረ) በቤተ ክርስቲያንህ ከሌሎች አማኞች ጋር እኩል አይደለንም የሚል ስሜት ያላቸው ሰዎች አሉ? እነዚህ እነማን ናቸው? የእኩልነት ስሜት እንዲሰማቸው ምን ልታደርግ ትችላለህ? |

3. አማኞች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር የፍቅር ግንኙነት ያደርጋሉ (ሮሜ 12፡9-13)

በአማኞች ማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በራስ ወዳድነት አንድን ነገር ከሌላው ለመውሰድ የሚፈልጉ ሳይሆኑ፥ እርስ በርሳቸው የሚዋደዱ መሆን አለባቸው። ፍቅር ከራሳችን በላይ ሌላውን ሰው እንድንረዳ ነው የሚፈልገው። እያንዳንዱ ክርስቲያንና ባጠቃላይም የአማኞች አካል ክፋትን በሚጠሉና በጎነትን በሚያስፋፉ፥ ትሑት በሆኑና ከራሳቸው በላይ ሌሎችን ለመጥቀም በሚፈልጉ፥ ወዘተ... ወገኖች የተገነባ እንዲሆን ይሻል።

17ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ጳውሎስ በክርስቲያኖች መካከል ስለሚኖረው ግንኙነት የገለጸውን ሃሳብ ከቤተ ክርስቲያንህ ሁኔታ ጋር አነጻጽር። የቤተ ክርስቲያንህ ጠንካራና ደካማ ጎኖች የትኞቹ ናቸው? ለ)ቤተ ክርስቲያንህ ጳውሎስ በዚህ ክፍል የገለጸውን ባሕርይ እንድታንጸባርቅ ለመርዳት ምን ልታደርግ ትችላለህ?

4. አማኞች ከክርስቲያኖችም ሆነ ክርስቲያኖች ካልሆኑ ሰዎች ጋር ሰላማዊ ግንኙነት ያደርጋሉ (ሮሜ 12፡14-21)።

ከሰዎች ጋር በሰላም ለመኖር ምንም ያህል ጥረት ብናደርግም፥ በግንኙነቶች ውስጥ ችግሮች ይከሰታሉ። ከአማኞችም ሆነ አማኞች ካልሆኑ ሰዎችም ጋር የግንኙነት ችግሮች ይከሰታሉ። ጳውሎስ ደኅንነታችንን እግዚአብሔርን በሚያስከብር መልኩ ለመኖር ከፈለግን፥ ከማንስማማቸው ሰዎች ጋር ስለሚኖረን አመለካከት መጠንቀቅ እንዳለብን። ግንኙነታችንን የሚመለከቱ አያሌ ትእዛዛትን ሰጥቷል።

ሀ. ከሌሎች ጋር በሰላም ለመኖር ፈልጉ።

ለ. በኩራት ሌሎችን ላለመናቃችሁ እርግጠኞች ሁኑ። በሮም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩ ብዙ አማኞች ባሮች እንደነበሩ አትዘንጋ። ነገር ግን ጥቂት ባሪያ አሳዳሪዎችም ነበሩ። ጥቂት ምእመናን የተማሩ ሲሆኑ፥ አብዛኞቹ ግን ያልተማሩ ነበሩ። ይህ ልዩነታቸውም አንዳቸው ከሌላቸው እንደሚበልጡ እንዲያስቡ ሊገፋፋቸው ይችላል። ጳውሎስ አንዱ ሰው ለእግዚአብሔር ከሌላው የተሻለ እንዳልሆነ ገልጾአል። ስለሆነም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኩራት፥ ጎሰኝነት ወይም ልማድ ሊኖሩ አይገባቸውም።

ሐ. ሰዎች በሚቃወሙህ ጊዜ እነርሱን መጥላትና መበቀል እንደሌለብህ እርግጠኛ ሁን። ነገር ግን በጎነታቸውን በመሻት፥ እግዚአብሔር በሕይወታቸው እንዲሠራ በመጠየቅ ባርካቸው። ቅጣታቸውን ለእግዚአብሔር ተወው። የጥላቻንና የክፋትን ዑደት ማስወገድ የሚቻልበት ብቸኛው መንገድ መልካምን ለማድረግ በመወሰን ነው። አንድን ሰው ብንበቀል ራሳችንን፥ ቤተሰባችንን፥ ቤተ ክርስቲያናችንን፥ ማኅበረሰባችንንና አገራችንን የሚያጠፋ የክፋት ዑደት እንቀጥላለን።

18ኛ ጥያቄ፡- ብዙ ቤተ ክርስቲያኖቻችን በመከፋፈል የታወቁ ናቸው። ሀ) ይህ የሆነው ለምንድን ነው? ለ) በቤተ ክርስቲያን ወይም በቤተ እምነትህ ዐቢይ ክፍፍል ከፈጠሩት ነገሮች አንዱን ነቅሰህ አውጣ። ጳውሎስ ባስተማረው መሠረት፥ አለመግባባቶቹን ለማቆም ክርስቲያኖች እንዴት መመላለስ ይኖርባቸዋል?

5. አማኞች ለሰብአዊ መንግሥታቸው ይጸልያሉ፥ ይታዘዛሉ (ሮሜ 13፡1-7)

እንደ ወንጌላዊያን ክርስቲያኖች ከመንግሥትና ከመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር የቀረበ ግንኙነት የለንም። በቀደመው ሥርዓት የስደት ምንጮች ሆነው

አሠቃይተውናል። አሁን ድምፅ የመስጠት ዕድል ሲሰጠን ደግሞ ብዙ አማኞች ድምፅ ለመስጠት ፈቃደኞች አይደሉም። ለአገልግሎት ሲጠይቁንም አዎንታዊ ምላሽ አንሰጥም። ከመንግሥት በመራቃችን ደስ የምንሰኝ ይመስላል።

ጳውሎስ ግን ከመንግሥት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ሊኖረን እንደሚገባ ይመክራል። ጳውሎስ ከመንግሥት ባለሥልጣናት ብዙ ጊዜ ስደት እንደደረሰበት አስታውስ። በሮሜ መንግሥት ለአራት ዓመታት ታስሮ ወደ ሚቆይበት የወኅኒ ቤት ይገባ ነበር። ጳውሎስ የሮሜን መልእክት ከጻፈ ከአሥር ዓመታት ያህል በኋላ የሮም ንጉሥ የሞት ቅጣት ፈርዶበታል። ይህም ሆኖ፥ ጳውሎስ ክርስቲያኖች ለመንግሥት መልካም አመለካከት እንዲኖራቸው አስተምሯል። ለምን? ምክንያቱም ኮሚኒስትም ይሁን እንደ የኔሮ ዓይነት ክፉ መንግሥት ይሁን ወይም ጥሩ መንግሥት የትኛውም መንግሥት በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ነው። ስለሆነም መንግሥትን መቃወም ማለት የእግዚአብሔርን ፈቃድ መቃወም ማለት ነው። እንግዲህ፥ ክርስቲያኖች ከመንግሥት ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል? ጳውሎስ አያሌ ነገሮችን ጠቃቅሷል።

ሀ. ለመንግሥት ባለሥልጣናት መገዛት አለብን። እነዚህ ባለሥልጣናት መጽሐፍ ቅዱስን በቀጥታ እስካልተቃወሙ ድረስ (የሐዋ. 5፡27-29ን አንብብ።)፥ ሕግጋቱን ባንወዳቸውም እንኳ መፈጸም አለብን። መንግሥት እግዚአብሔር ሕግንና ሥርዓትን ለማስከበር፥ የማኅበረሰቡ እንቅስቃሴ እንዳይደናቀፍ ለማገዝና የክፋትን ስርጭት ለመቋቋም ሲል የመሠረተው ተቋም ነው። ለመንግሥት አለመታዘዝ ማኅበረሰቡን ወደ ሁከት፥ ውድመትና ክፋት ይመራል።

ለ. ቀረጥ መክፈል አለብን። ብዙ ክርስቲያን ነጋዴዎች ለመንግሥት ቀረጥ አይከፍሉም። ጳውሎስ ግን ይህ ስሕተት እንደሆነ ያስረዳል። ሁላችንም መንግሥት የሚያሠራቸውን መንገዶች፥ ትምህርት ቤቶች፥ ሆስፒታሎች፥ ወዘተ... ስለምንጠቀም፥ ለእነዚህ ወጭዎች መሸፈኛ የሚያግዝ ቀረጥ መክፈል አለብን።

ሐ. ክርስቲያኖች መሪዎቻቸውን ማክበር አለባቸው። ጳውሎስ የሚናገረው ስለ ክርስቲያን የመንግሥት መሪዎች ወይም ስለ ጥሩ መሪዎች አይደለም። እርሱ የሚናገረው ብዙውን ጊዜ የራስ ወዳድነት አመለካከት ስላላቸው ክርስቲያን ያልሆኑ መሪዎች ነው። ጳውሎስ ሰዎቹ ጥሩ ናቸው ብለን በማሰባችን ሳይሆን እግዚአብሔር ለመሪነት እንዳስነሣቸው በመገንዘባችን ሁልጊዜም ልናከብራቸው እንደሚገባን ያብራራል።

| |
|---|
| 19ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ጳውሎስ ለመንግሥት መሪዎች ያለውን አመለካከት ከእኛ አመለካከት ጋር አነጻጽር። ለ) በ1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡1-2 ለባለሥልጣናት እንድንጸልይ ተነግሮናል። ቤተ ክርስቲያንህ ይህንን የምታደርገውና ክርስቲያኖች በቀዳሚነት ለመንግሥት ባለሥልጣናት እንዲጸልዩ የምታበረታታው እንዴት ነው? ሐ) በቀበሌህ፥ በወረዳህ፥ በክልልህና በፌዴራል ደረጃ ሥልጣን ላይ ያሉትን መሪዎች ስም ዘርዝር። አሁን ጊዜ ወስደህ ለእነዚህ ሰዎች ጸልይላቸው። |

6. የአማኙ ሕይወት በቅርብ በሚሆነው የኢየሱስ መመለስ ብርሃን ሲታይ (ሮሜ 13፡8–13)

ደኅንነት በምናገኝበት ጊዜ የሕይወታችን ክፍሎች በሙሉ መለወጥ አለባቸው። ጳውሎስ የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናችን ምክንያት የሚለወጡትን ነገሮች ዘርዝሯል።

ሀ. ክርስቲያኖች የተበደሩትን ገንዘብ ሁሉ ሊከፍሉና በተቻለ መጠን ከብድር የጸዳ ሕይወት መምራት አለባቸው። ከሰው ገንዘብም ሆነ ሌላ ነገር ተበድሮ ለመክፈል እየቻሉ ቸል ማለቱ የክርስቲያናዊ ፍቅር ምልክት አይደለም። ይህ ዓለም በሰዎች ትከሻ ላይ ሆኖ ለመጠቀም የምትከተለው አሠራር ነው።

ለ. ከሕግጋት ዝርዝሮች ይልቅ በአመለካከታችን ላይ ልናተኩር ይገባል። አመለካከቶቻችንም አጠቃላይ ግንኙነቶቻችንን፥ ማለትም ባልንጀራን መውደድ (ክርስቲያኖችንም ሆነ ክርስቲያኖች ያልሆኑትን)፥ ለራሳችን የምናደርገውን ያህልና ሌሎችም እንዲያደርጉልን የምንፈልገውን ጥንቃቄ ለእነዚህ ወገኖች ማድረግ፥ ወዘተ... ያጠቃልላሉ።

ሐ. ክርስቲያኖች ክርስቶስ ዛሬ እንደሚመለስ እያሰቡ ይኖራሉ። ስለሆነም፥ ሕይወታችን ክርስቶስ ሊያጠፋው የመጣበትን የዓለምን ክፋት ከሚያንጸባርቁ ነገሮች ሁሉ ተለይቶ በንጽሕና ሊያዝ ይገባል። ጳውሎስ ክርስቶስን እንድንለብስ አዞናል። ጳውሎስ ይህን ሲል በአመለካከታችንም ሆነ በተግባራችን ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ክብር እንድናደርጋቸው የሚፈልገውን ነገሮች ብቻ እንድናደርግ መጠየቁ ነው። አሁንም ጳውሎስ የምናስባቸውን ነገሮች እንድንቆጣጠር ማሳሰቡን አስተውል።

20ኛ ጥያቄ ፡– ሀ) ጳውሎስ እንደ አማኝ ስለመመላለስ ባስተማረው መሠረት፥ አዳዲስ ክርስቲያኖችን ማስተማር የሚያስፈልገው ስለ ምንድን ነው? ለ) ቤተ ክርስቲያንህ ለአዳዲስ አማኞች የምታስተምረው ምንድን ነው? ይህንን ጳውሎስ ካስተማረው ጋር አነጻጽር። ጳውሎስ ለክርስቲያን ሕይወት አስፈላጊ ነው ብሎ ያስተማረውን ሃሳብ ለመከተል ይቻል ዘንድ የቤተ ክርስቲያንህን ትምህርት ለመለወጥ ምን ሊደረግ ይገባል?

## ሦስተኛ ቀን ሮሜ 14–16

ሰላማዊት በአጥባቂ ቤተሰብ ውስጥ ያደገች ክርስቲያን ነበረች። ጥሩ ክርስቲያኖች ጌጣጌጥ እንደማይጠቀሙ፥ ከንፈራቸውንም ሆነ ጥፍራቸውን ቀለም እንደማይቀቡ፥ ፊልም ቤት እንደማይሄዱ፥ ፋሽን ልብስ እንደማይለብሱ፥ በቤተ ክርስቲያን ስካርፎችን እንደማይለብሱ፥ ወዘተ... ገና በትንሽነቷ ተምራለች። ፍቅርተ ክርስቲያን ባልሆኑ ሀብታም ቤተሰብ ውስጥ ያደገች ሴት ነበረች። ሁልጊዜም ሕይወቷ በፋሽን ልብሶች፥ ጌጣጌጦች፥ ፊልሞች፥ የፀጉር ስታይሎች፥ ወዘተ... የታጀበ ነበር። ፍቅርተ ክርስቲያን ስትሆን፥ እነዚህ ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ስላልተከለከሉ መተው አለብኝ ብላ አላሰበችም። አንድ ቀን የአንድ ቤተ ክርስቲያን መእመናን የነበሩት ሰላማዊትና ፍቅርተ መነጋገር ጀመሩ። በዚህ ጊዜ ሰላማዊት ለፍቅርተ፥ «ከአለባበስሽ እንደምረዳው፥ አንቺ ጥሩ ክርስቲያን አይደለሽም አለቻት።

ይህ ወደ ትልቅ ፀብ በመለወጡ፥ ሰላማዊትና ፍቅርተ ከመነጋገርና በጸሎት ከመተጋገዝ ታቀቡ። ይባስ ብለውም በጓደኞቻቸው መካከል አንዳቸው ስለሌላቸው መጥፎ ወሬዎችን ያዛምቱ ጀመር።

| |
|---|
| 21ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ጥሩ ክርስቲያን ሊያደርግ በሚችላቸውና በማይችላቸው ነገሮች ላይ የሚከሰተው የአሳብ ልዩነት ክፍፍልን ሲፈጥር የተመለከትከው እንዴት ነው? ለ) ጳውሎስ በሮሜ 14፡1–15፡13 ባስተማረው አሳብ መሠረት፥ ለሰላማዊትና ፍቅርተ ምን ምክር ትሰጣለህ? ሐ) ክርስቲያኖች በአሳብ የሚለያዩባቸውን ሌሎች ልምምዶች ዘርዝር። |

## 7. ክርስቲያኖች የተለየ አመለካከት ያላቸውን ክርስቲያኖች የሚያስቀይም ነገር ባለማድረግ ፍቅራቸውን ያሳያሉ (ሮሜ 13፡14–15፡13)

ሁልጊዜም ክርስቲያኖች የትኞቹን ልምምዶች ሊያደርጉ እንደሚገባቸው ወይም እንደማይገባቸው በአሳብ መለያየታቸው የማይቀር ነው። በተለይም ልምምዶቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ካልተብራሩ። መጽሐፍ ቅዱስ ዝሙት ኃጢአት እንደሆነ በግልጽ ስለሚያስተምር ብዙ ክርስቲያኖች በዚህ ጉዳይ ላይ አይከራከሩም። ነገር ግን ሌሎች ሰላማዊትና ፍቅርተ ያነሡዋቸው ዓይነት ጉዳዮች ቤተ ክርስቲያንን እስከ መከፋፈል ድረስ ይደርሳሉ። ለምሳሌ፥ አንዳንድ ክርስቲያኖች ምንም ዓይነት የአልኮል መጠጥ መጠጣት የለብንም ሲሉ፥ ሌሎች ደግሞ አልኮል መጠጣት ኃጢአት እንዳልሆነ ያስረዳሉ። በክርስቲያኖች መካከል መከፋፈልን የሚፈጥሩትን ጉዳዮች እንዴት ልናስተናግዳቸው ይገባል?

በሮሜ 14፡1–15፡13፥ ጳውሎስ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያልጠቀሳቸው ነገሮች የአሳብ ልዩነቶችን በሚያስከትሉበት ጊዜ ክርስቲያኖች እንዴት አንድነታችንን ጠብቀን ልናቆይ እንደምንችል አብራርቷል። በሮምና ከፍልስጥኤም ውጭ ባሉት አብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አይሁዶችና አሕዛብ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያመልኩ ነበር። ሁልጊዜም በሁለቱ ወገኖች መካከል የአሳብ ልዩነቶችን የሚያስከትሉ ባሕላዊ ልምዶች ነበሩ። ከእነዚህ ጉዳዮች አንዱ ክርስቲያኖች በገቢያ ውስጥ የሚሸጥ ሥጋ መብላት ይችላሉ ወይ? የሚል ነበር። በገበያ ውስጥ ከሚሸጥ ሥጋ አብዛኛው በሚታረድበት ጊዜ ለጣዖት የተሠዋና ከፊሉ ለጣዖት አምልኮ ያገለገለ ነበር። የተቀረው ገበያ ውስጥ ይሸጣል። የአይሁድ ክርስቲያኖችና አንዳንድ አሕዛብ ክርስቲያኖች ይህን ለአረማዊ ጣዖት የተሠዋ ሥጋ መብላት ትክክል አይደለም የሚል አሳብ አቀረቡ። ለእነርሱ ሥጋውን መብላት በጣዖት አምልኮ እንደ መካፈል ቆጠሩት። ብዙ ክርስቲያኖች ደግሞ ሥጋውን መብላት ምንም ስሕተት መስሎ አልታያቸውም። «ሥጋ ሥጋ ነው። ጣዖታትን በፊታዳችን እስካላመለክን ድረስ ሥጋውን ልንበላ እንችላለን። ሥጋውን በላን ማለት ጣዖት አመለክን ማለት አይደለም» ሲሉ አስተማሩ። ይህ በገበያ ላይ የሚሸጠውን ሥጋ ስለመብላት የቀረበው ሁለት ዓይነት አመለካከት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክፍፍልን አስከተለ። (ይህ በደቡብ ኢትዮጵያ የመስቀል በዓል ምግብ ስለመብላት ከሚነሣው ክርክር ጋር ተመሳሳይ ነው።) ቅዳሜ ወይስ እሑድ ልናመልክ ይገባል? የሚሉ ዓይነት ሌሎች ጉዳዮችም ክፍፍል አስከትለዋል።

ስለሆነም፥ ጳውሎስ የሮሜ ክርስቲያኖች ችግሩን ማስገናገድ እንደሚገባቸው ለሮሜ ክርስቲያኖች ጽፎላቸዋል። (ጳውሎስ ቀደም ሲል ለጣዖት የተሠዋን ምግብ ስለመብላት በ1ኛ ቆሮንቶስ 8–10 ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አብራርቷል። በሮም የተከሰተው ችግር ደግሞ ከሥጋ በተጨማሪ የአምልኮ ቀንንም ያካትት ነበር።)

ጳውሎስ ለሮሚ ክርስቲያኖች ያስተማራቸውን መርሆች መረዳት ጠቃሚ ነው። ሁልጊዜም ጥሩ ክርስቲያኖች ሊያደርጉ በሚገባቸውና በማይገባቸው ጉዳዮች ላይ የአመለካከት ልዩነቶች መከሰታቸው የማይቀር ነው። ጳውሎስ የጠቀሳቸውን መርሆች ካላወቅን በቤተ ክርስቲያናችን ወይም በክርስቲያኖች መካከል ክፍፍል በመፍጠር፥ ከሌሎች ክርስቲያኖች የተሻልን ነን የሚል የትዕቢት አመለካከት በመያዝ፥ ወይም የጥሩ ክርስቲያንነት ማረጋገጫዎች ናቸው የምንላቸውን የ«አድርጉ/አታድርጉ» ትእዛዛት በመዘርዘር ችግሮችን ልንጋብዝ እንችላለን። ሁልጊዜም መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊነት የልብ ጉዳይ እንጂ የውጫዊ ተግባራችን መግለጫ አለመሆኑን ያስረዳል። በቀዳሚነት ክርስቲያንነታችንን የምናሳየው በምናደርገው ወይም በማናደርጋቸው ነገሮች ሳይሆን፥ በሮሜ 12–13 እንደተገለጸው ከሌሎች ሰዎች ጋር በምንዛመድበት ሁኔታና በልባችን ዝንባሌዎች ነው።

ከዚህ በታች ጳውሎስ ያስተማራቸው ስምንት ዐበይት እውነቶች ቀርበዋል።

ሀ. ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ባላስተማረው ጉዳይ ላይ በአሳብ በሚለያዩበት ጊዜ፥ ሁልጊዜም «ደካማ» እና «ጠንካራ» ክርስቲያኖች ይኖራሉ። ደካማና ጠንካራ የሚሉት ቃላት አንዱ ከሌላኛው የበለጠ መንፈሳዊ መሆኑን አያሳዩም። ጳውሎስ እንደሚለው፥ «ደካማ» ክርስቲያኖች መልካም ክርስቲያኖች የተወሰኑ ነገሮችን ማድረግ የለባቸውም የሚል አቋም ሲይዙ፥ «ጠንካሮች» ክርስቲያኖች እነዚህን ነገሮች ለማድረግ እንደተፈቀደላቸው ያምናሉ።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ በማያስተምራቸው ጉዳዮች ላይ የአሳብ ልዩነት በሚከሰትበት ጊዜ፥ ሁለቱም ወገኖች ከእነርሱ በአሳብ የተለየውን ወገን ከመተቸትና መንፈሳዊ አይደለም ከማለት መቆጠብ አለባቸው። መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ባላስተማራቸው ጉዳዮች ላይ ክርስቲያኖች ነጻነት አላቸው። ያለማድረግ (አትክልት ብቻ የመመገብ) ወይም የማድረግ (ሥጋ የመብላት) ነጻነት አለን።

ሐ. ግልጽ ባልሆኑት ጉዳዮች ላይ ተመሥርተን የአንድን ሰው መንፈሳዊ ሁኔታ ከመመዘን የምንጠነቀቅባቸው ሁለት ምክንያቶች አሉ። ሀ) የሰውን ልብና አመለካከት ለመለካት የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ስለሆነም፥ እውነተኛ መንፈሳዊነት የሚገኝበት ልቡን ስለማናውቅ፥ በአከራካሪ ጉዳዮች ላይ ተመሥርተን ግለሰቡን ልንጠራጠር አይገባም። ለ) የኋላ ኋላ፥ ሁሉም ክርስቲያን የእግዚአብሔር ባሪያ ስለሆነ ተጠያቂነቱ ለእርሱ ነው። አንድ አማኝ በእንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ ላይ አቋም እንዲይዝ መምራቱ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ወይም የሌሎች ክርስቲያኖች ሳይሆን የእግዚአብሔር ኃላፊነት ነው። ፈራጅ ክርስቶስ እንጂ እኛ አይደለንም።

መ. ክርስቲያኖች በአንድ ልምምድ ላይ በሃሳብ በሚለያዩበት ጊዜ፥ በሁለቱም ወገን የሚገኙ ሰዎች በሚያደርጉት ነገር እግዚአብሔርን እያከበሩ ለመሆናቸው እርግጠኞች መሆን አለባቸው። ቢራ መጠጣት ትክክል ነው ብለው ቢያስቡና ቢራ የሚጠጡትን ክርስቲያኖች ምሳሌነት መከተል ቢጀምሩ፥ ዳሩ ግን ልባቸው ውስጥ ጥርጣሬ ካለ ኃጢአትን ሠርተዋል ማለት ነው። ኃጢአትን የሠሩት ቢራ በመጠጣታቸው ሳይሆን ትክክል ስላልሆነውና ስለሆነው ጉዳይ አቋም ባለመውሰዳቸው ነው። ያለ እምነት የምናደርገው ነገር ሁሉ ኃጢአት ነው።

ሠ. የክርስቲያኖች ሁሉ ትልቁ ፍላጎት «እግዚአብሔርን ማስደሰት» ሊሆን ይገባል። ከእሑድ ቀጥሎ ባለው ቀን አምልኮ ለማካሄድ፥ የተወሰነ ምግብ (ለምሳሌ የእስላም ሥጋ፥ የርኩስ እንስሳት ሥጋ) ለመብላት፥ ወይም የተወሰነ ልብስ ለመልበስ ብንፈልግ፥ «በማደርገው ነገር ለእኔ ሲል የሞተውን ክርስቶስን እያስደሰትሁት ነው?» ብለን ልንጠይቅ ይገባል።

ረ. ክርስቲያኖች ሁሉ ለምናካሂዳቸው ልምምዶችና የእኛን ዓይነት እምነት ለማይከተሉ ክርስቲያኖች ለምንይዛቸው አመለካከቶች ተጠያቂዎች እንደምንሆን መገንዘብ አለብን። ሁላችንም በእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር ፊት ስለምንቆም፥ ለተግባራችንና ለአስተሳሰባችን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል።

ሰ. ለክርስቲያኖች አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች አንዱ ፍቅርና ለሌሎች መስጠት ስለሆነ፥ ተግባራችን ሌሎች ክርስቲያኖችን በመጉዳት ወደ ኃጢአት እየመራቸው አለመሆኑን ማረጋገጥ አለብን። በፍቅር መኖር፥ በእምነት ለማደግ መደጋገፍና አንድነትን መፍጠር ከነጻነቶቻችን፥ ከግል መብቶቻችንና እምነቶቻችን በላይ ጠቃሚዎች ናቸው። ቀዳሚው ምስክርነታችንና ክርስቶስን የምናስከብርበት መንገድ የሚገለጸው የግል እምነቶቻችንና መብቶቻችንን በማሳየት ሳይሆን፥ በፍቅራችንና በአንድነታችን ነው።

ሸ. ከየትኛውም ጎሳ ብንመጣ (ለምሳሌ አይሁዳዊ፥ አሕዛብ፥ አማራ፥ ኦሮሞ) ወይም በተለያዩ ልምምዶች ላይ የትኛውንም አቋም ብንይዝ፥ ክርስቶስ ሁለቱንም አቋማት ለሚይዙ ክርስቲያኖች ስለ ሞተ፥ አንድነታችንን ልናጠብቅ ይገባል። የአይሁድ ክርስቲያኖች እነርሱ የማይቀበሏቸውን ነገሮች ስለሚያደርጉ ከአሕዛብ ክርስቲያኖች መለየት አልነበረባቸውም።

> 22ኛ ጥያቄ፦ ሀ) በቅርቡ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የተከሰተውን ዐቢይ ክፍፍል ግለጽ። ለ) እነዚህን እውነቶች ተግባራዊ ማድረግ ያንን ክፍፍል በመቀነስ አንድነትን ሊያመጣ የሚችለው እንዴት ነው? ሐ) የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ወይም ክርስቲያኖች የሚከራከሩባቸውን ልምምዶች ዘርዝር። ጳውሎስ ባስተማራቸው በእነዚህ እውነቶች መሠረት ክርስቲያኖች ምን ዓይነት ምላሽ ሊሰጡ ይገባል? በእነዚህ ትምህርቶች ምክንያት በሰዎች እምነቶችና ተግባራት ላይ ምን ምን ለውጦች ይከሰታሉ?

## ማጠቃለያ (ሮሜ 15፡14-16፡27)

### 1. የጳውሎስ የግል ምስክርነትና ዕቅዶች (ሮሜ 15፡14-33)

23ኛ ጥያቄ፦ ሮሜ 15፡14–33 አንብብ። ሀ) ጳውሎስ ስለ ራሱ የሰጠው መግለጫ ለሮሜ ሰዎች መልእክት የጻፈበትን ሁኔታ የሚያስረዳው እንዴት ነው? ለ) ጳውሎስ ስለ ወደፊት አገልግሎቱ ምን አለ?

ሰዎችንና አሳባቸውን በተሳሳተ መንገድ መረዳቱ ቀላል ነው። ብዙዎቻችን ከሰዎች ቃላት በስተጀርባ የተደበቁትን ፍላጎቶችን እየፈለግን በተሳሳተ መንገድ እንተረጉማለን። ከዚህም የተነሣ በማያስፈልግ መቀያየም ውስጥ እንገባለን። ጳውሎስ በአካል የማያውቁት የሮሜ ምእመናን ትምህርቱን በተሳሳተ መንገድ እንዳይረዱት ሰግቶ ነበር። ስለሆነም፥ ጳውሎስ በግልጽና ራሱን ዝቅ አድርጎ አሳቡን ይነግራቸዋል።

ሀ. ጳውሎስ የሮሜን ክርስቲያኖች ደኅንነት ማግኘትና በመንፈሳዊ ባሕርያት የታጀበ ሕይወት መምራታቸውን እንደማይጠራጠር ገልጾአል። መልእክቱን የጻፈላቸው እንደ «የአሕዛብ ሐዋርያነቱ» ኃላፊነቱን ለመወጣት ነበር። ጳውሎስ አሕዛብ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ስለማግኘታቸው ጉዳይ በግልጽ የጻፈው አሳብ የአይሁድ ክርስቲያኖችን ሊያስቀይም እንደሚችል በመገንዘቡ፥ ያስተማረውን ነገር በግልጽ ሊነግራቸው ፈለገ። እግዚአብሔር ለአሕዛብ መልካሙን የምሥራች የማካፈልን ልዩ አገልግሎት ሰጥቶታል። ጳውሎስም የአሕዛብ አማኞችን እንደ ቅዱስ መሥዋዕት በማቅረብ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ፈለገ።

ለ. የጳውሎስ ሸክም በቀዳሚነት ለአሕዛብ የክርስቶስን ወንጌል መስበክ ነበር። በቀዳሚነት ለማገልገል የፈለገው ደግሞ ከዚህ በፊት ወንጌል ባልተሰበከባቸው አካባቢዎች ነበር። ለዚህም ነበር ጳውሎስ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ወደ ሮም ለአገልግሎት ያልሄደው። እግዚአብሔር ጳውሎስ ወንጌሉን ከኢየሩሳሌም ወደ ኤልሪቆም (በሰሜን መቄዶንያ ውስጥ የምትገኝና አሁን በአልባኒያና ዩጎዝላቪያ ውስጥ ያለች ከተማ) በመውሰድ ጥሪውን ከፍጻሜ እንዲያደርስ ረድቶታል። እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተአምራትን እንዲሠራ በማድረግ የጳውሎስን አገልግሎት አጽድቋል።

ሐ. ወንጌሉ ባልተሰበከባቸው አካባቢዎች የማገልገል ጥሪው ከሮም ወደ ምዕራባዊ ጫፍ (ስፔይን) እየወሰደው ነበር። ይህን አገልግሎት በሚያካሂድበት ጊዜ እግረ መንገዱን የሮሜ ክርስቲያኖችን ለማየት ሲወጥን የነበረውን የረዥም ጊዜ ፍላጎቱን ለማሟላት አሰበ። ጳውሎስ በሮሜ ለተወሰነ ጊዜ ከቆየ በኋላ ክርስቲያኖቹ ወንጌሉን በማሰራጨቱ ረገድ አብረውት እንደሚሠሩ ተስፋ አደረገ። ይህም ለምሥራቃዊ የሮም ክፍል ወንጌሉን በመስበኩ በኩል የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ያበረከተችውን አስተዋጽኦ የሚመስል ነበር (ፊልጵ. 4፡10–18)።

መ. ጳውሎስ ወደ ሮሜ ከመሄዱ በፊት የመቄዶንያ (ሰሜን ግሪክ) እና አካይያ (ደቡብ ግሪክ) አሕዛብ ክርስቲያኖች ለድሀ የአይሁድ ክርስቲያኖች ያወጡትን ስጦታ ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዞ ነበር። በአካል ባንተዋወቅም እንኳን የክርስቶስ አካል ክፍሎች የሆንን ሁሉ እርስ በርሳችን ልንረዳዳ ይገባናል። የአይሁድ ክርስቲያኖች ለአሕዛብ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ በረከትን ስላመጡ፥ በአሕዛብ ክርስቲያኖች የገንዘብ ችግር ለደረሰባቸው አይሁዳውያን ድሆች እርዳታ መስጠቱ ተገቢ ነበር።

ሠ. ጳውሎስ የሮሜ ክርስቲያኖች እንዲጸልዩለት ጠየቀ። ለሌሎች መጸለይ በአገልግሎታቸው ውስጥ ከምንሳተፍባቸው መንገዶች አንዱ መንገድ ነው። የጳውሎስ ጭንቀት ምን ነበር? በመጀመሪያ፥ በኢየሩሳሌም ሊያጠፉት ስለሚፈልጉ የማያምኑ አይሁዶች ያስብ ነበር። ሁለተኛ፥ በኢየሩሳሌም የሚገኙ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች በአሕዛብ ክርስቲያኖች ላይ መጥፎ ስሜት ይዘው የሚያመጣላቸውን ስጦታ ላለመቀበል እንዳይወስኑ ስግቶ ነበር።

| |
|---|
| 24ኛ ጥያቄ፡- ሮሜ 16ን አንብብ። በዚህ የሰላምታ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኙትን ለየት ያሉ ነገሮች ዘርዝር። |

2. ጳውሎስ በሮሜ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚያውቃቸው ሰዎች ያቀረበው ሰላምታ (ሮሜ 16)

ጳውሎስ በሮሜ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚያውቃቸው ሰዎች ሰላምታ በማቅረብ መልእክቱን ይደመድማል። እንዲህ ዓይነት ረዥም የሰላምታ ዝርዝር በጳውሎስ ጽሑፎች ውስጥ ያልተለመደ በመሆኑ፥ ምሁራን ጳውሎስ በአካል ባይጎበኛቸውም የሮሜን ክርስቲያኖች እንደሚያውቃቸው ለማሳየት እየሞከረ ነበር ይላሉ። ነገር ግን በሮሜ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከነበሩት ብዙ ሰዎች ጋር ጥልቅ ግላዊ ወዳጅነት ነበረው።

ሀ. ፌቤን ከቆሮንቶስ ከተማ 8 ኪሎ ሜትሮች ያህል ወጣ ብላ በምትገኝ የክንክራኦስ ከተማ የምትኖር ክርስቲያን ነበረች። የጳውሎስን መልእክት ወደ ሮም ያደረሰችው እርሷው ነበረች። ጳውሎስ እንደ ዲያቆንና ልዩ የክርስቶስ አገልጋይ እንዲቀበሏት ጠይቋቸዋል።

ለ. ጳውሎስ ለሚከተሉት ወገኖችም ልዩ ሰላምታ ልኮላቸዋል (ሮሜ 16፡1-16)።

1. በዚህ ወደ ሮም ለተመለሱት ጵርስቅላና አቂላ እነዚህ ልዩ የጳውሎስ ወዳጆች ሕይወታቸውን ከአደጋ ላይ እየጣሉ ሁልጊዜም ከጳውሎስ ጎን የቆሙ ሲሆን፥ ለግሪክና ለትንሹ እስያ አብያተ ክርስቲያናት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። እንደ ጳውሎስ ያሉት ታላላቅ ወንጌላውያን ተግባራቸውን የሚወጡት ብቻቸውን አልነበረም። እግዚአብሔር ሁልጊዜም ወንጌላውያንን የሚረዱ ሰዎችን ያመጣል። ያለ እነዚህ ወገኖች እገዛ ቤተ ክርስቲያን ልታድግ አትችልም። ወንጌሉን በማሰራጨቱ ረገድ እግዚአብሔር አቂላና ጵርስቅላን በከፍተኛ ደረጃ ተጠቅሞባቸዋል። አሁንም እንኳ እግዚአብሔር እየተጠቀመባቸው ነበር። ምንም እንኳ የሙሉ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያልነበሩ በድንኳን ሰፊነት የሚተዳደሩ ቢሆኑም፥ እግዚአብሔር መንግሥቱን ለማስፋፋት ተጠቅሞባቸዋል። በሮም በቤታቸው ውስጥ የቤተ ክርስቲያን አምልኮ ይካሄድ ነበር።

2. አጤኔጦን ኤፌሶን በምትገኝበት የእስያ አውራጃ የመጀመሪያው አማኝ ነበር። ማርያ ለሮሜ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ዕድገት ተግታ ትሠራ ነበር።

3. አንዲራኒቆንና ዩልያን ምናልባትም የጳውሎስ ዘመዶች የሆኑ ባልና ሚስት ሳይሆኑ አይቀሩም። ከጳውሎስ ጋር ታስረው የነበሩ ሲሆኑ፥ ሐዋርያት

ተብለው ተጠርተዋል። ምሁራን ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ምን ማለቱ እንደሆነ ይከራከራሉ። እነዚህ ሁለት ሰዎች «ዘመዶቼ» የሆኑት አይሁዶች በመሆናቸው ነው ወይስ የጳውሎስ የሩቅ ዘመዶች ይሆኑ? ከጳውሎስ ጋር አብረውት የታሰሩት የት ነበር? ስማቸው በሐዋርያት ሥራ ውስጥ አልተጠቀሰም። ጳውሎስ ሐዋርያት ብሎ ሲጠራቸው ምን ማለቱ ነው? ምናልባትም ጳውሎስ የቃሉን ሰፊ ትርጉም በመውሰድ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ምሥረታ እንደተጠቀመባቸው መግለጹ ይሆናል። እነዚህ ሁለቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይህንን ስጦታ ተቀብለው ነበር (ሴቷ ዩልያ ‹ሐዋርያ› እንደተባለች ልብ በል።)

4. ኢሩባኖን፥ ጢልያጦን፥ ስንጣክን፥ ኤጤሌን የሚሉት ስሞች ሁሉ በሮም ቤተ መንግሥት ውስጥ የታወቁ የባሪያዎች ስሞች ነበሩ። ይህም ወንጌሉ በኔሮ ቤተ መንግሥት እንዴት ሥር ሰድዶ እንደገባ ሊያሳይ ይችላል። ጳውሎስ በኋላ ታስሮ ሳለ ለኔሮ የግል ጠባቂዎች መስክሮላቸዋል (ፊልጵ. 1፥13)።

5. አርስጣባሉስ ምናልባትም የታላቁ የሄሮድስ የልጅ ልጅና የሄሮድስ አግሪጳ ቀዳማዊ ወንድም ሳይሆን አይቀርም። ይህም ወንጌሉ ወደ ቤተ መንግሥቱ ባለሥልጣናትም እንደደረሰ ያሳያል።

6. ፕሮፊሞና፥ ጢሮፊሞሳ (ምናልባትም እኅትማማቾች) እና ጠርሲዳ ለጌታ ባበረከቱት አገልግሎት የሚታወቁ ሴቶች ነበሩ።)

ሐ. ጳውሎስ እነዚህ ክርስቲያኖች የሐሰት ትምህርትን እንዳያምኑ ያስጠነቅቃል (ሮሜ 16፡17-20)። ቤተ ክርስቲያንን የሚከፋፍል ትምህርት ከሚያስተምሩ ሰዎች መራቅ ያስፈልጋቸው ነበር። ይህ ዛሬ ለእኛም ጥሩ ማስጠንቀቂያ ነው። በጳውሎስ ዘመን የሐሰት አስተማሪዎች እንደነበሩ ሁሉ፥ በዘመናችንም አሉ። የሐሰት አስተማሪዎችን እንዴት ለይተን እናውቃለን? ቀዳሚው መለያ ክብሩን ማን እንደሚወስድ ማጤን ነው። አንዳንድ ሰዎች እንደበተ ርቱዕ ሆነው በመቅረብ ብዙዎችን ቢያታልሉም፥ ራሳቸውን እንጂ ክርስቶስን አያከብሩም። አንዳንድ ጊዜ አስተማሪዎች በሌሎች ኪሳራ ባለጸጋ ይሆናሉ። ክርስቲያኖች ራሳቸውን መጠበቅ ያለባቸው እንዴት ነው? ከእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ጋር ግንኙነት ወይም ኅብረትን ባለመፍጠር ነው። ጳውሎስ በክርስቲያናዊ አንድነት ላይ አጽንኦት ሰጥቷል። ነገር ግን አንድነትና ኅብረት ሊያደርጉ የሚገባቸው እግዚአብሔርን ለማክበር የሚፈልጉ ሰዎች ናቸው። ክርስቲያኖች ነን እያሉ አንድነትን የሚያሰናክሉና የሐሰት ትምህርትን የሚያስፋፉ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ኅብረት ውጭ መሆን አለባቸው። አለበለዚያ ከእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ጋር ኅብረት ማድረጉ ለእነርሱ የተሳሳተ ሃሳብ ረዳት መሆን ነው።

> 25ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ቤተ ክርስቲያንህን የሚያስቸግሩትን አንዳንድ የሐሰት አስተማሪዎች ዘርዝር። ለ) ሌሎች ክርስቲያኖችና ሽማግሌዎች እንዴት እየተቀበሏቸው ነው? ሐ) ጳውሎስ እነዚህን የሐሰት አስተማሪዎች እንዴት እንድንቀበላቸው የሚፈልግ ይመስልሃል? መ) ዛሬ ያንን ለማድረግ የማንፈልገው ለምንድን ነው?

መ. ጳውሎስ ሰላምታ ያስተላልፋል (ሮሜ 16፡21-24)።

1. ጢሞቴዎስ– ወንጌሉን በማሰራጨቱ በኩል የጳውሎስ ረዳትና የሥራ ባልደረባ።

2. ሉቂዮስ፥ ኢያሶን፥ ሱሲጴጥሮስ– ምናልባትም የቆሮንቶስና የመቄዶኒያ አብያተ ክርስቲያናት ዐበይት መሪዎች ሳይሆኑ አይቀሩም (የሐዋ. 17፡5–9፤ 20፡4)።

3. ጤርጥዮስ፥ የጳውሎስን መልእክት ጻሐፊ።

4. የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን መሪና ብዙውን ጊዜ ታይተስ ጆስትስ በመባል የሚታወቀው ጋይዮስ (የሐዋ. 18፡7፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡14)።

5. በቆሮንቶስ መንገዶች ጨምሮ ብዙ ጉዳዮችን የሚያስፈጽም ቁልፍ የፖለቲካ መሪ የሆነው ኤርስጦስ። ኤርስጦስ አማኝ መሆኑ አያጠራጥርም።

ሠ. ጳውሎስ መልእክቱን በቡራኬ ይደመድማል (ሮሜ 16፡25–27)። የሮሜ መልእክት በወንጌል ላይ ያማከለ መጽሐፍ ነው። የወንጌሉም አሳብ በዚህ የማጠቃለያ ቡራኬ ላይ ያማክላል። ክርስቶስ እስከመጣበት ጊዜ ድረስ ከሰዎች በምሥጢርነት ተሰውሮ የነበረው ወንጌል አሁን ተገልጧል። የእግዚአብሔር ፍላጎት ሰዎች በክርስቶስ አምነው የታዛዥነትን ሕይወት እንዲመሩ ነበር። የሮሜን ክርስቲያኖች በዚህ ወንጌል የሚመሠርታቸው ደግሞ እግዚአብሔር ነበር። የጳውሎስ ትልቁ ፍላጎት የእግዚአብሔር ለዘላለም መክበር ነበር።

> 26ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ዛሬ እግዚአብሔርን የምናስከብርባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ለ) ይህ እንዴት የሕይወታችን ዋነኛ ዓላማ መሆን እንዳለበት ግለጽ። ሐ) በምታደርገው ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብርን እያመጣህለት እንደሆነ በጸሎት ጠይቀው። ዛሬ ለእርሱ ክብር ለመኖር ራስህን እንደገና አሳልፈህ ስጥ።

**አራተኛ ቀን፡** ለሳምንታዊ ስብሰባ ለመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ

## ሳምንታዊ ስብሰባ

ውይይት፡–

ሀ. 1) አይሁዶች ከአሕዛብ የበለጠ ጥቅም ያገኙት እንዴት ነው? 2) በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ አይሁዶችና አሕዛብ በፊት፥ አሁንና ወደፊት ምን ዓይነት ግንኙነት ይኖራቸዋል? 3) አይሁዶች በክርቶስ ለማመን የሚቸገሩት ለምንድን ነው? 4) ራሳቸውን እንደ ጥሩ ሰዎች አድርገው የሚመለከቱ ሌሎች ሃይማኖተኞችም ስለ ደኅንነት የተሳሳተ አሳብ የሚይዙት ለምንድን ነው?

ለ. 1) ሮሜ 10፡9–10ን ጥቀስ። 2) ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ሰዎች ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው ሊቀበሉ እንደሚገባ እየተናገሩ፥ እንደ ጌታቸውም ሊቀበሉት እንደሚገባ ግን አይብራሩም። ሀ) ይህ ሚዛናዊ አስተምህሮ ይመስልሃል? ለ) ሰዎች ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው ሊቀበሉና በእርሱ ጌትነት ሥር ለመኖር ቃል ሊገቡ የሚገባቸው ለምን ይመስልሃል? 3) ብዙ አማኞች የሌሉባቸውን የኢትዮጵያ ነሳዎች ዘርዝር። 4)

ሰምተው ይድኑ ዘንድ ወንጌልን የሚመሰክርላቸው ማን ነው? ለእነዚህ ሰዎች ወንጌሉን ለማዳረስ እግዚአብሔር አንተና ቤተ ክርስቲያንህ ምን ዓይነት ሚና እንድትጫወቱ የሚፈልግ ይመስልሃል? 5) ብዙ ወጣቶች ለጠፉት ወንጌል መስበክን እንደተከበረ ሙያ የማይመለከቱት ለምንድን ነው? ለሕይወት አስፈላጊ ስለሆነው ጉዳይ የእግዚአብሔርን አመለካከት በተሳሳተ መንገድ የተረዱት እንዴት ነው?

ሐ. 1) ሮሜ 12፡1-2ን አንብብ። ከዚህ ምንባብ እግዚአብሔር ከአማኞች ምን እንደሚጠብቅ ነው የምንማረው? 2) ጳውሎስ በሮሜ 12-16 ከሌሎች አማኞች፥ ከማያምኑ ሰዎችና ከመንግሥት ጋር ሊኖረን ስለሚገባው ግንኙነት የሰጠውን ትምህርት ጠቅለል አድርገህ ግለጽ። 3) ዛሬ ክርስቲያኖች ከሁሉም በላይ የሚታገሉት ከየትኛው ጋር ነው? 4) ብዙ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች መንግሥትን እንዴት እንደሚመለከቱ ተወያዩ። ይህንን ከጳውሎስ አመለካከት ጋር አነጻጽሩ። በመንግሥት ሥልጣን ላይ የሚገኙ ክርስቲያኖች ምን ድርሻ አላቸው? በእነዚህ ክርስቲያኖች ላይ የሚያንዣብበው አደጋ ምንድን ነው? በመንግሥት ሥልጣን ላይ የሚገኙ ክርስቲያኖች እንደ ዮሴፍ እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ አገራቸውን እንዲመሩ ለማገዝ ቤተ ክርስቲያን ምን ሚና ልትጫወት ትችላለች? 5) በ1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡1-2 ለባለሥልጣናት እንድንጸልይ ታዘናል። ቤተ ክርስቲያንህ ይህንን የምታደርገውና ክርስቲያኖች በቀዳሚነት ለመንግሥት ባለሥልጣናት እንዲጸልዩ የምታበረታታው እንዴት ነው? 6) በቀበሌህ፥ በወረዳህ፥ በክልልና በፌዴራል ደረጃ የሚሠሩትን የመንግሥት ባለሥልጣናት ስም ዝርዝር። አሁን ጊዜ ወስደህ ጸልይላቸው።

መ. 1) ጥሩ ክርስቲያን ሊያደርግ በሚችላቸውና በማይችላቸው ነገሮች ላይ የሚከሰት የአሳብ ልዩነት ክፍፍልን ሲያስከትል ያየኸው እንዴት ነው? 2) ጳውሎስ በሮሜ 14፡1-15፡13 ባስተማረው መሠረት፥ ለሰላማዊትና ለፍቅርተ ምን ምክር ትሰጣለህ? 3) የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ወይም ክርስቲያኖች የሚከራከሩባቸውን ልምምዶች ዘርዝር። በዚህ የጳውሎስ አስተምህሮ መሠረት፥ ክርስቲያኖች ለእነዚህ ልምምዶች ምን ዓይነት ምላሽ ሊሰጡ ይገባል? ይህ ትምህርት በሰዎች አስተሳሰብና ተግባር ላይ ምን ዓይነት ለውጥ ያስከትላል?

ሠ. 1) ጳውሎስ አማኝ ሆኖ ስለመመላለስ በሚናገራቸው አሳቦች መሠረት፥ ለአዳዲስ ክርስቲያኖች ልናስተምር የሚገባን አስፈላጊ ነገር ምንድን ነው? 2) ቤተ ክርስቲያንህ ለአዳዲስ አማኞች የምታስተምረውን ጳውሎስ ካስተማረው አሳብ ጋር አነጻጽር። ጳውሎስ ለክርስቲያኖች ጠቃሚ ናቸው ያላቸውን ነገሮች ለመከተል ይቻል ዘንድ ምን ዓይነት ለውጥ ማድረግ ያስፈልግሃል?

ረ. 1) ቤተ ክርስቲያንህን እየጎዱ ያሉትን አንዳንድ የሐሰት አስተማሪዎች ዘርዝር። 2) የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና ክርስቲያኖች እነዚህን ሰዎች የሚያስተናግዱት እንዴት ነው? 3) ጳውሎስ እነዚህ አስተማሪዎች እንዴት እንዲስተናገዱ የሚፈልግ ይመስልሃል? 4) ዛሬ ያንን ለማድረግ የማንፈልገው ለምንድን ነው?

# ትምህርት አራት

## የመጀመሪያ ቀን　　　የ1ኛ ቆሮንቶስ መግቢያ

አንዳንድ ክርስቲያኖች «እንደ ጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ብንሆን መልካም ነበር። ክርስቲያኖች ታላቅ ፍቅርና አንድነት፥ እንዲሁም መንፈሳዊ ሕይወት ነበራቸው፥ አስደናቂ ተአምራት ይደረጉ ነበር። ወደ ጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ዘመን መመለስ ይኖርብናል። ያኔ እግዚአብሔር ያለ ጥርጥር ይባርከናል ይላሉ። እውን እነዚያ ጊዜያት ከእኛ ዘመን የተሻሉ ነበሩ? አዲስ ኪዳንን በጥንቃቄ በምናጠናበት ጊዜ ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችንን የሚያውኩ ችግሮች በቀድሞዪቱም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደነበሩ እንገነዘባለን። ግብዝነት፥ ክፍፍል፥ ዝሙት፥ የሐሰት ትምህርትና እግዚአብሔርን ለማስደሰት ከነበራቸው ፍላጎት የሚመነጩ የሕግ አጥባቂነት አመለካከቶች ይታዩ ነበር።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ክርስቲያኖች የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን በመሰልን እያሉ ሲመኙ የሰማኸው መቼ ነው? ለ) ከላይ የተጠቀሱትን የጥንት ቤተ ክርስቲያን ችግሮች ተመልከትና፥ ዛሬ ከእነዚህ መካከል የትኞቹ ችግሮች ቤተ ክርስቲያኖቻችንን እንደሚያውኩ ግለጽ። ለእነዚህ ለእያንዳንዳቸው ችግሮች ምሳሌዎችን ስጥ። |

የሮሜ መልእክት ከጳውሎስ መጻሕፍት ሁሉ ረዥም በመሆኑ፥ ከሐዋርያት ሥራ ቀጥሎ በቀዳሚነት ቀርቧል። ይህ መጽሐፍ ሰው እንዴት እንደሚድን፥ እንደዳነ፥ ሰው ኃጢአትን እንዴት እንደሚያሸንፍና የእግዚአብሔር ልጆች ስለሚወርሱት ተስፋ በመግለጽ ሥነ መለኮታዊ የደኅንነት ጉዳዮችን ያብራራል። ከጳውሎስ መልእክቶች በርዝመቱ የሁለተኛነቱን ደረጃ የያዘው የቆሮንቶስ መልእክት ነው። 1ኛ ቆሮንቶስ የተጻፈው በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩትን የተወሰኑ ችግሮች ለመቅረፍ ነበር። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ አብዛኞቹ ችግሮች ዛሬ በየቤተ ክርስቲያኖቻችን ውስጥ ይገኛሉ። ስለሆነም፥ ለክርስቲያኖች የ1ኛ ቆሮንቶስን ትምህርት በግልጽ መረዳት ጠቃሚ ነው።

| |
|---|
| 2ኛ ጥያቄ፡- ስለ 1ኛ ቆሮንቶስ ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት አንብብ። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደ ተመሠረተች፥ የቆሮንቶስ ከተማ ምን እንደምትመስል፥ የመጽሐፉ ደራሲ ማን እንደሆነ፥ የመጽሐፉ ዓላማ ምን እንደሆነ፥ ወዘተ... ጠቅለል አድርገህ ጻፍ። ለ) ይህ መጽሐፍ ከዛሬዪቱ ቤተ ክርስቲያን ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን እውነቶች ይይዛል ብለህ የምታስብባቸውን ምክንያቶች ዘርዝር። |

## የ1ኛ ቆሮንቶስ መግቢያ

ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 11፡28-29 በሐዋርያነት አገልግሎቱ ያጋጠሙትን ችግሮች ሲገልጽ፥ «የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው። የሚደክም ማን ነው? እኔም አልደክምምን? የሚሰናከል ማን ነው? እኔም አልናደድምን?» ብሏል። እግዚአብሔር በሮም ግዛት ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ለመመሥረት በጳውሎስ ተጠቅሟል። ጳውሎስ ግን ቤተ ክርስቲያን በመመሥረቱና የተወሰኑ ሰዎች ለጸሎትና አምልኮ ሲሰባሰቡ በማየቱ ብቻ የሚረካ ሰው አልነበረም። እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወቷ እንድትበስል

ይፈልግ ነበር። በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ጸሎቶች ብንመለከት፥ ጳውሎስ አማኞች በእውቀት፥ በአንድነትና በብስለት እንዲያድጉ ከልብ መሻቱን እናያለን። (ለምሳሌ፥ ኤፌ. 1፡14-21፤ 3፡14-21)። ጳውሎስ እጅግ አጥብቆ ለሚወደው ለክርስቶስ አማኞችን እንደ ንጽሕት ሙሽራ አድርጎ ለማቅረብ ይፈልግ ነበር (2ኛ ቆሮ. 11፡2)። ክርስቲያኖች እንደ እግዚአብሔር ልጆች የሚገባቸውን ዓይነት ሕይወት ሳይኖሩ በሚቀሩበት ጊዜ ጳውሎስ በፍቅርና አንዳንዴም በቁጣ ወደ ትክክለኛው ስፍራ ሊመልሳቸው ይተጋል። ከእግዚአብሔር መንገድ ሾልከው የሚወጡ ልጆች በሥጋ የወለዷቸውን ሰዎች ስሜት በእጅጉ እንደሚጎዱ ሁሉ፥ ጳውሎስም መንፈሳዊ ልጆቹ ከእውነት ፈቀቅ በሚሉበት ጊዜ በጽኑ ይቆስል ነበር። ጳውሎስ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለመመለስ ብቻ ሳይሆን በእምነታቸው እንዲያድጉ ለመርዳት ጭምር የተሰጠውን ሐዋርያዊ ሥልጣኑን ተመለከተ።

> 3ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ለቤተ ክርስቲያንህ በማሰብ ምን ያህል በጽኑ እንደተጎዳህ ግለጽ። ለ) አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለቤተ ክርስቲያናቸው ምእመናን መንፈሳዊ ዕድገት አጥብቀው በማሰባቸው ምክንያት እንደ ጳውሎስ የሚጎዱ ይመስልሃል? መልስህን አብራራ። ሐ) ብዙ ሰዎች እየዳኑ ቢሆኑም፥ ብዙዎች ደግሞ ከቤተ ክርስቲያን እየወጡ ናቸው። ይህ አማኞች ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው እንዲመለሱና በእምነታቸው እንዲያድጉ መሪዎች የሆንን ሰዎች ተግተን አለመሥራታችንን የሚያሳየው እንዴት ነው?

ምናልባትም የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በጳውሎስ ላይ ከፍተኛ ሥቃይና ሕመም ሳታስከትል አልቀረችም። በመሆኑም ከሌሎች ሁሉ በላይ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ብዙ መልእክት ጽፎአል። ጳውሎስ እነዚህ ክርስቲያኖች ችግሮቻቸውን ተቋቁመው በእምነታቸው እንዲያድጉ በማበረታታት 1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስን ጽፎላቸዋል። ጳውሎስ ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ቢያንስ ሁለት ተጨማሪ መልእክቶችን የጻፈ ቢሆንም፥ ጠፍተዋል።

ጳውሎስ በቆሮንቶስ 18 ወራትን ስላሳለፈ፥ ቤተ ክርስቲያኒቱንና ክርስቲያኖቹን በደንብ ያውቃቸው ነበር። ስለሆነም፥ እንደ ሮሜ መልእክት አጠቃላይ እውነቶችን ከማብራራት ይልቅ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያኒቱ ባጋጠማት የተወሰኑ ጉዳዮች ላይ አተኩሯል።

## የ1ኛ ቆሮንቶስ ደራሲ

> 4ኛ ጥያቄ፡- ሀ) 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡1ን አንብብ። ደራሲው ማን እንደሆነና ራሱን እንዴት እንደሚገልጽ ተናገር። ለ) ይህን መግቢያ ከሮሜ 1፡1 ጋር አነጻጽርና ደራሲው ስለ ራሱ አጽንኦት ሰጥቶ በጠቀሳቸው ነገሮች መካከል ያሉትን ልዩነቶች ግለጽ።

ጳውሎስ በመልእክቶቹ ሁሉ መጀመሪያ ራሱን፥ «በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ ጳውሎስ» ብሎ በማስተዋወቅ ጥንታዊ የደብዳቤ አጀማመር ይከተላል። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ከሚከፋፈሉባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የጳውሎስ ሥልጣን በኢየሩሳሌም ከነበሩት ሐዋርያት ጋር እኩል የመሆኑ ወይም ያለመሆኑ ጉዳይ ነበር። ለዚህም ነበር ሐዋርያው ጴጥሮስ የበለጠ ሥልጣን አለው ብለው ያሰቡት ወገኖች «እኛ የጴጥሮስ ነን» ያሉት። ከ2ኛ ቆሮንቶስ መልእክት አብዛኛው

ጳውሎስ ከሌሎች ሐዋርያት ጋር እኩል መሆኑን በመግለጽ የተከራከረበት ነው። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ መግቢያው የኢየሱስ ክርስቶስ «ሐዋርያ» መሆኑን በአጽንኦት ገልጾአል። ኢየሱስ ክርስቶስን ወክሎ ለዓለም ሁሉ እንዲያገለግል እግዚአብሔር ነበር ለይቶ የመረጠው። ጳውሎስ ራሱ ሐዋርያ ለመሆን እንዳልመረጠና ራሱን በሚያስደንቀው ሁኔታ እግዚአብሔር እንደመረጠው ገልጾአል። ስለሆነም፥ ጳውሎስ የሚናገረውን አለመስማት ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ የሚናገረውን አለመስማት እንደ ማለት ነበር።

ይህ ልናስታውሰው የሚገባን ጠቃሚ እውነት ነው። አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ወይም እንደ ጳውሎስ ያሉ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰጧቸውን ትእዛዛት በማይፈጽምበት ጊዜ ሁሉ፥ በእግዚአብሔር ላይ እያመፀ ነው ማለት ነው። እግዚአብሔር የሚናገረውን ለመስማት አይፈልግም ማለት ነው። ዛሬ የምንኖረው፥ ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ጋር ወደማይጣጣሙ አስደናቂ ነገሮችና ልምምዶች በሚሳቡበት ዘመን ውስጥ ነው። እነዚህ ልምምዶች ስለሚያስደንቋቸውና መልካም ስለሚመስሏቸው ብዙ ክርስቲያኖች ይከተሏቸዋል። «ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ጋር ይስማማል?» የሚል ጥያቄ በሚያነሡበት ጊዜም ስድብ ይሰነዘርባቸዋል። «ለእኛ ጥሩ ስሜት እንዲሰጠን ያደርጋል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆን አለመሆኑን ልትጠይቀን ምን መብት አለህ? ልምምዳችንን እያበላሸህብን ነው።» የሚል ምላሽ ይሰጣሉ። በዚህ ዓይነት በእግዚአብሔር ትእዛዝና ሥልጣን የጸፉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲያን ከመታዘዝ እንቆጠባለን። ራሳችንንና ሌሎች ሰዎችን ለልምምዶቻችን መመዘኛዎች አድርገን እንወስዳለን። ጳውሎስ የጻፈው መልእክት የግል አሳብ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችና እኛም እንድንገነዘብ ይፈልጋል። ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አለመገዛት ማለት ለእግዚአብሔር አለመገዛት ነው።

5ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንዳንድ ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ቃል ከመገዛት ይልቅ ከመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ጋር በማይስማሙ አስደናቂ ነገሮች ሲወሰዱ የተመለከትህበትን ሁኔታ ግለጽ። ለ) ይህ ለቤተ ክርስቲያን አደገኛ የሚሆነው ለምንድን ነው? ሐ) አንዳንድ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ የሚያቀርበውን ግልጽ ትምህርት እየጣሱ የሚያከናውኗቸውና ሌሎችን ወደ ጥፋት የሚመሩባቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? መ) ለብዙ ክርስቲያኖች የአንዳንድ ነገር እውነት መሆን ወይም አለመሆን አሳሳቢ የማይሆነው ለምን ይመስልሃል?

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ራሱን ያስተዋወቀበት ሁኔታ ከሮሜ ቤተ ክርስቲያን ይልቅ አጠር ያለው ለምንድን ነው? ምናልባትም ይህ የሆነው ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን መሥራች በመሆኑና በዚያ የነበሩት ክርስቲያኖች በሚገባ ስለሚያውቁት ይሆናል። ነገር ግን የሮሜ ክርስቲያኖች ጳውሎስን ስለማያውቁት ማንነቱንና የሮሜን መልእክት የጻፈበትን ሥልጣን በጥንቃቄ አብራርቶላቸዋል።

ጳውሎስ የ1ኛ ቆሮንቶስን መልእክት እንደጻፈ የሚጠራጠሩ ምሁራን ጥቂት ናቸው። 1ኛ ቆሮንቶስ ከተጻፈ ከ40 ዓመታት በኋላ (በ95 ዓ.ም.) የሮሜው ክሌመንት የተባለው እውቅ ግለሰብ ይህን መልእክት ጠቅሶታል።

በዚያን ጊዜ መልእክቱ እንደ ሮም ባሉት የአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት እየተገለበጠ ተሰራጭቶ ነበር።

## ጳውሎስ መልእክቱን ለማን ጻፈ?

> 6ኛ ጥያቄ፦ ሀ) 1ኛ ቆሮ. 1፥2 አንብብ። ጳውሎስ ይህንን መልእክት የጻፈው ለማን ነበር? ለ) ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያኒቱን እንዴት ነው የገለጻት? ሐ) ይህንን ከሮሜ 1፥7 ጋር አነጻጽር። ይህ ጳውሎስ የሮሜን ቤተ ክርስቲያን ከገለጸበት ሁኔታ ጋር እንዴት እንደሚመሳሰልና እንደሚለያይ አብራራ። መ) የሐዋ. 18፥1-11ን አንብብና ቤተ ክርስቲያኒቱ መጀመሪያ እንዴት እንደተመሠረተች ጠቅለል አድርገህ ግለጽ።

ጳውሎስ የጥንታዊ ደብዳቤዎችን አጻጻፍ በመከተል ደራሲነቱን ከገለጸ በኋላ ደብዳቤውን ለማን እንደሚጽፍ ጠቅሷል። ጳውሎስ፥ «በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት» ብሏል። ከዚህ ገለጻ አራት ነገሮችን ልንመለከት እንችላለን።

1. ደብዳቤው የተጻፈው ለቆሮንቶስ **ቤተ ክርስቲያን** ነበር። ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ቃል ስንሰማ ሰዎች ስለሚያመልኩበት ሕንፃ እናስባለን። ለዚህም ነው በአማርኛ ቋንቋ «ቤተ ክርስቲያን» (የክርስቲያን ቤት) የሚባለው። ሌሎች ደግሞ «የጸሎት ቤት» ይሉታል። በባሕላችን፥ የቤተ ክርስቲያኑ አስፈላጊነት የሚለካው በቤቱ ትልቅነት ነው። ለዚህም ነው የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች የቤተ ክርስቲያን ሕንፃዎቻቸውን ሁሉም ሰው ሊያይ በሚችልባቸው ደብሮች ላይ የሚሠሩት። የሕንጻዎቹ ማማርም የቤተ ክርስቲያኑን አስፈላጊነት ያጎላዋል ብለው ያስባሉ። ወንጌላውያን ክርስቲያኖችም በሕንፃ ላይ ያተኩራሉ። በቤት ወይም ከቤት ውጭ በመጠለያ ውስጥ ተሰባስቦ ማምለኩ የትንሽነት ስሜት የሚያሳድር ይመስላቸዋል። ይህ ደግሞ መሬት አግኝተው የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ እስኪገነቡ ድረስ ለጊዜው ብቻ የሚጠቀሙበት አማራጭ ነው። የጭር ቤት ካለን ወደ ቆርቆሮ ቤት ለመለወጥ ጥረት እናደርጋለን። ሕንፃው ትልቅ በሚሆንበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያኑም የበለጠ አስፈላጊ ይመስለናል። እንደዚህ ሲሆን ሰዎች ለአምልኮ ይመጣሉ ብለን እናስባለን።

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግን እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ አልነበረም። «ቤተ ክርስቲያን» ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል የትኛውንም ዓይነት የሰዎች ስብስብ ያመለክታል። መንግሥት ሕዝቡን በሚሰበስብበት ጊዜ ስብሰባው «ቤተ ክርስቲያን» ተብሎ ይጠራ ነበር። ስለሆነም፥ እንደ ጳውሎስ ያሉ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ይህን ቃል የሚጠቀሙት የክርስቶስን ተከታዮች ለማመልከት ነበር። የቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎች የተሠሩት ክርስቶስ ከሞተና ከተነሣ ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ በመሆኑ፥ የጥንት ክርስቲያኖች የሚሰባሰቡት በግለሰብ ቤቶች ውስጥ ነበር።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ «ቤተ ክርስቲያን» የሚለው ቃል በሦስት ዐበይት መንገዶች ይተረጎማል። <u>በመጀመሪያ፥</u> የአንድ አካባቢ አማኞች በግለሰቦች ቤት ውስጥ ይሰባሰቡ ነበር። በሮሜ 16፥5 ጳውሎስ በጵርስቅላና አቂላ ቤት ውስጥ ስለምትሰባሰብ ቤተ ክርስቲያን ጽፎአል። <u>ሁለተኛ፥</u> በአንድ አካባቢ የሚገኙ ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን ይባሉ ነበር። ምንም እንኳ በቆሮንቶስ

የሚገኙ ክርስቲያኖች በተለያዩ ቤቶች እየተሰባሰቡ ያመልኩ የነበረ ቢሆንም፥ ጳውሎስ ለሁሉም ባስተላለፈው መልእክት «ለቆሮንቶስ» ሰዎች የሚል አገላለጽ ተጠቅሟል። ሦስተኛ፥ በዓለም ውስጥ የሚገኙትን አማኞች በሙሉ ያመለክታል። ይህም አንዳንድ ጊዜ «ዓለም አቀፋዊው ቤተ ክርስቲያን» የሚባለው ነው (ኤፌ. 1፡22)።

7ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ብዙ ኢትዮጵያውያን ለአምልኮ ጥሩ ሕንፃ ያስፈልጋል ብለው የሚያስቡት ለምንድን ነው? ለ) ይህንን አመለካከት ከአዲስ ኪዳን ዘመን ሁኔታ ጋር አነጻጽር። ሐ) ትልቅ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ መፈለጋችን ጥሩ ይመስልሃል ወይስ መጥፎ? መልስህን አብራራ።

2. **የእግዚአብሔር** ቤተ ክርስቲያን። ለጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን የግለሰብ፥ የክርስቲያኖች ቡድን ወይም የቤተ እምነት ሳትሆን የእግዚአብሔር ናት። ቤተ ክርስቲያንን በክርስቶስ ደም የገዛት እግዚአብሔር ነው። ክርስቲያኖችን የሚጠራቸው እግዚአብሔር ሲሆን፥ መንፈስ ቅዱስ ወደ አማኞች ኅብረት ውስጥ ይጨምራቸዋል። ዛሬ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቤተ ክርስቲያን የእነርሱ ንብረት እንደሆነች ያስባሉ። «ቤተ ክርስቲያኒቱ በእኔ መሬት ላይ ነው የቆመችው። ለቤተ ክርስቲያን ብዙ ገንዘብ ሰጥቻለሁ» ይላሉ። መሪዎች አንዳንድ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የእነርሱ እንደሆነችና ያሻቸውን ሊያደርጉባት የሚችሉ ይመስላቸዋል። ባለቤቷ ለሆነው ለክርስቶስ የሚሠሩ መጋቢያን ብቻ የመሆናቸውን እውነታ ይዘነጋሉ። እርሱም ቤተ ክርስቲያኑን ስላስተዳደሩበት ሁኔታ አንድ ቀን ይጠይቃቸዋል። መሪዎች ቤተ እምነታቸው ብዙ ክብር እንዲያገኝ ይጥራሉ። ቤተ እምነታቸው የፈለጉትን ያህል ክብር ሳያገኝ ሲቀር ወይም አባሎቻቸው የሌላ ቤተ ክርስቲያን አባላት በሚሆኑበት ጊዜ ይቀናሉ። ጳውሎስ ግን የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን ቢመሠርታትም እንኳ የእርሱ ንብረት እንዳልሆነች ያውቅ ነበር። ቤተ ክርስቲያኒቱ ሙሉ ለሙሉ የእግዚአብሔር ንብረት ስለሆነች፥ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የሚያደርጉት ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ሊያስከብር ይገባል። ለግል ወይም ለቤተ እምነት ክብር መሥራት አያስፈልጋቸውም ነበር።

8ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ብዙውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ሳትሆን የእኛ ናት ብለን የምናስበው ለምንድን ነው? ለ) የየትኛውም ቤተ እምነት ተከታይ የሆነ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ የእግዚአብሔር እንደሆነ ብናስብ አመለካከታችን እንዴት ይቀየራል?

3. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ሰዎች **በክርስቶስ ተቀድሰዋል**። ጳውሎስ በኃላፊ ጊዜ ግስ እየተናገረ መሆኑን አጢን። ጳውሎስ ወደፊት እንደሚቀደሱ ሳይሆን ቀደም ሲል እንደተቀደሱ ገልጾአል። ጳውሎስ የሚጽፍላቸው እነዚህ ክርስቲያኖች ምን ዓይነት ሕይወት ይኖሩ ነበር? ትክክለኛውን የቅድስና ፍች የሚያንጸባርቅ ሕይወት ይመሩ ነበር? አልነበረም። የወሲብ ኃጢአት፥ ክፍፍል፥ የጌታን እራት አግባብነት በጎደለው ሁኔታ የመመገብ ኃጢአቶች ነበሩባቸው። እንዲያውም አንዳንዶች በጌታ እራት አወሳሰድ ላይ በፈጸሙት ጥፋት የሞትና የሕመም ቅጣት ደርሶባቸው ነበር። ቤተ ክርስቲያኒቱ በራስ ወዳድነት ተሞልታ ነበር። ይህም ሆኖ፥

ጳውሎስ «ተቀድሰዋል» ብሏል። ለምን? ምክንያቱም መቀደስ ማለት መለየት ማለት ነው። እግዚአብሔር በቆሮንቶስ ከተማ ውስጥ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ መካከል ልጆቹ እንዲሆኑለት መርጧቸዋል። እንደ ልጆቹ ተመላለሱም አልተመላለሱ፥ በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት በክርስቶስ በማመናቸው ምክንያት ከዓለም የተለዩ ልጆቹ ናቸው።

4. **ቅዱሳን ለመሆን ተጠርተዋል።** ምንም እንኳ እነዚህ ሰዎች ከብዙ ችግሮች ጋር ቢታገሉም፥ እግዚአብሔር በሕይወታቸው ለመሥራት የሚፈልግበት ዓላማ ነበረው። ጳውሎስ እግዚአብሔር ከሁሉም በላይ በቅድስና እንዲኖሩ የሚፈልግ መሆኑን ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ገልጾላቸዋል። ቢቀደሱ ኖሮ ክፍፍላቸው፥ የወሲብ እርኩሰታቸው፥ ራስ ወዳድነታቸው፥ ወዘተ... ይለወጥ ነበር። ጴጥሮስ እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ፥ እኛም በቅድስና እርሱን እንድንመስል ጠይቆናል (1ኛ ጴጥ. 1:15-16)። መቀደስ ማለት ኃጢአትን አለመሥራት ማለት ብቻ አይደለም። መቀደስ ማለት መለየትና ልዩ መሆን ማለት ነው። ይህም በአመለካከታችን፥ በዓላማችን፥ በባሕሪያችንና በተግባራችን ከዓለም መለየታችንን ያሳያል። ይህ ክርስቶስን የምንመስልበትና እንደ እርሱ የምንመላለስበት ሕይወት ነው። እግዚአብሔር ከልጆቹ ሁሉ የሚፈልገው ይህንን ነው። አንድ ሰው አማኝ ነኝ እያለ ምንም ዓይነት ለውጥ ሳያሳይ በተከታይ በኃጢአት ውስጥ የሚመላለስ ከሆነ፥ ደኅንነቱን ልንጠራጠር እንችላለን።

> 9ኛ ጥያቄ፡- እግዚአብሔር አንተን ከጠራባቸው ምክንያቶች አንዱ እርሱን እንድትመስልና እንድትቀደስ ነው። ሀ) ክርስቲያን ከሆንህ በኋላ ክርስቶስን ለመምሰልና ለመቀደስ የለወጥሃቸውን ነገሮች ዘርዝር። ለ) በተግባርህና በአስተሳሰብህ አሁንም ክርስቶስን እንዳትመስል የሚከራከሩህ ያልተቀደሱ ነገሮችህ ምንድን ናቸው? አሁን ጊዜ ወስደህ እነዚህን ኃጢአቶች ተናዘዝና መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን ትመስል ዘንድ እንዲለውጥህ ጠይቀው።

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ተመሠረተች? ጥንታዊቷ የቆሮንቶስ ከተማ ምን ትመስል ነበር? በሐዋርያት ሥራ 18 እንደተገለጸው፥ ጳውሎስ በሁለተኛው የወንጌል መልእክተኛነት (ሚሲዮናዊ) ጉዞው ወደ ቆሮንቶስ ከተማ ሄደ። በዚያም ለ18 ወራት ሲሰብክና ቤተ ክርስቲያን ሲተክል ቆየ። ቆሮንቶስ ጳውሎስ በሁለተኛው የወንጌል መልእክተኛነት ጉዞው ወቅት የቆየባት ዐቢይ ከተማ ነበረች። በዚህ ጊዜ ነበር እግዚአብሔር ጳውሎስ ብዙ አይሁዶችንና አሕዛብን፥ በተለይም ግሪኮችን ወደ ክርስቶስ እንዲመልስ የተጠቀመበት። አብዛኞቹ ግሪኮች በግሪክ ፍልስፍናና ትምህርት ይደነቁ ስለነበር፥ ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ጥበብ ጋር ሲነጻጸር የዓለም ጥበብ ሞኝነት እንደሆነ ገለጻላቸው (1ኛ ቆሮ. 1:18-2:16)። ነገር ግን አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ከሀብታሞች ወይም ከተማሩት ወገን የመጡ ሳይሆኑ፥ ድሆች፥ ያልተማሩና ምናልባትም ባሮች ነበሩ (1ኛ ቆሮ. 1:26-28)። በሦስተኛው የወንጌል መልእክተኛነት ጉዞው ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ተመልሶ 3 ወራት በዚያ አሳልፎአል።

ጳውሎስ ወንጌልን በሰበከበት ወቅት የወንጌሉ ንጹሕነት ከሰዎች የክፋት ሥራ ጋር ግጭት ሊፈጥር ችሏል። ቆሮንቶስ በሮሜ የአካይያ ክፍለ ሐገር ዋና ከተማ ነበረች። (ቆሮንቶስ ግሪክ ውስጥ ያለችበትን ስፍራ ለማወቅ

ከመጽሐፉ በስተጀርባ ያለውን ካርታ ይመልከቱ።) ቆሮንቶስ በአያሌ ነገሮች የታወቀች ከተማ ነበረች።

ሀ. ትልቅ ከተማ ነበረች። በከተማዪቱ ውስጥ 250,000 ነፃ ሰዎችና 400,000 ባሪያዎች ይኖሩ እንደነበረ ይገመታል።

ለ. ዋነኛ የንግድ ከተማ ነበረች። ቆሮንቶስ ሁለት ውኃማ አካላትን በምትከፍል አነስተኛ ሰርጥ ውስጥ የተመሠረተች ከተማ ነበረች። በስተምሥራቅ ወደ እስያና መካከለኛው ምሥራቅ የሚወስድ የኤጂያን ባሕር ነበር። በስተምዕራብ የአድሪያቲክ ባሕርና ወደ ሮም የሚወስድ መንገድ ነበር። ይህም የሮም ግዛት እምብርት ነበር። ከሮም ወደ ምሥራቅና እስያ የሚሄዱ ነጋዴዎች ሁሉ በቆሮንቶስ ከተማ ውስጥ ይገናኙ ነበር። ብዙውን ጊዜ ባለመርከቦች አደገኛ በሆነው የብስ ዙሪያ ከመጓዝ ይልቅ ዕቃዎቻቸውን በቆሮንቶስ ከተማ ውስጥ ያራግፉ ነበር። ዕቃው ወደ ሌላው የመሬቱ ሰርጥ 8 ኪሎ ሜትሮች ያህል ከተጓዘ በኋላ በሌላ ጀልባ ይጫናል። ይህም ቆሮንቶስ የንግድ ቀጠና እንድትሆን አድርጓታል።

ሐ. ቆሮንቶስ የፍቅር ጣዖት የሆነችው የአፍሮዳይት አምልኮ እምብርት ነበረች። ምንም እንኳ በከተማዪቱ ውስጥ ቢያንስ ሌሎች 11 ቤተ ጣዖታት የነበሩ ቢሆኑም፥ አፍሮዳይት ከሁሉም የላቀ ዝና ነበራት። በተራራው ጫፍ ላይ ታላቅ ቤተ ጣዖት ተሠርቶላት ነበር። ሰዎች ይህችን የፍቅር ጣዖት የሚያመልኩት እንዴት ነበር? ከቤተ ጣዖት ጋለሞታዎች ጋር ወሲብ በመፈጸም ነበር የሚያመልኳት። በቤተ ጣዖቱ ውስጥ ከ1000 የሚበዙ ጋለሞታዎች ይገኙ እንደነበር ይገመታል።

መ. ቆሮንቶስ እንደ አቴና ዓይነት የዩኒቨርስቲ ከተማ ባትሆንም፥ ፈላስፎችና የተማሩ ሰዎች አዳዲስ ፍልስፍናዎችን የሚወያዩበት ከተማ ነበረች።

ሠ. ምንም እንኳ ሰዎች ሁሉ ክፉዎች ቢሆኑም፥ ብዙ ሰዎች በሚሰባሰቡበት ጊዜ ክፋት ይጨምራል። በንግድ እምብርት ውስጥ ደግሞ ክፋት ገደቡን የሚያጣ ይመስላል። ቆሮንቶስ በሮም ግዛት ሁሉ ዋነኛ የክፋት ተግባራት መዲና ሆና ትታወቅ ነበር። እንዲያውም፥ አንድ ሰው የተበላሸ ወሲባዊ ባሕርይ በሚያሳይበት ጊዜ ሰዎች «ቆሮንቶሳዊ» ብለው ይጠሩት ነበር። በዚህች የክፋት ከተማ ነበር ወንጌሉ ሥር የሰደደው። ጳውሎስ አብዛኞቹ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች እንደ ሌላው ቆሮንቶሳዊ ሁሉ ጣዖትን በማምለክ፥ ግብረሰዶማዊነትን በማካሄድ፥ ወንድና ሴት የቤተ ጣዖታት ጋለሞታዎች በመሆን፥ በመስረቅ፥ በመስከር፥ ወዘተ... ኃጢአቶችን ያደርጉ እንደነበረ ገልጾአል (1ኛ ቆሮ. 6፡9-11)። የሚያሳዝነው ዛሬ ብዙ ሰዎች ክፉዎች ከሚመስሉ ሰዎች ይርቃሉ። ለመመስከር የምንፈልገው ለተከበሩት ሰዎች ብቻ ነው። ይህም የወንጌሉ ኃይል ሰዎችን ከሁሉም ዓይነት ክፋት ነፃ እንደሚያወጣና ክርስቶስም መንፈሳዊ በሽታ ያለባቸውን እንጂ ጤነኞችን ለመርዳት እንዳልመጣ መዘንጋታችንን ያሳያል (ማቴ. 9፡12)።

ጳውሎስ አብረውት የሚሠሩትን ሁለት ባልደረቦቹን (ጢሞቴዎስንና ሲላስን) በፊልጵስዩስና ተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ትቶ ወደ ቆሮንቶስ ሲሄድ

ጵርስቅላና አቂላ የተባሉትን ሁለት አይሁዶች አገኘ። ብዙውን ጊዜ ጳውሎስ አገልግሎቱን የሚጀምረው በምኩራብ ውስጥ ነበር። ብዙም ሳይቆይ ግን አይሁዶች በጳውሎስ ላይ በተቃውሞ በመነሣታቸው ምኩራቡን ትቶ በኢዮስጦስ ቤት ውስጥ ማገልገል ጀመረ። የአይሁድ የምኩራብ አለቃ የነበረውን ቀርስጶስ ጨምሮ አንዳንድ አይሁዶች ወደ ክርስቶስ ተመለሱ። በጃስተስ ቤት ውስጥ እያለ በአገልግሎቱ ላይ ለውጥ ተከሰተ። በዚህ ጊዜ በአሕዛብ ላይ ትኩረት በማድረጉ ብዙ ሰዎች ወደ ክርስቶስ መጡ። ይህ ለጳውሎስ ቀላል ጊዜ አልነበረም። ተስፋ በመቁረጡ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም እግዚአብሔር እንደሚጠብቀው በመግለጽ አዚያው ተግቶ እንዲያገለግል የሚያበረታታ ልዩ መልአክ ልኮለታል (የሐዋ. 18፡9-10)። ጳውሎስ ለ18 ወራት በቆሮንቶስ ከተማ ውስጥ ቆይቶ ሲመሰክር፥ ሲያስተምርና ቤተ ክርስቲያንን ሲመሠርት ሰነበተ። ቤተ ክርስቲያኒቱ እያደገች ስትሄድ የአይሁዶችም ቁጣ እንዲሁ ተጠናከረ። ጋሊዮስ በተባለ ገዢ ፊት ጳውሎስን ከሰሱት። ጋሊዮስ ፖለቲካዊ ያልሆነ ክስ ለመመርመር ባለመፈለጉ አይሁዶችን ከችሎቱ አስወጣቸው።

ከዚህ በኋላ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ሁለተኛውን የወንጌል መልእክተኝነት ጉዞውን ፈጸመ። ጳውሎስ በኢየሩሳሌምና አንጾኪያ ሳለ አጵሎስ የተባለ የንግግር ችሎታ ያለው ግለሰብ ከኤፌሶን ወደ ቆሮንቶስ መጣ። አጵሎስ በኤፌሶን ሳለ ከጵርስቅላና አቂላ በተሰጠው ምስክርነት በክርስቶስ አምኖ ነበር። እግዚአብሔር በቆሮንቶስ አጵሎስን በከፍተኛ ደረጃ ተጠቀመበት። የሚያሳዝነው ሰይጣን ሰዎች ስጦታውን ከሰጠው እግዚአብሔር ይልቅ በተቀበለው በአጵሎስ ላይ እንዲያተኩሩ ለማድረግ ቀልባቸውን ነጠቃቸው።

10ኛ ጥያቄ፦ ክርስቲያኖች ለሁሉም ስጦታዎችን ከሚሰጠው ክርስቶስ ይልቅ ከፍተኛ ስጦታ ባላቸው መሪዎች ወይም ዘማሪዎች ላይ ዓይኖቻቸውን የሚጥሉት እንዴት ነው?

አንዳንድ ምሁራን ጴጥሮስም (ኬፋ) ወደ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ለአጭር ጊዜ እንዳገለገለ ያስባሉ። ለዚህ ነበር በዚያ የነበሩ አንዳንድ ክርስቲያኖች ሊከተሉት የፈለጉት። ነገር ግን ጳውሎስ ወይም የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ የነበረው ሉቃስ እንዲህ ዓይነቱን ጉብኝት ሳይጠቅሱ ስለማያልፉ ትክክለኛ ግምት አይመስልም።

አጵሎስ በቆሮንቶስ ከሰበከ በኋላ ብዙም ሳይቆይ፥ ጳውሎስ ሦስተኛውን የወንጌል መልእክተኝነት ጉዞውን ጀመረ። ጳውሎስ በሦስተኛው ጉዞው በእስያና ኤፌሶን አካባቢ ትኩረት አድርጎ ለሁለት ዓመታት (አንዳንድ ምሁራን ከሞላ ጎደል ሦስት ዓመት ነበር ይላሉ) ሠርቷል። ጳውሎስ በዚህ ጊዜ ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ጋር የመልእክት ልውውጥ ጀምሮ ነበር። አጵሎስና ምናልባትም ጴጥሮስ በዚህ ጊዜ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩ አይመስልም። ጠንካራ አመራር ባለመኖሩ ምክንያት ችግሮች ተከሰቱ። ቤተ ክርስቲያኒቱም መከፋፈል ጀመረች። ጳውሎስ ከኤፌሶን ሆኖ ደብዳቤ በመጻፍ ችግሮቹን ለማስተካከል ሞከረ።

## ሁለተኛ ቀን፤ ጳውሎስ 1ኛ ቆሮንቶስን የጻፈበት ዘመንና ስፍራ

ምንም እንኳ ብዙዎቹ የጳውሎስ መልእክቶች የተጻፉባቸውን ቁርጥ ጊዜያት መናገሩ አስቸጋሪ ቢሆንም፥ 1ኛ ቆሮንቶስን የጻፈው በሦስተኛው የወንጌል መልእክተኝነት ጉዞ ኤፌሶን ውስጥ እያገለገለ ሳለ መሆኑ ግልጽ ነው። ጳውሎስ እስከ በዓለ ኀምሳ ድረስ በኤፌሶን እንደሚቆይና ከዚያ በኋላ ቆሮንቶሶችን እንደሚጎበኝ ተናግሯል (1ኛ ቆሮ. 16፡8፥19፤ በተጨማሪም የሐዋ. 19፡10ን አንብቡ።) ይህም የ1ኛ ቆሮንቶስ መልእክት የተጻፈው ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያኒቱን ከተከለ ከ5 ዓመታት በኋላ በ55 ዓ.ም መሆኑን ያሳያል።

## ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ የጻፋቸው መልእክቶችና ያደረጋቸው ጉብኝቶች ቅደም ተከተል

ምሁራን ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ባደረጋቸው ጉብኝቶችና በተለይም በጻፋቸው የተለያዩ መልእክቶች ቅደም ተከተል ላይ ይከራከራሉ። ጳውሎስ በኤፌሶን ላይ ባተኮረበት በሦስተኛው የወንጌል መልእክተኝነት ጉዞው ወቅት አራት የተለያዩ መልእክቶችን የጻፈ ይመስላል።

በመጀመሪያ፥ ጳውሎስ በኤፌሶን ሳለ አንድ መሠረታዊ የመጀመሪያ መልእክት ሳይጽፍ እንዳልቀረ ብዙ ምሁራን ያምናሉ (1ኛ ቆሮ. 5፡9)። ይህ መልእክት ጠፍቷል። ጳውሎስ በዚህ የመጀመሪያ መልእክቱ ስለ ግብረገባዊ ንጽሕና ሳያስተምር አልቀረም። የቆሮንቶስ ሰዎች ንጹሕ ግብረገባዊ ሕይወት ከሌላቸው ሰዎች ጋር ኅብረት እንዳያደረጉ አሳስቧቸዋል (1ኛ ቆሮ. 5፡9)። ክርስቲያኖቹ የጳውሎስን አሳብ በተሳሳተ መንገድ በመረዳት ይህ ማለት አምልኮተ ጣዖት ከሚያካሂዱና ግብረገባዊነት የጎደለው የወሲብ ግንኙነት ከሚፈጽሙ ዓለማውያን ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት አለማድረግን ያሳያል ብለው አሰቡ። የክርስቲያኖች ከዓለማውያን ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት አለማድረግ መልካም ውጤት የሚያስገኝ ነገር አልነበረም። እንደዚያ ከሆነ፥ ለማያምኑ ሰዎች መስክረው ወደ ክርስቶስ የሚመልሷቸው እንዴት ነው? ጳውሎስ የሚናገረው ለክርስቶስ ለመገዛትና የእግዚአብሔርን ሕግጋት ለመከተል ከማይፈልጉ ክርስቲያኖች ጋር ኅብረትን ስለማድረግ ነበር። ጳውሎስ አማኞችን ወደ ንስሐ ለመምራትና ለመቅጣት በማሰብ እነዚህ ግብረ ገባዊነት የጎደላቸው ክርስቲያኖች ከክርስቲያናዊ ኅብረት እንዲገለሉ ነበር የተናገረው። የዚህም ቅጣት ዓላማ አማኞቹ አፍረው በኃጢአት ከተሞላው አኗኗራቸው እንዲመለሱ ለመርዳት ነበር።

እንደ ቆሮንቶስ ሰዎች ሁሉ፥ ዛሬም ብዙ ክርስቲያኖች በግልጽ ኃጢአት ከሚመላለሱ ሰዎች ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት እንደሚያደርጉ ይቸገራሉ። ኃጢአትን እየፈጸሙ የሚኖሩትን ክርስቲያኖች ወደ መታገሡ እናዘነብላለን። ክርስቲያኖች ካልሆኑና በክርስቲያናዊ ማኅበረሰብ ውስጥ ለመኖር ከሚፈልጉት ክርስቲያኖች ደግሞ ራሳችንን እናገላለን። ብዙውን ጊዜ ምስክርነታችን ደካማ የሚሆነውና ብዙ ዓለማውያን ወደ ክርስቶስ የማይመጡት ለዚህ ነው።

11ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቀዳሚነት ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ብቻ ኅብረት ለማድረግ ክርስቲያኖች (በተለይም የክርስቲያኖች ልጆች) ዝንባሌ ማሳየታቸውን እንዴት እንደታዘብህ ግለጽ። ለ) ይህ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያስከተለው አሉታዊ ውጤት ምንድን ነው?

ሁለተኛ፥ ጳውሎስ ሊጎበኙት ከመጡት የቆሮንቶስ አማኞች በመካከላቸው ስለነበረው ክፍፍል ከሰማና ቤተ ክርስቲያኒቱ የተወሰኑ ጥያቄዎችን በማንሣት የላከችለትን ደብዳቤ ካነበበ በኋላ፥ ሁለተኛውን መልእክት ጻፈ። ይህም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተካትቶ የምናገኘው የ1ኛ ቆሮንቶስ መልእክት ነው። ጳውሎስ አጵሎስ ወደ ቆርንቶስ ተመልሶ ችግሮችን እንዲፈታ ቢጠይቀውም ፈቃደኛ ሊሆን አልቻለም (1ኛ ቆሮ. 16፡12)። ስለሆነም፥ ጳውሎስ በሌሎች ሰዎች፥ ምናልባትም ሊጎበኙት በመጡት የቀሎዔ ቤተ ሰዎች አማካኝነት ደብዳቤውን ላከላቸው።

ሦስተኛ፥ ጳውሎስ መልእክቱን ከጻፈ በኋላ አንዳንድ ችግሮች እርሱ በፈለገበት መንገድ ሳይሄዱለት የቀሩ ይመስላል። ስለሆነም፥ ጳውሎስ ለአጭር ጊዜ ጉብኝት ወደ ቆርንቶስ ሄደ። ጳውሎስ ይህንን ጉብኝት «የሥቃይ ጉብኝት» ብሎታል (2ኛ ቆሮ. 2፡1)። ወደ ኤፌሶን ከተመለሰ በኋላ፥ «የኃዘን ደብዳቤ» የተባለ ሌላ መልእክት ጽፎ በቲቶ በኩል ሰደደ (2ኛ ቆሮ. 2፡4፤7፡8-9)። (አንዳንድ ምሁራን ይህ የ1ኛ ቆሮንቶስን መልእክት ያመለክታል ይላሉ። ሌሎች ግን በዚህ መልእክት ውስጥ ብዙ ኃዘን እንደሌለ በመግለጽ፥ ጳውሎስ አሁን በእጃችን ስለሌለ መልእክት እየተናገረ ሳይሆን አይቀርም ይላሉ።)

አራተኛ፥ ጳውሎስ የኤፌሶን አገልግሎቱን ከፈጸመ በኋላ ወደ ቆሮንቶስና ኢየሩሳሌም አመራ። ይህንንም ያደረገው በሁለተኛው የወንጌል መልእክተኝነት ጉዞው የመሠረታቸውን አብያተ ክርስቲያናት በእግር እየተጓዘ በመጎብኘት በመቄዶንያ በኩል በማለፍ ነበር። በተጨማሪም፥ አብያተ ክርስቲያናት በኢየሩሳሌም ለሚገኙ ድሆች ክርስቲያኖች እንዲሰጥ ያዋጡትን ገንዘብ ሰብስቧል። ጳውሎስ በመቄዶንያ ሳለ፥ ቲቶ ከቆሮንቶስ ተመልሶ ስለ ቆሮንቶስ ክርስቲያኖች መለወጥ ገለጸለት (2ኛ ቆሮ. 7፡5-7)። ጳውሎስም በአመስጋኝነት በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ የሚገኘውን የሁለተኛ ቆሮንቶስን መልእክት ጻፈ።

ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ደርሶ በጋውን (3 ወራት ያህል) እዚያው አሳለፈ። ከዚያም የአሕዛብ ክርስቲያኖች ለአይሁድ ክርስቲያኖች ያዋጡትን ገንዘብ ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ።

## የ1ኛ ቆሮንቶስ መልእክት ዓላማ

ጳውሎስ በአብዛኞቹ ሌሎች መልእክቶቹ ውስጥ እንደሚያደርገው፥ በ1ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ ለሥነ መለኮታዊ እውነቶች ትኩረት አልሰጠም። በመሆኑም፥ መጽሐፉን በሥነ መለኮታዊና ተግባራዊ ክፍሎች አልከፈለም። (ይህም ከሮሜና ከኤፌሶን መልእክቶች የተለየ ነው።) በ1ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለሚያጋጥሟት ችግሮች መፍትሔ በመጠቆሙ ሂደት ላይ ሁሉንም ሥነ መለኮታዊና ተግባራዊ እውነቶች ይዳስሳል።

ጳውሎስ በንድፈ ሐሳባዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር የሥነ መለኮት ምሁር ሳይሆን፥ አማኞች እንደ ክርስቶስ ተከታዮች በእውነት ላይ ተመሥርተው እንዲኖሩ የሚሻ አገልጋይ ነበር። ጳውሎስ 1ኛ ቆሮንቶስን ከጻፈባቸው ምክንያቶች አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. የመንፈሳዊ ብስለትን ምንነት ለማስረዳት። መንፈሳዊ ትኩሳት ወይም የጸጋ ስጦታዎች አንድ ክርስቲያን ወይም ቤተ ክርስቲያን በሳልና መንፈሳዊ ጤንነቱ የተሟላ መሆኑን በትክክል አያመለክቱም። ጳውሎስ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ከፍተኛ የጸጋ ስጦታዎች እንደነበሯቸው መስክሯል። (1ኛ ቆሮ. 1፡5-7 አንብብ።) ነገር ግን ከሌሎች ጥንታዊያን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የባሰ መንፈሳዊ ትግል አድርገዋል። ስለዚህ ጳውሎስ ለእነዚህ ላልበሰሉና መንፈሳዊያን ላልሆኑ ክርስቲያኖች እንደ ክርስቶስ እንዴት ሊኖሩ እንደሚገባቸው በደብዳቤው ገለጸላቸው (1ኛ ቆሮ. 3፡1-4)። የአንድ ሰው ችሎታ ወይም መንፈሳዊ ስጦታዎች መንፈሳዊነቱን ሊገልጹ እንደማይችሉ ጳውሎስ አካፍሎአል። ይልቁን የአንድ ሰው መንፈሳዊ ብስለት ምልክቱ አንድነት፥ ፍቅርና ለሌሎች ክርስቲያኖች ግድ የሚለው ሲሆን ነው። ጳውሎስ የተወሰኑ ችግሮችን ማለትም እንደ መከፋፈልና ልቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በተመለከተ ከቤተ ክርስቲያን በደረሰው መረጃ መሠረት መንፈሳዊ ብስለት ምን እንደሆነና መንፈሳዊ ብስለት ያላቸው ሰዎች እንዴት መመላለስ እንደሚገባቸው ለማስረዳት ይጥር ነበር።

> 12ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዛሬ ምን ያህል ክርስቲያኖች እንደ ልሳንን የመሳሰሉትን መንፈሳዊ ስጦታዎች እንዴት እንደ ዋነኛ የመንፈሳዊ ብስለት ምልክቶች አድርገው እንደሚወስዱና አንድነት፥ ፍቅር፥ ንጽሕና በመሳሰሉት መንፈሳዊ ባሕርያት ላይ እንደማያተኩሩ ግለጽ። ለ) በተወሰኑ መንፈሳዊ ስጦታዎች ላይ ትኩረት ማድረጉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነት፥ ፍቅር፥ መንፈሳዊነትና ቅድስና እንዲጨምር አስተዋጽኦ ያደረገ ይመስልሃል? ለምን?

2. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታዩትን ትክክለኛ ያልሆኑ አስተምህሮዎችና ተግባራት ለማረም። ጳውሎስ በኤፌሶን በሚያገለግልበት ጊዜ የተለያዩ ክርስቲያኖች ሊጎበኙት ከቆሮንቶስ መጥተው ነበር። የቀሎዔ ቤተ ሰዎች በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ስለነበረው ክፍፍል ነግረውታል (1ኛ ቆሮ. 1፡11)። ሦስት ቁልፍ የቆሮንቶስ መሪዎች ለጳውሎስ የተወሰነ ገንዘብና ደብዳቤ አምጥተውለታል። ምናልባትም በቆሮንቶስ ስለነበረው ሁኔታ ዝርዝር ያለ መረጃ ሳይሰጡት አልቀሩም። ስሞቻቸውም እስጢፋኖስ፥ ፈርዶናጥስና አካይቆስ ይባል ነበር (1ኛ ቆሮ. 16፡17)። (ምሁራን እነዚህ ሦስት ሰዎች የቀሎዔ ቤተ ሰዎች ይሁኑ ወይም ሌሎች በርግጠኝነት አያውቁም። አብዛኛዎቹ ግን ከሌላ ወገን ናቸው ይላሉ።) ኤፌሶን ከቆሮንቶስ በጀልባ ለመሄድ ከ300 ኪሎ ሜትሮች በላይ ስለሚርቅና ጳውሎስም በኤፌሶን የጀመረውን አገልግሎት ለማቋረጥ ባለመቻሉ፥ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን ችግሮች ለመፍታት ይህን ጠቃሚ መልእክት ጽፎላቸዋል። ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ ያነሣቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚከፋፍሉ ዐበይት ችግሮች ነበሩ። ክርስቲያኖች በክርስቶስ የነበራቸውን አንድነት ዘንግተው በሕይወታቸው ላይ

ለውጥ ያመጡትን ወይም ጠቃሚዎች ናቸው ብለው ያሰቧቸውን የተለያዩ መሪዎች ይከተሉ ነበር (1ኛ ቆሮ. 1፡11-12)።

ለ. የጳውሎስን የሐዋርያነት ሥልጣን የሚጠራጠሩ ሰዎች ነበሩ። ስለሆነም፥ ጳውሎስ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን የሚናገር ሐዋርያ መሆኑን ገልጾላቸዋል። ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ መልእክቱ ስለዚህ ጉዳይ የበለጠ ያስተምራል።

ሐ. ጳውሎስ ምእመናን ግልጽ ወሲባዊ ርኩሰት እንደሚፈጽሙና መሪዎችም በኃጢአት ላይ አቋም ከመውሰድ ይልቅ የግልጽነትና የቸርነት ምልክት ነው በሚል የተሳሳተ ግምት ኃጢአት ሳይቀጣ እንዲቀር ያደርጉ እንደነበር ሰማ።

መ. በተጨማሪም፥ አንዳንድ ክርስቲያኖች ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በሚጋጩበት ጊዜ ወደ ፍርድ ቤት ይወስዱቸው እንደነበር ሰምቶ ነበር።

ሠ. በጌታ እራት ጊዜ ሰዎች የሚበሉት የሌሏቸውን ድሆች ቸል እያሉ በራስ ወዳድነት ይበሉና ይጠጡ ነበር።

ረ. ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ጥያቄዎች መልስ ሰጥቷል። እነዚህም ጥያቄዎች፥ 1) ክርስቲያን ማግባት አለበት ወይስ በላጤነት መኖር አለበት? 2)ክርስቲያን ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ ከገበያ ገዝቶ መብላት ይችላል? 3) ሴቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጡ አለባበሳቸው ምን ዓይነት መሆን አለበት? 4) በልሳን መናገር ክርስቲያኖች ሁሉ ሊፈልጉት የሚገባ እጅግ አስፈላጊ ስጦታ ነው ወይስ ሊከለከል ይገባል? 5) ክርስቲያኖች ከሞት ሊነሡ ይችላሉ? 6) ለኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች የሚወሰደው ገንዘብ እንዴት መሰብሰብ አለበት?

---

13ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ከእነዚህ ጉዳዮች ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግር እየፈጠረ ያለው የትኛው ነው? ለ) ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች የጳውሎስን መልስ መረዳቱ ጠቃሚ የሚሆነው ለምንድን ነው?

---

ምሁራን 1ኛ ቆሮንቶስ የጥንቱ ቤተ ክርስቲያን ላጋጠማት ችግር ጥሩ ምሳሌ እንደሆነች ያምናሉ። ምንም ወይም ጥቂት የብሉይ ኪዳን ግንዛቤ የነበራቸው አሕዛብ ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚመጡበት ጊዜ፥ የራሳቸውን ባሕላዊ ግንዛቤ ይዘው ነበር የመጡት። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በሁሉም ባሕሎች ላይ በመፍረድ ወደ ራሱ ይመልሳቸዋል እንጂ ራሱን ከየትኛውም ባሕል ጋር አያስማማም። ጳውሎስ ምእመናን እንደ ዓለም አባላት ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር መንግሥት አባላት መመላለስ እንዳለባቸው በመግለጽ ያስተላለፈው ትምህርት ከቆሮንቶስ ሰዎች ባሕል ያፈነገጠ ነበር።

ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለነበሩት ጉዳዮችና ችግሮች እንዴት መልስ እንደሰጠ አጢን። ለጳውሎስ «እንዲህ አድርጉ አታድርጉ» የሚሉ የትእዛዛት ዝርዝር መስጠት ይቀለው ነበር። ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ችግሮችን የሚያስተናግዱት በዚህ መንገድ ነው። ትልቁን ግንዛቤያቸውን በመጠቀም፥ ሰዎች እንዲከተሉ የሚፈልጓቸውን ዝርዝር ደንቦች ያወጣሉ። (ወደ ሲኒማ ቤት አትሂዱ፤ ጫት አትቃሙ፤ ፋሽን ልብስ አትልበሱ፤ የከንፈር ቀለም አትቀቡ) የሚሉትን ዓይነት ትእዛዛት ይሰጣሉ። ምንም እንኳ ብዙ

ሰዎች የዚህ ዓይነቱን ክርስትና ቢመርጡም፥ ይህ አደገኛ ልምምድ ነው። ሰይጣን እንደዚህ ዓይነት ሰው ሠራሽ ደንቦችን በመጠቀም ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ሳያደርጉና ውስጣዊ ለውጥ ሳያካሂዱ በውጫዊ ደንቦች ላይ እንዲያተኩሩ ይገፋፋቸዋል።

ጳውሎስ ግን ለችግሮቹ ምላሽ የሰጠው በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ሊያገለግሉ የሚችሉትን መርሆች በማቅረብ ነበር። ክርስቲያኖች በፍርድ ቤት የማይካሰሱት ለምንድን ነው? አንድ ክርስቲያን ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ መብላት ያለበት ወይም የሌለበት ለምንድን ነው? በልሳን መናገር የሚከለከለውና የሚፈቀደው ለምንድን ነው? የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የፈለጉት ዝርዝር ትእዛዛትን ነበር። ጳውሎስ ግን በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ክርስቲያኖች ሊያገለግሉ የሚችሉትን አመለካከቶች ሰጥቷቸዋል። ለክርስቲያኖች የሚያስፈልጉት ፍቅርና አንድነት መሆናቸውን አመልክቷል። ራስ ወዳድነት፥ ሌሎችን ከመረዳት ይልቅ የራስን መብት ለማስከበር የሚደረግ ጥረት ሁሉ ትክክል አይደለም። ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለንን ግንኙነት የማያደናቅፍ ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ነጻነት አለን።

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ፡- በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የሚገኝ አንድ ችግር ግለጽ። ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደንቦችን በማውጣት ለችግሩ እልባት ሊሰጡ የሚችሉበትን ሁኔታ በምሳሌ ግለጽ። ለ) መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ በመፈለግ ችግሩን መፍታት የሚቻለው እንዴት ነው? ሐ) ችግሩን ለመፍታት የትኛው መንገድ ይሻላል? ለምን? |

ሌላው በሕግጋትና በደንቦች ላይ ተመሥርቶ ችግሮችን መፍታት ከሁሉም የተሻለ አማራጭ የማይሆንበት ምክንያት፥ ችግሮች ሁልጊዜም የሚለዋወጡ በመሆናቸው ነው። በአንድ ዘመን ተቀባይነት ያልነበራቸው ነገሮች በሌላው ዘመን ተቀባይነት ያገኛሉ (ለምሳሌ፥ ከበሮዎችን ለአምልኮ ዝማሬ መጠቀም)። በአንድ ባሕል ተቀባይነት የሌለው ነገር በሌላው ባሕል ተቀባይነት ይኖረዋል (ለምሳሌ፥ የአሳማ ሥጋ መብላት)። ነገር ግን ሁልጊዜም የምንጋፈጣቸው ችግሮች አሉ። ብዙ ዓይነት ችግሮችን ለመፍታት የሚያገለግሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆችን በማቅረብ ለአንድ ጉዳይ መፍትሔ በምንሰጥበት ጊዜ መፍትሔው ወደፊት ለሚከሰቱት ሌሎች ችግሮችም የሚሠራ ሆኖ እናገኘዋለን።

3. <u>ወንጌልን የተቃወሙትን ወይም በተሳሳተ መንገድ የተረዱትን ለማረም</u>። እግዚአብሔር አንድን ክርስቲያን መሪ በከፍተኛ ደረጃ በሚጠቀምበት ጊዜ ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚቃወሙት ሰዎች ይነሣሉ። ይህ እውነት በሐዋርያው ጳውሎስ ላይ ደርሷል። በሚሄድበት ስፍራ ሁሉ ከማያምኑ አይሁዶች ተቃውሞ ይደርስበት ነበር። ስለ ክርስትና ከጳውሎስ የተለየ አመለካከት የነበራቸው የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ሰዎችም ተቃውመውታል። ለምሳሌ ያህል፥ አንዳንድ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች አሕዛብ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት መገረዝና የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን መጠበቅ እንደሚገባቸው በመግለጽ የጳውሎስን ትምህርት እንደተቃወሙ ከመልእክቶቹ እንረዳለን።

1ኛ ቆሮንቶስ በተጨማሪም የጳውሎስን ትምህርቶች ስለሚቃወሙት ወይም ከራሳቸው አሳብ ጋር እንዲሄድላቸው ስለሚያጣምሙ የተለያዩ ቡድኖች ያስረዳል። በመጀመሪያ፥ አንድ ሰው የፈለገውን (ኃጢአትንም ጨምሮ) ሊያደርግ እንደሚችል በመግለጽ በክርስቲያኑ ነጻነት ላይ የሚያተኩሩ ነበሩ። «በሥጋችን ላይ የምናደርገው ነገር በነፍሳችን ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ አይኖርም። ትክክል ካልሆነ ደግሞ በኋላ ይቅርታ ልንጠይቅ እንችላለን» ብለው ያስቡ ነበር። በ1ኛ ቆሮንቶስ 5 በወሲብ ኃጢአት ውስጥ የነበረውን ክርስቲያን ለመቅጣት ያልፈለጉት ከዚሁ ስለ ቅድስናና ይቅርታ ከነበራቸው የተሳሳተ ግንዛቤ ሳቢያ ሳይሆን አይቀርም። ሁለተኛ፥ ሌሎች ደግሞ ክርስትና የምንኩስና ዓይነት የአኗኗር ስልት ሊከተል ይገባል ብለው ያስባሉ። ትዳር አለመመሥረትና፥ ከሥጋ ይልቅ አትክልቶችን መመገብ አንድን ሰው የተሻለ ክርስቲያን ያደርገዋል ብለው ያስባሉ (2ኛ ቆሮ. 2፡20-23)። ሦስተኛ፥ አንዳንዶች ደግሞ መንፈስ ቅዱስ የሰጣቸው የልሳን ስጦታ ከሁሉም በላይ አስፈላጊ ስጦታ እንደሆነ ከማመናቸውም በላይ፥ ለአምልኮ በሚሰባሰቡበት ጊዜ የበለጠ ስሜታዊ ከሆኑ የሌሎችን አምልኮ ቢረብሽም እንኳን አምልኳቸው የተሻለ እንደሚሆን ያስቡ ነበር። ጳውሎስ አማኞች ወንጌሉን፥ እውነተኛውን መንፈሳዊነትና ሁልጊዜም ፍቅር ማሳየትን ይረዱ ዘንድ የእነዚህን የተለያዩ ቡድኖች የተዛቡ አመለካከቶች ለማስተካከል ጥረት አድርጓል።

## የ1ኛ ቆሮንቶስ ልዩ ባሕርያት

1. አብዛኛው የ1ኛ ቆሮንቶስ ክፍል የተለመደው ዓይነት ደብዳቤ ሳይሆን ችግሮችን የሚያንጸባርቅ ሆኖ እናገኘዋለን። ስለሆነም፥ ከዳር እስከ ዳር ጎልቶ የሚታይ ጭብጥ ከመያዝ ይልቅ (የሮሜ መልእክት በደኅንነት ላይ እንደሚያተኩር)፥ የቆሮንቶስ መጽሐፍ በቤተ ክርስቲያኒቱ ችግሮችና ጥያቄዎች ላይ ያተኩራል።

2. 1ኛ ቆሮንቶስን ማንበብ አንድ ሰው በስልክ ሲነጋገር እንደ መስማት ነው። ከአጠገባችን ያለው ሰውዬ የሚናገረውን ልንሰማ ብንችልም፥ ከሌላኛው የስልኩ ጫፍ ያለው ግለሰብ የሚያነሣቸውን ጥያቄዎች ወይም ሃሳቦች ልንሰማ አንችልም። ስለሆነም፥ የዚያ ሰውዬ ጥያቄዎችና የነበረበት ሁኔታ ምን ዓይነት እንደሆኑ መገመት ይኖርብናል። በ1ኛ ቆሮንቶስ፥ ጳውሎስ ለቆሮንሮስ ክርስቲያኖች ችግሮች የሰጣቸውን መልሶች ብንመለከትም፥ ችግሮቹ የተነሡባቸውን ዝርዝር ሁኔታዎች ግን አናውቅም። ለምሳሌ፥ ጳውሎስ ሴቶች በቤተ ክርስቲያን እንዳይናገሩ ወይም ራሶቻቸውን እንዲከናነቡ ያዘዘው ለምን ነበር? ይህ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ አንድ ችግር እንደነበረ ቢያሳይም፥ በትክክል ምን እንደሆነ አናውቅም። ጳውሎስ ምላሽ የሚሰጠው ለእንደነዚህ ዓይነት በጊዜው ለተከናወኑ ዝርዝር ጉዳዮች በመሆኑ፥ ይህን ክፍል በምንተረጉምበትና ከቤተ ክርስቲያናችን ጋር በምናዛምድበት ሁኔታ ላይ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል። ዛሬ የምንጋፈጣቸው ችግሮች ከቆሮንቶስ የተለዩ ሊሆኑ ስለሚችሉ፥ የጳውሎስ ዝርዝር ትምህርቶች ከዛሬው ሁኔታችን ጋር እንደሚስማሙ ከመገመት ይልቅ መርሆችን መፈለግ ይኖርብናል። ለምሳሌ፥ ዛሬ ሴቶች ጸጉራቸውን

መሸፈናቸው የተለየ ዓላማ ካለውና በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተከሰተውን ዓይነት ሁኔታ የማያስከትል ከሆነ፥ ዛሬም ይህንኑ ደንብ መከተል አለብን? ብዙ ክርስቲያኖች የለብንም ይላሉ።

## የ1ኛ ቆሮንቶስ መዋቅር

የ1ኛ ቆሮንቶስ መልእክት በሁለት ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል። በመጀመሪያ፥ ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ሊጎበኙት ከመጡት ሰዎች የሰማቸውን ጉዳዮች በማስመልከት ከምዕራፍ 1-6 ያለውን አሳብ ጽፎአል። ጳውሎስ ከዚህ ቃላዊ ዘገባ ተነሥቶ ስለ ክፍፍል፥ በጥበብ ላይ ስለሚደረግ የተጋነነ ትኩረት፥ ስለ ራሱ ሐዋሪያዊ ሥልጣን፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚታይ ወሲባዊ እርኩሰትና ስለ አማኞች መካሰስ ምላሽ ሰጥቷል።

| |
|---|
| 15ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ቆሮ. 1፡11፥ 19፤ 5፡1፤ 6፡1፤ 7፡1፤ 8፡1፤ 11፡3፤ 12፡1፤ 15፡1፤ 16፡1 አንብብ። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የዘገባና የደብዳቤ ምላሽ በመስጠት ያነሣቸውን ጉዳዮች ዘርዝር። |

ሁለተኛ፥ 1ኛ ቆሮንቶስ 7-16 የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ለጳውሎስ ባቀረቧቸው የተወሰኑ ጥያቄዎች ላይ ያተኩራል። (1ኛ ቆሮ.7፡1 አንብብ።) ጳውሎስ አዲስ ጉዳይ በሚጀምርበት ጊዜ «ስለ . . .» የሚል መስተዋድድ ስለሚጠቅም (1ኛ ቆሮ. 7፡1፥ 25፤ 11፡3፤ 12፡1፤ 16፡1)፥ የቤተ ክርስቲያኒቱን ጥያቄዎችና መልሶች በቀላሉ መለየት ይቻላል። ጳውሎስ በምላሹ ስለ ጋብቻ፥ ለጣዖት የተሠዋን ሥጋ ስለ መብላት፥ ስለ ሴቶች አለባበስ፥ ስለ ቅዱስ ቊርባን፥ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች፥ ስለ አማኞች ትንሣኤና በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ድሆች ስለሚሰጠው እርዳታ አብራርቷል።

## የ1ኛ ቆሮንቶስ ርእሰ ጉዳዮች

1. መግቢያ (1ኛ ቆሮ. 1፡1-9)
2. ክፍል አንድ፤ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳሉ የተገለጹ ችግሮች (1ኛ ቆሮ. 1፡10-6፡20)
   - ሀ. የመጀመሪያው ችግር፤ የቤተ ክርስቲያን ክፍፍል (1ኛ ቆሮ. 1፡10-4፡21)
     1. ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ክፍፍል የመኖሩን እውነታ ያስተዋውቃል (1ኛ ቆሮ. 1፡10-17)
     2. ስለ ዓለማዊ ጥበብና በክርስቶስ መስቀል በተገለጠው የመንፈሳዊ ጥበብ መካከል ያለውን ልዩነት ጥርት አድርጎ አለማወቅ ክፍፍልን ያስከትላል (1ኛ ቆሮ. 1፡18-2፡14)
     3. የተለያዩ ሰዎችን ከመከተል የሚመጣው ክፍፍል መሪዎችን እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች የሚያበረክቱትን ድርሻ በተሳሳተ መንገድ እንድንረዳ ያደርጋል (1ኛ ቆሮ. 3)
     4. የሐዋርያነትን ምሳሌነት በመከተል ክፍፍልን ማሸነፍ (1ኛ ቆሮ. 4)

ለ. ሁለተኛው ችግር፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተከሰተ የሥነ ምግባር ብልሹነት (1ኛ ቆሮ. 5፡1–12)

ሐ. ሦስተኛው ችግር፤ የአማኞች በችሎት ፊት መካሰስ (1ኛ ቆሮ. 6፡1–8)

መ. ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚከሰት ወሲባዊ ኃጢአት ያቀረበው ተጨማሪ ትምህርት (1ኛ ቆሮ. 6፡9–20)።

3. ክፍል ሁለት፤ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ጥያቄዎች የሰጣቸው መልሶች (1ኛ ቆሮ. 7፡1–16፡4)።

ሀ. 1ኛ ጥያቄ፡– ክርስቲያን ሊያገባ ወይስ ብቻውን ሊኖር ይገባል? (1ኛ ቆሮ 7)

ለ. ሁለተኛ ጥያቄ፡– ክርስቲያን ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ ሊበላ ይገባል (1ኛ ቆሮ. 8–11፡1)

1. የመብላት ነጻነት ለሌሎች ክርስቲያኖች ባለን ፍቅር መወሰን አለበት (1ኛ ቆሮ. 8)

2. ጳውሎስ ነጻነትን ስለ መገደብ ከራሱ ሕይወት የሰጠው ምሳሌ (1ኛ ቆሮ. 9)

3. ከብሉይ ኪዳን እስራኤላውያን ታሪክ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (1ኛ ቆሮ. 10፡1–13)

4. በምግብ አማካኝነት የጣዖት አምልኮ ተካፋይ እንዳይሆኑ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (1ኛ ቆሮ. 10፡14–22)።

5. ክርስቲያን ለሌላው ክርስቲያን ካለው ፍቅር የተነሣ ከምግብ ለመታቀብ ወይም ምግብ ለመብላት ስለሚኖረው ነጻነት ጳውሎስ የሰጣቸው ዝርዝር መመሪያዎች (1ኛ ቆሮ. 10፡23–11፡1)።

ሐ. ሦስተኛ ጥያቄ፡– ወንዶችና ሴቶች በአምልኮ ስብሰባ ላይ ምን ዓይነት ልብስ መልበስ ይኖርባቸዋል? (1ኛ ቆሮ. 11–14)

መ. አራተኛ ጥያቄ፡– በቅዱስ ቁርባን ላይ ሊኖር የሚገባው ትክክለኛ አመለካከት ምንድን ነው? (1ኛ ቆሮ. 11፡17–34)።

ሠ. አምስተኛ ጥያቄ፡– የመንፈሳዊ ስጦታዎች፥ በተለይም የልሳን ዓላማ ምንድን ነው? (1ኛ ቆሮ. 12–14)።

1. ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ይውሉ ዘንድ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን የሚሰጡ የተለያዩ ስጦታዎች አሉ (1ኛ ቆሮ. 12)።

2. መንፈሳዊ ስጦታዎችን የምንጠቀምበት ዓላማ ፍቅርና ለሌሎች ክርስቲያኖች ማሰብ ሊሆን ይገባዋል (1ኛ ቆሮ. 13)።

3. ትንቢት በልሳን ከመናገር ለምን እንደሚሻል (1ኛ ቆሮ. 14፡1–12)።

4. ስለ ልሳን፥ ትንቢትና በጉባዔ ውስጥ ስለሚደረግ የሴቶች ንግግር የተሰጠ መመሪያ (1ኛ ቆሮ. 14፡13–40)።

ረ. ስድስተኛ ጥያቄ፡- አንድ አማኝ ከሞተ በኋላ ሥጋው ምን ይሆናል? (1ኛ ቆሮ. 15)

ሰ. ሰባተኛ ጥያቄ፡- የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች አይተዋቸው ለማያውቋቸው የአይሁድ ክርስቲያኖች ገንዘብ መስጠት ያለባቸው ለምንድን ነው? (1ኛ ቆሮ. 6፡1-4)

4. መደምደሚያ፡- (1ኛ ቆሮ. 16፡5-21)

## ሦስተኛ ቀን 1ኛ ቆሮንቶስ 1-3

16ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡1-3፡16 አንብብ። ሀ) ጳውሎስ የቆሮንቶስ አማኞችን ያመሰገናቸው ለምን ነበር? በችግሮች ተከብበን ባለንበት በአሁኑ ሰዓት ይህ እንዴት ያጽናናል? ለ) በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ክፍፍሎችን ያስከተለው ምንድን ነው? ዛሬ በቤተ ክርስቲያኖቻችን በተመሳሳይ ሁኔታ ክፍፍል የሚከሰተው እንዴት ነው? ሐ) የዓለምን ጥበብ ከእግዚአብሔር ጥበብ ጋር አነጻጽር። ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለተከሰተ ክፍፍል እየተናገረ ሳለ ስለ «ጥበብ» ያነሣው ለምን ይመስልሃል? መ) ጳውሎስ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቤተ ክርስቲያንን ለመሥራት ስለሚያበረክቱት ሚና ምን አለ? እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን መሪ ስለ አሠራሩ ምን ማስታወስ አለበት?

## መግቢያ፡- (1ኛ ቆሮ. 1፡1-9)

1. ጳውሎስ የመጽሐፉ ደራሲ መሆኑን ይናገራል (1ኛ ቆሮ. 1፡1)። ሰላምታው በእግዚአብሔር የተመረጠ ሐዋርያ መሆኑን ያመለክታል። ጳውሎስ የክርስቶስ ወኪል ሆኖ ስለሚናገር፥ የቆሮንቶስ አማኞች በጥንቃቄ ሊሰሙት ይገባ ነበር። ምሁራን የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ይህንን መልእክት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ማካተቷ ጳውሎስ የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ ሆኖ መናገሩን እንደሚያሳይ ያስረዳሉ።

2. ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን መጻፉን ገልጾአል (1ኛ ቆሮ. 1፡2-3)። ብዙውን ጊዜ የጳውሎስ መግቢያ የደብዳቤውን ትኩረት ያሳያል። ለዚህም ነው በሮሜ መልእክቱ ወንጌል ላይ ያተኮረው። በዚህ ክፍል ጳውሎስ የመልእክቱ ዓላማ ስለ ቅድስና ማብራራት እንደሆነ ገልጾአል። እግዚአብሔር በክርስቶስ የሚያምኑትን ሁሉ ቅዱሳን ብሎአቸዋል። ይሁንና፥ በአኗኗራችን ይህንኑ ቅድስና ማሳየት አለብን።

3. ጳውሎስ የቆሮንቶስን አማኞች ያመሰግናቸዋል (1ኛ ቆሮ. 1፡4-9)። አብዛኛዎቹ ጥንታዊ ደብዳቤዎች የሚጀምሩት በምስጋና ወይም ጸሐፊው ስለ አንባቢዎቹ እንደሚያስብ በሚያሳዩ ቃላት ነበር። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ችግሮች ቢኖሩም ጳውሎስ ተስፋ አልቆረጠም ነበር። በአንጻሩ ጳውሎስ እግዚአብሔርን በቆሮንቶስ አማኞች ሕይወት ውስጥ ስለሚሠራው ሥራ ያመሰግነዋል። እግዚአብሔርን ያመሰገነባቸው ምክንያቶችም የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. ለቆሮንቶስ ቤተ ክርቲያን ስለ ሰጠው ብዙ በረከት። ምንም እንኳ አማኞቹ ከእነዚህ ስጦታዎች ብዙዎቹን ተገቢ ባልሆነ መንገድ ቢጠቀሙም፥ ስጦታዎቹ ያው የእግዚአብሔር በረከቶች ነበሩ። ከስጦታዎቹ አንዱ የንግግርና የእውቀት ችሎታ ነበር። ችግሩ አማኞቹ ትክክል ባልሆነ

እውቀት (ጥበብ) እና በመንፈሳዊ ኩራት ላይ ማተኮራቸው ነበር። ሌላው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታዩ መንፈሳዊ ስጦታዎች ነበሩ። ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ሊሰጣቸው ከፈለገው ስጦታዎች አንድም እንዳልጎደለባቸው ገልጾአል። አሁንም ችግራቸው ለተወሰኑ መንፈሳዊ ስጦታዎች የነበራቸው አመለካከትና ለሰዎች ሁሉ ከማገልገል ይልቅ ለራስ ወዳድነት ዓላማ ለማዋል መፈለጋቸው ነበር።

ለ. የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መመለስ ይጠባበቁ ነበር። የሚያስቡትም በዚህ ዓለም ውስጥ እንዴት እንደሚኖሩ፥ እንዴት ብዙ ሀብት፥ ብዙ መሬት፥ የተሻለ ሥራ ወይም ትምህርት እንደሚያገኙ አልነበረም። ዓይኖቻቸውና ልባቸው በኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት ላይ ነበር። ነገር ግን የዚያን መጭ መንግሥት አንዳንድ ዝርዝር ጉዳዮች በተለይም የሙታንን ትንሣኤና በምድር ላይ እያሉ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት አካል ሆነው የሚኖሩበትን ሁኔታ በተሳሳተ መልኩ ነበር የተረዱት።

ሐ. ጳውሎስ እግዚአብሔር በልጆቹ ሕይወት ውስጥ ለሚያከናውነው በትዕግሥት የተሞላና ዳሩ ግን ጥብቅ የሆነ ተግባር ልበ ሙሉነት ይሰማው ነበር። እኛ በኃጢአትና በራስ ወዳድነት የተሞላን፥ መንፈሳዊ ብስለትም የጎደለን ልንሆን እንችላለን። ጳውሎስ ግን በእግዚአብሔር ባሕርይ ምክንያት ልበ ሙሉነት ይሰማዋል። እግዚአብሔር ታማኝ ነው። እያንዳንዱን አማኝ ስለመረጠ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት በምንቆምበት ጊዜ እንከን የለሽ እንሆን ዘንድ በሕይወታችን ውስጥ ይሠራል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ መሆናችን፥ ይህንን ማስታወስ አለብን። ብዙውን ጊዜ ዓይኖቻችን የሚያርፉት በአብያተ ክርስቲያኖቻችን ድክመቶችና በክርስቲያኖች ችግሮች ላይ ነው። ጳውሎስ በእግዚአብሔር ላይ ስላተኮረና በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ በሚያከናውነው ተግባር ላይ ልበ ሙሉነት ስለተሰማው፥ ዐበይት የቤተ ክርስቲያን ችግሮች በሚታዩበት ጊዜ ሳይቀር በመተማመን ይመላለስ ነበር።

> 17ኛ ጥያቄ፦ ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉትን ችግሮች ዘርዝር። ለ) በእነዚህ ችግሮች ላይ ማተኮር ተስፋ መቁረጥን ወይም ፍራቻን እንዴት ሊያስከትል እንደሚችል ግለጽ። ሐ) እግዚአብሔር በግለሰቦችና አብያተ ክርስቲያናት ሕይወት በመሥራት ስሙን ሊያስከብር በመቻሉ ላይ ብናተኩር አመለካከታችን እንዴት ይቀየራል?

## ክፍል አንድ፣ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳሉ የተገለጹ ችግሮች (1ኛ ቆሮ. 1፡10-6፡20)

### የመጀመሪያው ችግር፣ ክፍፍል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ (1ኛ ቆሮ. 1፡10-4፡21)

ጳውሎስ በመልእክቱ ውስጥ ያነሣው የመጀመሪያው ዐቢይ ጉዳይ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለተከሰተው ክፍፍል ነበር (1ኛ ቆሮ. 1-4)። ጳውሎስ ክፍፍል፥ በተለይም የተወሰኑ መሪዎችን በመከተል የሚፈጠር ክፍፍል የዓለምን ጥበብ እንደሚያሳይ፥ የአማኞችን አለመብሰል

እንደሚያመለክትና የመሪነትን ጽንሰ ሐሳብ በተሳሳተ መንገድ መረዳታቸውን እንደሚያስረዳ ገልጾአል።

1. ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መከፋፈል መኖሩን ገለጸ (1ኛ ቆሮ. 1፡10–17)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተመዘገበው የመጨረሻው የክርስቶስ ጸሎት ስለ አማኞች አንድነት የቀረበ ነው (ዮሐ. 17)። ጳውሎስ ጠንካራ አገላለጾችን በመጠቀም የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በሃሳብና በተግባር አንድነት በመመሥረት ይህንኑ ጸሎት እውን እንዲያደርጉ ጠይቋል። ይህ ግን ጳውሎስ ሰዎች ሁሉ በሁሉም ነገር ተመሳሳይ አሳብ እንዲይዙ መፈለጉን አያሳይም። ነገር ግን ጠቃሚ በሆነው ጉዳይ ላይ እንዲያተኩሩ፥ ማለትም አንድነትን ለመፍጠር እንዲቆርጡና አብረው እንዲሠሩ ይፈልጋል።

ክርስቲያኖች በተለያዩ ነገሮች ላይ ይከፋፈላሉ። አንዳንድ ጊዜ በአነስተኛ የአስተምህሮ ጉዳዮች፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ በዘርና በጎሳ፥ ወይም አንዱ ቡድን ሌላውን በሆነ መንገድ በመጉዳቱ ምክንያት እንከፋፈላለን። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የተከፋፈሉበት ምክንያት የተለያዩ ታዋቂ መሪዎችን በሞዴልነት ለመከተል በመፈለጋቸው ነበር። (ይህም ሰዎች እንደ ሮናልዶ ዓይነቱን ስፖርተኛ ወይም እንደ ቦንኬ ዓይነቱን ሰባኪ ወይም የፈውስ አገልጋይ በቲፎዞነት ከሚከተሉበት ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ነው።) እነዚህ ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታላቁ መሪ ማን እንደሆነና ማንን ለመከተል እንደሚፈልጉ ይከራከሩ ነበር። አንዳንዶች የቤተ ክርስቲያናቸው መሥራችና ታላቅ የአሕዛብ ሐዋርያ የነበረውን ጳውሎስን ተከተሉ። ሌሎች ጳውሎስ በሁለተኛው የወንጌል መልእክተኝነት ጉዞው መጨረሻ ከቆሮንቶስ ከወጣ በኋላ መጥቶ ሲያገለግል የነበረውንና በአንደበተ ርቱዕነት የሚታወቀውን አጵሎስን ተከተሉት። የአይሁድ ክርስቲያኖች የቤተ ክርስቲያን መሥራችና የአይሁዶች ሐዋርያ የነበረውን ኬፋን (የጴጥሮስ አይሁዳዊ ስም) ተከተሉት። አንዳንድ ምሁራን ይህ ጴጥሮስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማገልገል እንደመጣ ያሳያል ይላሉ። በመጨረሻም፥ በጣም መንፈሳውያን ነን የሚሉት ደግሞ የክርስቶስ ተከታዮች መሆናቸውን ገለጹ።

| |
|---|
| 18ኛ ጥያቄ፡– በኢትዮጵያ ውስጥ አንዳንድ ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ይልቅ በሰብአዊ መሪ ላይ ሲያተኩሩ የተመለከትከው እንዴት ነው? |

ጳውሎስ የትኛውንም ሰብአዊ መሪ መከተሉ ትክክል እንዳልሆነ ገልጾአል። የበለጠ የስብከት ስጦታ አለው የሚባለውን አገልጋይ ለማግኘት ከቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን መዟዟሩ ትክክል አይደለም። ለችግሮቻችን ሁሉ መፍትሔ የሚያመጣ ይመስል ታላቅ የፈውስ አገልጋይ በሄደበት ሁሉ መዞሩም ተገቢ አይሆንም። ይህንን በምናደርግበት ጊዜ ሰይጣን ዓይኖቻችንን ከክርስቶስ ላይ አንሥተን ኃጢአተኛ፥ ደካማና ፍጹም ባልሆነ የሰው ልጅ ላይ እንድናሳርፍ አድርጓል ማለት ነው። ጳውሎስ አሉታዊ ምላሽ የሚያስገኙ ጥያቄዎችን በማንሣት እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት ትክክል አለመሆኑን ያሳያል። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካልና አንድ ክፍል ነች። የክርስቶስ አካል እንዴት ሊከፋፈል ይችላል? ጳውሎስ ለኃጢአታቸው አልተሰቀለም ነበር። በእርሱ ስምም አልተጠመቁም ነበር (ጳውሎስ ሰዎች

በእርሱ ስለመጠመቃቸው በትምክሕት እየተናገሩ ከክርስቶስ ይልቅ እርሱን እንዳይከተሉት በማሰብ ብዙዎችን ከማጥመቅ እንደ ተቆጠበ ገልጾአል። ይህም ዛሬ አንዳንድ ክርስቲያኖች በተሳሳተ መልኩ ከሚያስተምሩት በተቃራኒ ጳውሎስ የውኃ ጥምቀት ለደኅንነት አስፈላጊ ነው ብሎ እንዳላሰበ ያሳያል። እንደዚያ ዓይነት አመለካከት ቢኖረው ኖሮ፥ ወደ ክርስቶስ የመለሳቸውን ሰዎች በሙሉ ራሱ ባጠመቃቸው ነበር።)

መንፈሳዊ ስጦታ ባለው መሪ ላይ ትኩረት በምናደርግበት ጊዜ ሁሉ የሰውን ጥበብ ተከትለናል ማለት ነው። በዓለም የሚታየው ይኸው ነውና። በሰዎች ላይ በምናተኩርበት ጊዜ ደግሞ ከክርስቶስ መስቀል ለችግሮቻችን ሁሉ መፍትሔ ከመሻት እንታቀባለን።

2. <u>ስለ ዓለማዊ ጥበብና በክርስቶስ መስቀል በተገለጠው መንፈሳዊ ጥበብ መካከል ያለውን ልዩነት ጥርት አድርጎ አለማወቅ ክፍፍልን ያስከትላል</u> (1ኛ ቆሮ. 1፡18-2፡16)። ስሕተት የሆነው ነገር እንደ አስፈላጊ ነገር አጽንኦት ሲሰጠው ዓለማዊ ጥበብ ይንጸባረቃል።

ሀ. ዓለማዊ ጥበብ በሰው አንደበተ ርቱዕነት ምክንያት፥ በማቅረብ ችሎታውና ሰዎችን የሚያስደስቱ ጥበቦችን በመጠቀም ብቃቱ ላይ ያተኩራል። ጳውሎስ ይህን «የሰው የቃል ጥበብ» ይለዋል (1ኛ ቆሮ. 1፡17)። ይህ ጥበብ በእውነት፥ በሚነገረው መልእክት፥ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በመስማማቱ ወይም እግዚአብሔር የሚፈልገውን በማብራራቱ ላይ አያተኩርም። ይህ ጥበብ የሚያተኩረው በንግግር ችሎታው፥ ሰዎችን ለመሳብና ስሜቶችን ለማነሣሣት በመቻሉ ላይ ነው።

ለ. ዓለማዊ ጥበብ የተማሩ ሰዎች በሚወዱቸው ነገሮች ላይ ያተኩራል። የተማሩትና የሠለጠኑት ግሪኮች እውቀታቸውን በሚያሳዩበት ጥበብ ላይ አጽንኦት ያደርጉ ነበር። ዛሬ ብዙ ሰዎች፥ «ምን ያህል እንደተማርህ አሳየን፤ አስደናቂ ቃላትን ተጠቀም፤ እንግሊዝኛም እየቀላቀልህ ተናገር፤ አሳቦችን ውስብስብ አድርግ» ሲሉ የዓለማዊ ጥበብን ዝንባሌ ያሳያሉ። ጳውሎስ አብዛኛው የዓለም የፍልስፍና ትምህርት ወንጌሉን እንደሚቃወምና ,የእግዚአብሔርን ጥበብ እንደማይቀበል አስረድቷል።

ሐ. ዓለማዊ ጥበብ ሰዎችን ለሚያስደንቁ ነገሮች ትኩረት ይሰጣል። አይሁዶች የታላቅነት ዐቢይ ማረጋገጫው ተአምር ማድረግ ነው ብለው ያስቡ ስለነበረ ሁልጊዜም ተአምራዊ ምልክቶችን ይፈልጉ ነበር። «ተአምር አሳየንና እንከተልሃለን። ተአምር አድርግና ወደ ስብሰባህ እንመጣለን።» ስለሆነም፥ ተአምራትን እንደሚያሳዩ ቃል የሚገቡና ሥጋዊ ጥቅም የሚሰጡ ሰዎች በአይሁዶች ዘንድ እጅግ ተወዳጆች ነበሩ። ይህ ከዛሬው ዘመን ጋር ይመሳሰላል?

---

19ኛ ጥያቄ፡- ዛሬ ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በዚሁ ዓለማዊ ወጥመድ የሚጠመዱት እንዴት ነው?

---

የእግዚአብሔር ጥበብ ከዓለም የጥበብ ትምህርት ተቃራኒ ነው።

ሀ. የእግዚአብሔር ጥበብ በመስቀሉ ስብከት ላይ ያተኩራል። ዋናው ነገር የሰባኪው ማንነት ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ መምጣቱና እውነት መሆኑ ነው።

ለ. መለኮታዊ ጥበብ ሰዎች እንደ ታላቅ ነገር ከሚመለከቱት ጋር ይቃረናል። ዓለም መስቀል የሽንፈት ስፍራ እንደሆነ ታስባለች። የነፍሰ ገዳዮች መቀጫ የሆነው መስቀል ለሰው ልጆች ችግሮች መፍትሔ የሚሆነው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ግን በጥበቡ የሞትን መሣሪያ ወደ ሕይወት መሣሪያነት በመለወጥ የሰውን ልጆች የኃጢአት ዋጋ በከፈለበት ቦታ የእርሱ ልጆች የሚሆኑበትን መንገድ ከፍቷል።

ሐ. የእግዚአብሔርን ጥበብ የሚረዳው ትሑቱ እንጂ ኩሩው አይደለም። ስለሆነም፥ ዝቅ ያሉ፥ ብዙ ትምህርት፥ ሀብት ወይም የዓለም ክብር የሌላቸው ሰዎች ናቸው ወንጌሉን ተረድተው የሚቀበሉት። የእግዚአብሔር መንግሥት በቀዳሚነት የተገነባው ዓለም በምትንቃቸው ሲሆን፥ ዓለም የምታከብራቸው ሰዎች የእግዚአብሔርን የደኅንነት መንገድ ለመቀበል ይቸገራሉ።

መ. የእግዚአብሔር ጥበብ ከሰዎች፥ በተለይም የፖለቲካ፥ የትምህርትና የኢኮኖሚ መሪዎች ከሆኑት ወገኖች የተሰወረ ነው። ብዙውን ጊዜ ወንጌሉ ትሕትናን እንዴት እንደሚጠይቅ ለመረዳት የሚቸገሩ ሲሆኑ፥ ያላቸውን በረከት ትተው ሙሉ ለሙሉ ወደ እግዚአብሔር ደኅንነት ለመመለስ ይፈተናሉ። ይህ ለመሪዎች ከባድ ነው። የፖለቲካና የሃይማኖት መሪዎች ክርስቶስ እንዲሰቀል የጠየቁት ለዚህ ነበር።

ሠ. በክርስቲያኖች ውስጥ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፍላጎት፥ አሳብና አመለካከት ያውቃል። እውነተኛ መንፈሳዊነት ያላቸው ሰዎች ራሳቸውን ለመንፈስ ቅዱስ የሚሰጡና እርሱም በሰዎች፥ በትምህርት ወይም በኃይልና በመሳሰሉት ላይ ሳይሆን በደኅንነትና እግዚአብሔርን በማስከበር ላይ የሚያተኩረውን ጥበብ እንዲገልጥላቸው የሚፈቅዱት ብቻ ናቸው።

ረ. የእግዚአብሔር ጥበብ የመንፈሳዊ ጥበብ መለያ ነው። ክርስቲያኖች በሚጣሉበት ጊዜ ወይም ከክርስቶስ ይልቅ ሰዎችን በሚከተሉበት ወቅት የእግዚአብሔር ጥበብ እንደሌላቸው ያሳያል። መንፈሳዊ ብስለት ቢኖራቸው ዓለማዊ ጥበብ (ዓለም ዋጋ የምትሰጣቸው ነገሮች) ለዘላለማዊ መንግሥትና ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር የሚስማማ ሕይወት እንዲመሩ ለማድረግ እንደማይጠቅም ባወቁ ነበር።

ሰ. የእግዚአብሔር ጥበብ ከትምህርት አይገኝም። ይህ እግዚአብሔር ለሰዎች የሚገልጠው ነው። ጳውሎስ ደኅንነትን ያላገኙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ሊረዱ አይችሉም ማለቱ አይደለም። ያልዳነ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ ቃላቱን ሊረዳ ቢችልም፥ እውነቱ ከሕይወቱ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ግን አያውቅም። አንዳንዶች የእግዚአብሔር የተገለባበጠ ጥበብ የሚሉትን እውነት ለመረዳት አይችልም። ይህም የተገለባበጠ ጥበብ፥ ትሑቱን ሲሸልምና ኩሩውን ግን ይፈርድበታል፥ በእግዚአብሔር

የሚታመነውን ሲያድን በራሱ የሚታመነውን ይኮንነዋል። መስቀሉ ደኅንነትን እንዲያመጣ ሲያደርግ የሰው ፍልስፍናን አታላይነት ያሳያል፥ ሌሎችን ማገልገል እንደሚያስከብርና ራስን ማገልገል እንደሚያዋርድ ያሳያል።

ሸ. ዓለም ሞኝነትና ጥበብ የሆነውን እንደምታውቅ ብታስብም፥ ትክክል የሆነውንና ያልሆነውን፥ ዘላለማዊውንና በዚህ ዓለም ብቻ የተወሰነውን፥ እንዲሁም እውነተኛውንና እውነተኛ ያልሆነውን ጥበብ በግልጽ ሊረዱ የሚችሉት የእግዚአብሔር ጥበብ ያላቸው ብቻ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስን የሚያውቁና የመጽሐፍ ቅዱስን እውነቶች ለመከተል የወሰኑ ሰዎች «የክርስቶስ ልብ» ስላላቸው፥ ጠቢባን ብቻ ሳይሆኑ ጠቅላላ ሕይወታቸውን እግዚአብሔርን ለማስከበርና ለዘላለማዊ ሕይወት በሚያዘጋጃቸው መልኩ የሚኖሩ ናቸው።

---

20ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ከምታውቃቸው ሰዎች መካከል በዓለም ጠቢባን ላይባሉ ቢችሉም፥ በአኗኗራቸው መለኮታዊ ጥበብን የሚገልጹትን ሰዎች ዘርዝር። ለ) ሕይወታቸው በሌሎች ሰዎች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ምንድን ነው?

---

ጳውሎስ ዘላለማዊ መፍትሔዎች የሚገኙት በክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ጥበብ በመቀበል ብቻ መሆኑን ስለተገነዘበ፥ የሚከተሉትን ነጥቦች አስተላልፎአል።

1) ጳውሎስ ግሪኮችን ያስደነቀው አንደበተ ርቱዕነቱ የወንጌሉን መልእክት እንዳይሰውር በማሰብ በዚሁ ጉዳይ ላይ አጽንኦት ከማድረግ ተቆጥቧል (1ኛ ቆሮ. 2፡1-5)። መልእክቱን ቀለል አድርጎ አቅርቧል። አንዳንድ ምሁራን ጳውሎስ ይህን ሲል በአቴና የፈላስፋዎችን ትምህርት እየጠቀሰ በዓለም ጥበብ ለመናገር የሞከረበትን ሁኔታ እያስታወሰ ነበር ይላሉ። ይህ የማስተማር መንገድ ውጤታማ ሆኖ በአቴና ብዙ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ አላመጣም ነበር። ስለሆነም፥ ጳውሎስ በቆሮንቶስ የሚያባብል ቃል ሳይጠቀም ወንጌሉን በግልጽ ሰበከ። ኩሩና የተማሩ የአቴና ሰዎች ወንጌሉን ለመቀበል ቢቸገሩም፥ በቆሮንቶስ የሚገኙ ድሆች፥ ባሮችና ያልተማሩት ግን በቀላሉ ለማመን ችለዋል።

2) እግዚአብሔር መልእክቱን ለማጠናከር ተአምራትን ሠርቷል። እግዚአብሔር ዛሬም ተአምራትን ይሠራል። ነገር ግን እግዚአብሔር ተአምራትንና ፈውስን የሚያመጣበት ቀዳሚ ምክንያት ሰዎችን ለማስደነቅ ወይም ችግራቸውን ለመቅረፍ አይደለም። በዓለም ዙሪያ ብዙ ተከታይ ለማግኘትም አይደለም። የደኅንነት መልእክት ከእግዚአብሔር እንደመጣ ለማሳየት ነው። ጳውሎስ ሕዝቡ በእርሱ ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔርና በወንጌሉ ላይ እንዲያተኩር በመፈለጉ ተአምራትን በጥንቃቄ እንዳደረገ ገልጾአል (1ኛ ቆሮ. 2፡5)።

---

21ኛ ጥያቄ፦ ጳውሎስ ለርቱዕ አንደበትና ለተአምራት ካሳየው አመለካከት ምን እንማራለን?

---

3. <u>የተለያዩ ሰዎችን ከመከተል የሚመጣው ክፍፍል መሪዎች እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች የሚያበረክቱትን የአገልግሎት ድርሻ በተሳሳተ መንገድ</u>

እንድንረዳ ያደርጋል (1ኛ ቆሮ. 3)። መንፈሳዊ መሆንህን ወይም አለመሆንህን እንዴት ታውቃለህ? በልሳን በመናገር ወይም ታላላቅ መንፈሳዊ ስጦታዎችን በመጠቀም ነውን? ጳውሎስ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ስጦታዎች በሙሉ እንደነበሯቸው አስረድቷል። ነገር ግን መንፈሳዊ ብስለት ስላልነበራቸው ዓለማዊ ጥበብን ይከተሉ ነበር። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሃሳባቸውና ድርጊታቸው እንደ ዓለማዊያን ነበር። ሕይወታቸው በእግዚአብሔር ጥበብ የሚመራ አልነበረም። ዓለማዊነት ወይም የዓለምን ጥበብ መከተል ራሱን የሚገልጸው እንዴት ነው? ከዐበይት የመገለጫ መንገዶች አንዱ ክፍፍል ነው። በቆሮንቶስ ክፍፍሉን ያስከተለው መንፈሳዊ ስጦታ ስለነበራቸው መሪዎች በምእመናኑ ዘንድ የነበረው የተሳሳተ አመለካከት ነበር። ዛሬ ክፍፍሉን የሚያስከትለው ጎሰኝነት፥ ገንዘብ፥ ወዘተ. ሊሆን ይችላል። የችግሮቻችን ሁሉ መፍትሔ ክርስቶስ ብቻ ሆኖ ሳለ በሰብአዊ መሪዎች ላይ በምንደገፍበት ጊዜ፥ የዓለምን መንገዶች እንደምንከተል ማሳየታችን ነው።

እንግዲህ፥ ተሰጥዖ ያላቸውን መሪዎችና ክርስቲያኖች ሁሉ መረዳት ያለብን እንዴት ነው?

ሀ. እያንዳንዱ መሪ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት የሚያስችል ልዩ ክፍል የሰጠው አገልጋይ ብቻ ነው። ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ተካይ ነበር። እግዚአብሔር ጳውሎስ ወንጌል ወዳልተሰበከባቸው አካባቢዎች በመሄድ ስለ ክርስቶስ እንዲመሰክርና አብያተ ክርስቲያናት በሚባሉ ኅብረቶች እንዲያደራጃቸው ልኮት ነበር። አጵሎስ በእግዚአብሔር ቃል አማካኝነት ጳውሎስ የተከላቸውን አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት እንዲያጠጣ የተመረጠ ስጦታ የነበረው አስተማሪ ነበር።

ለ. ዘላቂ ፍሬ የሚያስገኘው የግለሰቡ ስጦታ ሳይሆን የእግዚአብሔር ሥራ ነው። አንድ ገበሬ ችግኙን ከመትከልና ውኃ ከማጠጣት በቀር የማሳደግ ችሎታ እንደሌለው ሁሉ፥ የትኛውም መሪ መንፈሳዊ ዕድገትን ሊያመጣ አይችልም። ይህን ሊያደርግ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር በዋናነት የሚሠራው በሰዎች አማካኝነት ነው። እኛ እግዚአብሔር የሚሠራብን መሣሪያዎች ነን። ለሰው ስጦታዎችን የሚሰጠውም ሆነ መንግሥቱን ለመገንባት የክርስቲያኖችን ሥራ የሚጠቀመው እግዚአብሔር ስለሆነ፥ ቀዳሚ ትኩረት የሚገባው ለሰዎች ሳይሆን ለእግዚአብሔር ነው። ማንኛውም ስጦታ ያለው መሪ (ሰባኪ፥ የፈውስ አገልጋይ) ከእግዚአብሔር በስጦታ የሚቀበለው እንጂ ከራሱ ጥረት የመነጨ አይደለም። ስለሆነም፥ በመሪው ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ማተኮር እንዳለብን ልንገነዘብ ይገባል። (ይህ ከእኛ የበለጠ ስጦታ ባላቸው ሰዎች መቅናት እንደሌለብንም ያሳያል። ይህ እነርሱ በጥረታቸው ያገኙት ሳይሆን፤ የእኛን ስጦታ ከእግዚአብሔር እንደተቀበልን ሁሉ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተቀብለውታል።)

ሐ. እያንዳንዱ መሪ ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ ጥሪ፥ ዓላማና ችሎታ አለው። እያንዳንዱ ግለሰብ መሪና እያንዳንዱ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የተቀበላቸውን ችሎታዎች ለተጠቀመበት ሁኔታ በኃላፊነት ይጠየቃል።

ዓላማው ስጦታውን የተቀበለውን ሰው ለማስከበር ሳይሆን፥ ቤተ ክርስቲያኒቱ አድጋ እግዚአብሔር ከሚፈልግበት ደረጃ እንድትደርስ ለማድረግ ነው። እያንዳንዱ ግለሰብ ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ ለማገዝ የራሱን ድርሻ በጥንቃቄ ማበርከት አለበት።

መ. እያንዳንዱ ክርስቲያንና በተለይም መሪዎች የሚሠሩት የክርስቶስ ቤተ መቅደስ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ለመገንባት የጋራ ዓላማ ነው። ስለሆነም፥ አንድ ክርስቲያን ከሌላው የበለጠ ክብር እንዳገኘ በማሰብ መቅናት ወይም ከሌላው ክርስቲያን ወይም መሪ የበለጠ ክብር ለማግኘት መወዳደር አያስፈልግም።

ሠ. ክርስቶስ እያንዳንዱን ክርስቲያን እግዚአብሔር በሰጠው ስጦታ አማካኝነት ለቤተ ክርስቲያን ግንባታ ስላበረከተው አስተዋጽኦ ይጠይቀዋል። እግዚአብሔር ፍርዱን የሚሰጠው በምን ላይ ተመሥርቶ ነው? ስለምንሠራ ብቻ ሳይሆን በግንባታው ወቅት ስለ አገልግሎታችን ባለን አመለካከትና በመነሻ አሳባችን ላይ በመመሥረት ነው። የቤተ ክርስቲያን አገልግሎታችን ጊዜያዊ (ገለባ፥ እንጨት፥ ሣር) ወይም ዘላቂ (ወርቅ፥ ብር፥ የከበረ ማዕድን) የሚሆነው በአመለካከታችንና በመነሣሣታችን፥ እንዲሁም ለማን ክብር እንዳገለገልን በሚያመለክቱ መስፈርቶች ነው። ስለሆነም የዓለምን ጥበብ በመጠቀም ለሰው ክብር ከሠራን፥ ሥራችን ሁሉ ዋጋ ቢስና ሽልማትን የማያስገኝ ይሆናል። ነገር ግን እግዚአብሔርን ለማስከበርና መንግሥቱን ለመገንባት ባለን መሻት የምናከናውናቸው ነገሮች በዓለም ፊት ተደናቂነትን ቢያተርፉ ወይም ባያተርፉ፥ ትንሽ ወይም ትልቅ ቢሆኑ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሽልማትን ያስገኛሉ። ጳውሎስ ይህ ግምገማ ከእግዚአብሔር ዘንድ የምናገኘውን ሽልማት እንጂ ዘላለማዊ ደኅንነታችንን እንደማይነካ አመልክቷል።

ጳውሎስ ሁለት ዐበይት አሳቦችን በመግለጽ ይህንን ክፍል ደምድሟል። በመጀመሪያ፥ የአማኞች ሰውነት መንፈስ ቅዱስ የሚያድርበት የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆነ ገልጾአል። ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ውስጥ እንደሚያድር ከሚገልጸው 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡19 በተቃራኒ፥ በዚህ ስፍራ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚገኙ የክርስቲያኖች ቡድን ነበር የሚናገረው። በቆሮንቶስ (ወይም በኢትዮጵያ፥ አዲስ አበባ ወይም በሆነች አጥቢያ) ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚገኝ የአማኞች አካል ውስጥ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ያድራል። ይህም እግዚአብሔር በምድረ በዳው ጉዞ ወቅት በመገናኛ ድንኳን ውስጥ፥ በሰሎሞን ዘመን ደግሞ በቤተ መቅደስ ውስጥ ካደረበት ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ነው። በመጣላታችን ምክንያት ቤተ ክርስቲያንን ከመገንባት ይልቅ የምናፈርስ ከሆነ፥ ከእግዚአብሔር ጋር እየተጣላን ስለሆነ ፍርድ ይጠብቀናል። በብሉይ ኪዳን በሕንፃ ውስጥ የነበረው እግዚአብሔር አሁን በአማኞች ማኅበረሰብ ውስጥ እንደሚኖር ጳውሎስ ገልጾአል። እኛም እርሱንና በማኅበረሰባችን ውስጥ የሚገኘውን የእርሱን ሕልውና ማክበር አለብን። የክርስቲያኖች መጣላት የእግዚአብሔርን ሕልውና ትርጉም አልባ

ያደርገዋል። እንደ ዝሙት ሁሉ የእርስ በርስ ጠብም በሕዝቡ መካከል የሚኖረውን የእግዚአብሔርን ስም ያሰድበዋል።

ሁለተኛ፥ ጳውሎስ ነገሮችን በዓለም ጥበብ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ጥበብ እይታ እንዲመለከቱ አስጠንቅቋቸዋል። እንደ እግዚአብሔር መመዘኛ ጠቢብ መሆን ትሕትናን (ሞኝ መሆን) የሚያካትት ሲሆን፥ እንደ ጳውሎስ፥ እንደ አጵሎስ ወይም ጴጥሮስ ባሉት ልዩ ስጦታ ባላቸው መሪዎች ላይ አያተኩርም። መንፈሳዊ ጥበብ ክርስቶስን ብቻ በመገንዘብ አሳብን በሰማያዊው ነገር ላይ ሲያደርግ፥ አስፈላጊ የሚመስሉትን ምድራዊ ነገሮች ሁሉ ይጥላል። እንደ ደኅንነት፥ የእግዚአብሔር ልጅነት መንፈሳዊ በረከቶች፥ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ እንክብካቤ ያሉትን ወሳኝ ነገሮች እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ሰጥቶናል።

| |
|---|
| 22ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ከዚህ ክፍል ስለ መሪነት ምን ልንማር እንደምንችል ግለጽ። ለ) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለው የእግዚአብሔር ጥበብ ይልቅ የዓለምን ጥበብ ለአሳባችንና ለተግባራችን መሠረት አድርገን በምንጠቀምበት ጊዜ ችግሮች ስለመከሰታቸው ምን እንማራለን? ሐ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ስለሚገኙት ችግሮች የዘረዘርኸውን ተመልሰህ ከልስ (17ኛ ጥያቄ)። እያንዳንዱ ችግር በመለኮታዊ ሳይሆን በዓለማዊ ጥበብ ላይ መመሥረቱን አሳይ። መ) እግዚአብሔር የሰጠህን ስጦታዎችና ኃላፊነቶች ዘርዝር። ሁሉንም በጸሎት ሆነህ መዝናቸው። እነዚህን ነገሮች የምታከናውናቸው ጊዜያዊ ጥቅሞችን በሚያመጣና እግዚአብሔርን በማያስከብር መንገድ (በእንጨት፥ በሣር፥ በገለባ) ነው? ወይስ በንጹሕ ልብ ለእግዚአብሔር ክብርን በሚያመጣ መልኩ (በወርቅ፥ በብርና በከበረ ድንጋይ ነው)? |

## አራተኛ ቀን 1ኛ ቆሮንቶስ 4-6

ተመስገን በቅርቡ ከሥነ መለኮት ኮሌጅ የተመረቀ ክርስቲያን ነው። ወደ አካባቢው ሲመለስ የቤተ ክርስቲያኒቱ የአውራጃው መንፈሳዊ አገልግሎቶች ኃላፊ ሆኖ ይሠራ ጀመር። የአውራጃው ቤተ ክርስቲያን፥ መንፈሳዊነት እንዲያድግ ይፈልግ ነበር። «እኔ ዲግሪ ያለኝ ሊቅ ነኝ። ኃላፊነቱም በእጄ ውስጥ ስላለ ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ልነግራቸው እችላለሁ። እንዲህ ዓይነት ጠቃሚ ዲግሪና እንዲህ ዓይነት አገልግሎት ስላለኝ፥ ሊያከብሩኝና ጥሩ ደመወዝ ሊከፍሉኝ ይገባል። በተጨማሪም፥ በተለይ በወጣቱ ዘንድ ታዋቂ መሆን ስላለብኝ ምንም እንኳ ፕሮግራሞቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ባይመሠረቱም እነርሱ የሚወዷቸውን ፕሮግራሞች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጀመር አለብኝ» ሲል አሰበ።

| |
|---|
| 23ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንዳንድ ጊዜ የተመስገን አስተሳሰብ በሌሎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚታየው እንዴት ነው? ለ) የዚህ ዓይነቱ አመለካከት በቤተ ክርስቲያን ላይ ምን ዓይነት ለውጥ ያመጣል? ሐ) 1ኛ ቆሮ. 4ን አንብብ። ጳውሎስና ተመስገን ለአገልግሎት ያላቸውን አመለካከት አነጻጽር። ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪነትን በተመለከተ የተመስገንን ዓይነት አመለካከት ላላቸው መሪዎች ምን የሚል ይመስልሃል? |

1. የሐዋርያትን ምሳሌነት በመከተል መከፋፈልን ማስወገድ (1ኛ ቆሮ. 4)። ክርስቲያኖች በቀላሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላለ አመራር የተሳሳተ መረዳት ሊኖራቸው ይችላል። በተሳሳተ መንገድ ሊረዱ ይችላሉ። ስለ

መሪዎች የተሳሳቱ አሳቦችን ይዘው ከእገሌ ይልቅ እገሌን እከተላለሁ በሚሉ ምእመናን ምክንያት አንዳንድ ክፍፍሎች ተከስተዋል። አንዳንድ ጊዜም መሪዎቹ ራሳቸው ስለ ክርስቲያናዊ አመራር የተሳሳተ አመለካከት በመያዝ፥ ምእመኖቻቸው እንዲያከብሯቸውና እንዲከተሏቸው ይሻሉ። ይህ ሰይጣን ክርስቲያኖች እንደ እግዚአብሔር ጥበብ ሳይሆን እንደ «ዓለም ጥበብ» እንዲያስቡ ለማድረግ የሚጠቀምበት አንድ አቅጣጫ ነው። ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያንን መሪዎች ራሳቸውን እንደ ባሪያዎች እንዲመለከቱ በግልጽ አሳስቧል (ማቴ. 20፡24-28 አንብብ።) ነገር ግን ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የዓለምን ምሳሌነት በመከተል ራሳቸውን እንደ አለቆች ይቆጥራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን የሚያተኩረው በአገልጋይ መሪዎች አገልግሎት ላይ ነው። ሰይጣን ግን ብዙውን ጊዜ መሪዎች በሥልጣንና ክብር ላይ እንዲያተኩሩ ያደርጋል። መሪዎቿ ወይም ምእመናኖቿ ስለ አመራር ተገቢውን ግንዛቤ ካልጨበጡ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለትልቅ አደጋ ትጋለጣለች።

ለዚህ ነው ጳውሎስ አመራር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን እንደሚመስል የጻፈው። የቤተ ክርስቲያን አመራር ከዓለማዊ አመራር ሙሉ በሙሉ የሚቃረን ስለሆነ፥ ይህንን ትምህርት መገንዘቡ ጠቃሚ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን እንጂ በአስተዳደር ዘዴዎች፥ በትምህርትና በሥልጠና ላይ የሚያተኩረውን የዛሬውን ዘመን የዓለም የአመራር ጥበብ እንዳንከተል መጠንቀቅ አለብን። ጳውሎስ ስለ መሪነት የሚከተሉትን እውነቶች አመልክቷል።

ሀ. መሪዎች እንደ ጳውሎስና አጵሎስ የክርስቶስ ባሪያዎች ሲሆኑ፥ የእግዚአብሔርን እውነት በአደራ የተረከቡ ናቸው። መሪዎች ማንን የማክበር ኃላፊነት እንዳለባቸው ማወቃቸው በጣም ጠቃሚ ነው። የመሪዎቹ ጌታ የሽማግሌዎች ቦርድ ወይም አውራጃ ሳይሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ለአመራር ተግባራቸውም በኃላፊነት የሚጠይቃቸው ክርስቶስ ነው። ሽማግሌዎችን ለማስደሰት የሚሠራ መሪ የሽማግሌዎች ባሪያ ነው። ምእመናንን ለማስደሰት የሚሠራ መሪ የቤተ ክርስቲያኒቱ ባሪያ ነው። ዋነኛው ፍላጎታችን ክርስቶስን ማስከበር በሚሆንበት ጊዜ የእርሱ ባሪያዎች እንሆናለን (ገላ. 1፡10ን አንብብ።)።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንድ ዐቢይ አገልግሎት አላቸው። የእግዚአብሔር እውነት ተሰጥቷቸዋል። ይህንን እውነት ሊያውቁ፥ ሊኖሩትና ሊሰብኩት ይገባል። ጳውሎስ ብዙ ክርስቲያኖችና የማያምኑት ስለማያውቁት «የእግዚአብሔር ምሥጢር» የሚለውን ይህንኑ የእግዚአብሔርን ቃል እውነት መሪዎች በአግባቡ መጠቀማቸው ወሳኝ ነው። እግዚአብሔር በኃላፊነት የሚጠይቃቸው በዚህ ተግባራቸው ነውና። መሪዎች እንደ ጥሩ አኗኗር፥ ተጨማሪ እውቀት፥ ጥሩ ደመወዝ፥ የፈውስ አገልግሎት፥ የማኅበረሰቡን ተወዳጅነት በመሻት፥ ወዘተ... ከኃላፊነታቸው ሊዘናጉ ይችላሉ። እነዚህ ነገሮች የእግዚአብሔርን ቃል ምሥጢራት ከማካፈል ካደናቀፉአቸው የመሪነት ተግባራቸውን ሊወጡ አልቻሉም ማለት ነው።

ሰዎችን የሚያስደንቅ የጸጋ ስጦታ ያላቸውም ሆኑ ተራ የሚመስሉ መሪዎች በእኩል ደረጃ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው። ስለሆነም አንዱን በመውደድና ሌላውን በመጥላት መሪዎችን የማወዳደር መብት የለንም።

ለ. እግዚአብሔር ከመሪዎች የሚፈልገው ዋናው በሕርይ ታማኝነት ነው። የአንድ መልካም መሪ ዋነኛ ባሕርይ ጥበብ፥ የባሕርይ ጽናት፥ ጥሩ የጊዜ አጠቃቀም ወይም የአመራርና አስተዳደር ችሎታ አይደለም። ጳውሎስ ታማኝነት ከሁሉም እንደሚበልጥ ያስረዳል። ለቤተ ክርስቲያን፥ ለሽማግሌዎች ታማኝ መሆኑ አስፈላጊ ነው። ከሁሉም በላይ ግን እግዚአብሔር የወንጌሉን እውነት እንዲሰብኩ የሰጣቸውን «አደራ» በመወጣት መሪዎች ታማኝነታቸውን ማረጋገጣቸው ወሳኝ ነው።

ሐ. ዋናው ነገር የመሪው ታዋቂነት አይደለም። ጳውሎስ ውጫታማነቱን የለካው የቆሮንቶስ አማኞች ታላቅ መሪ ነው ብለው በማሰባቸው ላይ ተመሥርቶ አልነበረም። ነገር ግን እግዚአብሔር በሰጠው ችሎታና ስጦታ አማካኝነት ጥሪውን በትክክል ለመፈጸሙ ሕሊናው ይመሰክርለት ነበር። ጳውሎስ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ምስጋናም ሆነ ወቀሳ አገልግሎትን ለመመዘን የሚጠቅም ዋነኛ ጉዳይ ነው የሚል ግምት አልነበረውም። ይህ ዘላለማዊ ሁኔታውን ሊለውጥ አይችልም ነበር። ነገር ግን ጳውሎስ የወንጌሉን እውነት በመስበኩ በኩል ምን ያህል የታማኝነት ተግባር እንዳከናወነ በዘላለም ፈራጅ ፊት የሚመዘን መሆኑን ያውቅ ነበር። ዋናው ነገር ደግሞ ይሄ ነበር። እግዚአብሔር ሰዎች የሚመለከቷቸውን ውጫዊ ነገሮች (ርቱዕ አንደበት፥ የሰዎችን ስሜት ማስደሰት፥ ታዋቂነት፥ ትምህርት) አልፎ ልብን ያያል። ከመሪዎች ተግባር በስተጀርባ ያለውን የተነሣሽነት ምክንያት ያያል። እግዚአብሔር እንዲያከብረን የማያደርጉት ወይም የሚያደርጉት እነዚህ የተነሣሽነት ምክንያቶች እንጂ ሰዎች የሚመለከቷቸው ውጫዊ ተግባራት አይደሉም።

መ. ለሁሉም ክርስቲያኖችና መሪዎች ስጦታዎችን የሚሰጣቸው እግዚአብሔር ነው። ችሎታውን ያገኙት የበለጠ ስለተማሩ፥ የበለጠ መንፈሳውያን ስለሆኑ፥ ተግተው ስለሚሠሩ ወይም ከሌላው ሰው የተለዩ ስለሆኑ አይደለም። ስለሆነም በችሎታቸው ወይም በታዋቂነታቸው ሊመኩ አይገባም። ከእነርሱ ያነሰ ችሎታ ያላቸውን ሰዎች መናቅ የለባቸውም። ከእነርሱ የበለጠ ችሎታ ባላቸው ሰዎችም ላይ ሊቀኑ አይገባም።

ሠ. የቤተ ክርስቲያን መሪነት መንገድ ብዙውን ጊዜ ብዙ ጥቅሞችን ሳይሆን ብዙ ሥቃዮችን ያስከትላል። ጳውሎስ የራሱን ሕይወት ከቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሕይወት ጋር አነጻጽሯል። ጳውሎስ ከአሥራ ሦስቱ እጅግ ወሳኝ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች አንዱ የሆነ ሐዋርያ ነበር። ነገር ግን በጦርነት ከተማረኩ በኋላ ሕዝብ እንዲያያቸውና በኋላም እንዲገደሉ ወደ ስታድዩም እንደሚወሰዱ የዘመኑ ወታደሮች፥ እርሱም ለመሳለቂያነት መዳረጉን ያስረዳል። ጳውሎስም ሆነ ሌሎች ሐዋርያትና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመከራ ሕይወት ከመግፋት አልፈው እንደ ጠቢብና ባለጸጋ ሊከበሩ አልቻሉም ነበር። ሰዎች እንደሚያሳድዷቸውና እንደሚቀልዱባቸው ለማኞች ነበሩ።

በአንጻሩ፥ የቆሮንቶስ አማኞች ቀላልና ምቹ ሕይወት ይመሩ ነበር። ብዙ ገንዘብ ነበራቸው። ልጆቻቸው የተሻለ የትምህርት ዕድል ያገኙ ነበር። የተሻለ ቤት፥ የተሻለ ገቢ፥ ወዘተ... ነበራቸው። ጳውሎስ ይህ ትክክል አይደለም አላለም። እርሱ የሚለው መሪዎችና መእመናን አብረው ሊያድጉ ይገባል ነው። የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ለመሪዎቻቸው በቂ ደመወዝ አለመክፈላቸውና እነርሱ እየበለጸጉ መሪዎች በኑሮ ሲቸገሩ ይሄ ለእግዚአብሔር ነገሮች ብዙም ትኩረት አለመስጠታቸውን ያሳያል። በሌላ በኩል፥ መሪዎቹ ከምእመናን የበለጠ ደመወዝ ማግኘታቸውና ምእመኖቻቸው የገንዘብ ችግር እያጋጠማቸው እነርሱ እየከበሩ መሄዳቸው ይሄም በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ትክክል አይደለም። ነገር ግን የመሪነት ወይም የወንጌላዊነት ሕይወት ተጨማሪ በረከትን ሳይሆን ተጨማሪ ሥቃይን እንደሚያስከትል ጳውሎስ ከራሱ ሕይወት ጠቅሶ አስረድቷል። ይህም ሙሉ ለሙሉ መጥፎ አይደለም። ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያን አመራር ከከባድ ሥቃይ ይልቅ ብዙ ጥቅም የሚያስገኝ ቢሆን ኖሮ ሰዎች የተሳሳቱ ምክንያቶች እያቀረቡ መሪዎች ለመሆን ይፈልጉ ነበር።

ረ. አብያተ ክርስቲያናት ለመሪዎች፥ በተለይም እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ለመትከል ለሚጠቀምባቸው አገልጋዮች ልዩ ክብር መስጠት አለባቸው። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የበለጠ ስጦታ ያለው ሰባኪ በሚመጣበት ጊዜ በእርሱ ላይ ከመሳለቅ ይልቅ ጳውሎስን ማክበር ነበረባት።

ሰ. መሪነት በቀዳሚነት ተግባራዊ የሚሆነው ከቃላት ይልቅ በሕይወት ምሳሌነት ነው። ብዙውን ጊዜ የተማሩ ወጣቶች ለመሪነት ይሾማሉ። ነገር ግን የክርስቶስ አርአያ ለመሆን የሚያበቃ ብስለት የላቸውም። ስለሆነም፥ ስለ መሪነት የተሳሳቱ አመለካከቶችን በሚያንጸባርቁበት ጊዜ ልንፈርድባቸው አይገባም። ለመሪነት ወሳኙ ቅድመ ሁኔታ መንፈሳዊ ብስለት ሲሆን፥ ይህም ብዙ ጊዜ የሚወስድ ሂደት ነው። ጳውሎስ ልቡም ሆነ ተግባራቱ ትክክል መሆናቸውን ስለሚያውቅ፥ «እኔን ምሰሉ» ለማለት ችሏል (1ኛ ቆሮ. 4፡16)። ምእመኖቻችን መንፈሳውያን እንዲሆኑ፥ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ፥ እንዲቀደሱና ስለ አመራር ተገቢውን ግንዛቤ እንዲያገኙ ከፈለግን እኛ መሪዎች ይህንን እንዴት እንደሚያከናውኑ ማሳየት አለብን። በራስ ወዳድነትም ይሁን ለእግዚአብሔር ክብር አመራር በምንሰጥበት ጊዜ የእኛን ምሳሌ ይከተላሉ።

ሸ. ጳውሎስ ሐዋርያ እንደ መሆኑ «በትር» ሲል የገለጸው ልዩ ሥልጣን ነበረው። ጳውሎስ ይህን ሥልጣኑን በዓመፀኞች የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ላይ ፍርድን ለማምጣት ሊጠቀም እንደሚችል ገልጾአል። ነገር ግን ንስሐ ገብተው አመለካከታቸውንና ተግባራቸውን ከቀየሩ በፍቅርና በገርነት እንደሚመጣላቸው አስታውቋል።

| |
|---|
| 24ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የተመሰገነ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ነህ እንበል። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 4 ስለ አመራር የገለጻቸውን አሳቦች በመጠቀም፥ ተመስገንን እንዴት ትመክረዋለህ? ለ) የቤተ ክርስቲያን አመራር አመለካከታቸውን መለወጥ የሚያስፈልጋቸው አንዳንድ መሪዎች አሉ? በዚህ ክፍል ውስጥ ስለ መሪነት የተማርኸውን እንዴት በአግባቡ ልታካፍላቸው ትችላለህ? |

25ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ቆሮ. 5፡1-6፡20ን አንብብ። ሀ) ጳውሎስ የገለጸው ኃጢአት ምን ነበር። ለ) ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት እርምጃዎችን እንድትወስድ አሳሰባት? ሐ) እነዚህ ክርስቲያኖች በኃጢአት ላይ የነበራቸው የተሳሳተ አመለካከት ምን ነበር? መ) አማኞች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ዓይነት ድርሻ ሊኖራቸው እንደሚገባና ይህም ሰዎችን በፍርድ ቤት ከመክሰስ ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት እንዳለው ግለጽ። ሠ) ጳውሎስ ወሲባዊ ኃጢአት እጅግ የከፋ መሆኑን የገለጸው ለምንድን ነው? ክርስቲያን በዚህ ኃጢአት ላይ ምን እርምጃ እንዲወስድ ጠየቀ?

## ሁለተኛው ችግር፡ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ምግባረ ብልሹነት ነበር (1ኛ ቆሮ. 5፡1-12)

መሪዎችን ጨምሮ ክርስቲያኖችን በተደጋጋሚ ከሚያውኩ ኃጢአቶች አንዱ ወሲባዊ እርኩሰት ነው። ከጋብቻ ውጭ ወሲብ የሚፈጽም ባል ወይም ሚስት፥ ወንድ ወይም ሴት ወጣት እግዚአብሔርን በጽኑ ያሳዝነዋል።

የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ከብዙ ሰዎች ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ተቀባይነት ባገኘበት ማኅበረሰብ ውስጥ ይኖሩ ነበር። የቆሮንቶስ ሰዎች ከጋብቻ ውጭ ከሚፈጽሟቸው የወሲብ እርኩሰቶች በተጨማሪ፥ እንደ ግብረ ሰዶማዊነት ያሉትን ያልተለመዱ ወሲባዊ ተግባራት ያከናውኑ ነበር። በዚህ ባሕል ውስጥ የነበሩት የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ይህን ችግር እንዴት መቋቋም እንዳለባቸው አላወቁም ነበር። ስለሆነም አከራሪ ጫፍ ይመዙ ጀመር። አንዳንዶች ሁሉም ወሲባዊ ግንኙነቶች ከፉዎች ስለሆኑ መጋባት ለክርስቲያኖች አስፈላጊ እንዳልሆነ ይናገሩ ጀመረ። ሌሎች ደግሞ ሁሉም ዓይነት ወሲባዊ ግንኙነቶች ተቀባይነት እንዳላቸው አስተማሩ። እነዚህ ወገኖች የእግዚአብሔር ጸጋ ለኃጢአት ይቅርታን የሚያስገኝ ከመሆኑም በላይ በሥጋ የሚሠራው ኃጢአት መንፈሳዊ ሕይወትን እንደማይነካ ገለጹ። ስለሆነም፥ ጳውሎስ እነዚህን ሁለት የተራራቁ አመለካከቶችን በማማከል መናገር ነበረበት። በ1ኛ ቆሮንቶስ 7 ስለ ጋብቻ ይናገራል። በ1ኛ ቆሮንቶስ 5-6፥ ከጋብቻ ውጭ ስለሚካሄዱ ወሲባዊ ግንኙነቶች ክርስቲያኖች የነበራቸውን የተሳሳተ አመለካከት ያብራራል።

ሁለተኛውና የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለጳውሎስ ሪፖርት ያደረጉት ችግር ግልጽ የሆነ ወሲባዊ እርኩሰት በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ መከሰቱ ነበር። ጳውሎስን ያስደነቀው ወሲባዊ እርኩሰት መፈጸሙ ሳይሆን፥ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንና መሪዎች ለዚህ ኃጢአት የነበራቸው አመለካከት ነበር።

1. ሁኔታው (1ኛ ቆሮ. 5፡1)፡- በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ከአባቱ ሚስት ጋር ዝሙት የሚፈጽም ሰው ነበረ። ይህች ሴት እናቱ ሳትሆን የእንጀራ እናቱ ነበረች። ሴቲቱ ለኃጢአቷ መቀጣት እንዳለባት የሚያመለክት አሳብ ስላልተጠቀሰ፥ ሴትዮዋ አማኝ ያልነበረች ይመስላል። ቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ያላት በምእመኖቿ ላይ ብቻ ስለሆነ፥ ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በኃጢአት የሚመላለሱ ምእመኖቿን እንዴት ማረም እንዳለባት ያስረዳል። መሪዎቹ ግለሰቡን ከመገሠጽና የቤተ ክርስቲያን የቅጣት ደረጃዎችን ተከትለው ከመሥራት ይልቅ ሁኔታውን በቸልተኝነት ይመለከቱ ነበር። ለምን? ምክንያቱም ኃጢአት እየቀጠለ እንዲሄድ መፍቀዳቸው

ለተፈጸመው ጥፋት ተቃውሞ የሌለበት ምላሽ እንዳላቸው ያሳያል። ጳውሎስ ራሱ ኃጢአት ሲበዛ የእግዚአብሔር ጸጋ ከዚያ በላይ እንደሚገለጥ አስተምሮ የለም? ሲሉ አሰቡ (ሮሜ 5፡20-21)።

2. የጳውሎስ ውሳኔ (1ኛ ቆሮ. 5፡2-5)፡-

ሀ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚከሰት ኃጢአት አስደሳች ወይም በቀላሉ የሚታይ ሳይሆን ኃዘንን የሚያስከትል ነው።

ለ) ይህን ኃጢአት የሚፈጽመው ግለሰብ ከቤተ ክርስቲያን ኅብረት መውጣት አለበት። ጳውሎስ ይህንኑ ግለሰቡን ከቤተ ክርስቲያን ኅብረት የማስወጣት ሂደት ሰውዬውን «ለሰይጣን አሳልፎ መስጠት» ሲል ይጠራዋል። የቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ስብሰባና ኅብረት ውስጥ ስለሚኖር ስፍራው ደኅንነት የሚገኝበትና ክርስቶስ የሚገዛበት በመሆኑ የሰይጣን ኃይል የተዳከመበት እንደሆነ ያምኑ ነበር። ነገር ግን ከክርስቲያኖች ኅብረት ውጭ ሰይጣን በንጉሥነት እንደሚገዛ ያምኑ ነበር። ስለሆነም አንድን ሰው ከኅብረቱ ማስወጣት ማለት ወደ ሰይጣን ግዛት መመለስ ማለት ነበር። በዚህ ጊዜ ሰይጣን ግለሰቡን በተለያዩ መንገዶች ሊያጠቃው ይችላል። ግለሰቡን ከቤተ ክርስቲያን ማስወጣታቸው ክርስቲያን ወዳለመሆን እንደተመለሰ አያሳይም። ቀዳሚ ዓላማውም ቅጣት አልነበረም። ይህ የግለሰቡ የኃጢአት ባሕርይ እንዲጠፋና መንፈሱ በጌታ ቀን እንድትድን ታስቦ የተደረገ የመማሪያ ገጠመኝ ነበር። ሰውዬው ከሚወዳቸው ምእመናን ተለይቶ ሲወጣ በሚሰማው ኃፍረትና በሚደርስበት የሰይጣን ጥቃት ምክንያት ከኃጢአቱ ንስሐ ገብቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመለስ ለማድረግ የተወሰደ እርምጃ ነበር። (የዚህን አሳብ ተጨማሪ ማብራሪያ ከ1ኛ ጢሞ. 1፡20 አንብብ።)

ጳውሎስ ግለሰቡ በኃጢአቱ እየገፋበት መሆኑንና ይህም በምእመናን ሁሉ ዘንድ መታወቁን ገምቷል። ይህ አንድ ሰው ስለ ሌላው የሚያቀርበው ወቀሳ ወይም ጉምጉምታ ሳይሆን፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ጥናት አድርገው ለጳውሎስ የጻፉት ጉዳይ ነበር። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኃጢአት በሚኖርበት ጊዜ ሽማግሌዎች በማቴ. 18፡15-17 የተሰጠውን ደረጃ መከተላቸው ጠቃሚ ነው። ይህን ከፍተኛ ቅጣት መስጠት የሚቻለው ከዚያ በኋላ ብቻ ነው።

3. ይህ ከፍተኛ ቅጣት የተሰጠበት ምክንያት (1ኛ ቆሮ. 5፡6-8)፡- ኃጢአትን በትኩረት ተከታትለን የቤተ ክርስቲያን ቅጣት እንዲሰጥበት ካላደረግን ጥቂት እርሾ ጠቅላላውን ሊጥ እንደሚያቦካ ሁሉ፥ ኃጢአት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መስፋፋቱ የማይቀር ነው። ጳውሎስ ከብሉይ ኪዳን የአይሁዶች የፋሲካ ልምምድ ተነሥቶ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ይመክራል። ከፋሲካው በዓል ቀደም ብሎ እያንዳንዱ አይሁዳዊ ቤተሰብ እርሾ ያለበትን ነገር ሁሉ ያስወግድ ነበር። ይህም ክፋትን የማስወገድ ተምሳሌት ነበር። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችም የትኛውንም ዓይነት ያፈጠጠና ንስሐ ያልተገባበትን ኃጢአት ከቤተ ክርስቲያን ለማስወገድ ነቅተው ሊሠሩ ይገባል። ጳውሎስ፥ «በክፋትና በግፍ

አርሾም አይደለም» ሲል ለወሲባዊ እርኩሰት ብቻ ሳይሆን፥ በቤተ ክርስቲያን ስላለ ሥነ ሥርዓትም ጭምር ነበር። ስለሆነም፥ ንስሐ ያልተገባበትና የዓመፃ ኃጢአት ሁሉ እልባት ሊሰጠው ይገባል። ጳውሎስ ራሷን በንጽህና የምትጠብቅ ቤተ ክርስቲያንን «የቅንነትና የእውነት ዳቦ» ይላታል።

በተጨማሪም፥ ጳውሎስ ፍርዱ በክርስቲያኖች ፊት በይፋ መሰጠት እንዳለበት አመልክቷል። ይህ ኃጢአት ለፈጸመው ግለሰብ ብቻ ሳይሆን ለክርስቲያኖች ሁሉ የመማሪያ ገጠመኝ ይሆናል። ኃጢአት ከፈጸሙ በኋላ ንስሐ በማይገቡት ሰዎች ላይ የሚደርሰውን ቅጣት በመመልከት ክርስቲያኖች በተመሳሳይ ኃጢአት ላለመውደቅ ይጠነቀቃሉ። በማቴዎስ 18፡15-17 የተጠቀሰውን ሂደት ከተከተሉ በኋላ ከፍፍል እንዳይፈጠር ሽማግሌዎች ፍርዱን ለክርስቲያኖች ሁሉ ማሳወቃቸው አስፈላጊ ነው። ይህም መከፋፈል እንዳይፈጠር ያደርጋል። ስለተፈጸመው ኃጢአት ሰዎች ሁሉ ከሰሙ በኋላ ከዋናው ጋር ቢስተያይ የሽማግሌዎችን ውሳኔ በይፋ አለማሳወቁ፥ ሰይጣን የወሬ ጉምጉምታዎችን በመጠቀም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎችን እንዲከፋፍል በር ይከፈታል። በተጨማሪም፥ እነዚህ በማቴዎስ 18፡15-17 የተጠቀሱትን ምስክሮች በምንመርጥበት ጊዜ አድልዎአዊ አቅጣጫ የማይዙትን ሰዎች መጠቀም እንዳለብን ያሳያል።

| |
|---|
| 26ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ጳውሎስ የሰጠው ዓይነት ፍርድ ሲበየን አይተህ ታውቃለህ? እንደዚህ ከሆነ፥ የተከሰተውን ሁኔታ አብራራ። ለ) ቤተ ክርስቲያን በዓመፃ ኃጢአቶች ላይ ብዙም ይፋዊ ፍርድ የማትሰጠው ለምን ይመስልሃል? ይህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኃጢአት እንዲስፋፋ የሚያደርገው እንዴት ነው? ሐ) በሽምግልና ተመርጠህ በምታገለግልበት ጊዜ ሁለት የኳዬር መዘምራን ዝሙት እንደሚፈጽሙ ሰማህ እንበል። ማቴዎስ 18፡15-17 እና በዚህ ክፍል ጳውሎስ ያስተማረውን አሳብ በመከተል፥ ለዚህ ኃጢአት መፍትሔ መጠቀም ያለብህ እንዴት ነው? መ) «እነዚህን ሰዎች ብናጋልጥ እነርሱና ቤተሰቦቻቸው ቤተ ክርስቲያናችንን ጥለው ይወጣሉ። እነዚህ ሰዎች ስለሚጠቅሙን በዚህ መንገድ ልናሳፍራቸው አንችልም?» የሚል አሳብ ለሚያቀርብ ሽማግሌ ምን ምላሽ ትሰጠዋለህ? |

4. ጳውሎስ ቀደም ሲል ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ትእዛዝ አብራራ (1ኛ ቆሮ. 5፡9-11)፡- ጳውሎስ ስለዚህ ወይም ስለ ሌላ ወሲባዊ ኃጢአት ቀደም ሲል የሰማና ክርስቲያኖች ጭፍን ዝሙት ከሚፈጽሙና በእግዚአብሔር ላይ ከሚያምፁ ሰዎች ጋር ኅብረት እንዳያደርጉ የሚያሳስብ መልእክት የጻፈላቸው ይመስላል። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የጳውሎስን ትእዛዛት በተሳሳተ መንገድ በመረዳት ከዓለማውያን ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንዳያደርጉ የከለከላቸው መስላቸው። ጳውሎስ ግን የተቀደሰ አኗኗር ሳይከተሉ እንደ ዓለማውያን ስለሚኖሩ ክርስቲያኖች እየተናገረ መሆኑን ገልጾላቸዋል። አሁንም ጳውሎስ ስለ ወሲባዊ ርኩሰት ብቻ እየተናገረ አለመሆኑን መገንዘብ ጠቃሚ ነው። ስለ ራስ ወዳዶች፥ ነጣቂዎች በክርስቶስ እናምናለን እያሉ የቤተሰቦቻቸውን ወይም የማኅበረሰቡን ፍርድ በመፍራት የድሮ አምልኮአቸውን የሚያካሂዱትን ጭምር ይዘረዝራል።

ጳውሎስ ክርስቲያኖች ያፈጠጠ ኃጢአት ከሚፈጸሙ ሰዎች ጋር ምንም ዓይነት ኅብረት እንዳያደርጉ የከለከለው ክፉ መንገዳቸውን አይተው በንስሐ እንዲመለሱ ለማገዝ ነበር። በአንጻሩ ግን ጳውሎስ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በኃጢአት ከሚኖሩት ከዓለማውያን ጋር ኅብረት በማድረግ እንደሚመሰክሩላቸው አሳስቧል። እግዚአብሔር ክርስቲያኖችን የጠራቸው ዓለምን እንዲተዉና ራሳቸውን ከዓለማውያን እንዲለዩ አይደለም። ነገር ግን እርሱ ባስቀመጠን ማኅበረሰብ ውስጥ እየኖርን ንጹሐንና ቅዱሳን እንድንሆን ጠርቶናል።

---

27ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ሆን ብለው ኃጢአትን ከሚፈጽሙ ክርስቲያኖች ጋር ያለንን ግንኙነት እምብዛም የማናቋርጠው ለምን ይመስልሃል? ለ) አንዳንድ ክርስቲያኖች በክርስቲያናዊ ድርጅቶች ውስጥ ለመሥራት ሲሉ ሥራቸውን የሚለቁት ወይም ከክርስቲያኖች ጋር ለመኅራበት የሚፈልጉት ለምንድን ነው? ጳውሎስ እንዲህ ያለውን ምክንያት የሚቀበል ይመስልሃል?

---

5 ጳውሎስ ኃጢአት የሚሠሩትን ክርስቲያኖች እንደ ዓለማውያን ለምን መፍረድ እንደሌለብን ያብራራል (1ኛ ቆሮ. 5፡12-13)። በዓመፀኝነት መንፈስ ግልጽ ኃጢአት የሚፈጽሙትን ክርስቲያኖች መቅጣትና መፍረድ ያለብን እግዚአብሔር ከሰጠን የፈራጅነት ሥልጣን የተነሣ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጆች በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የመፍረድ ሥልጣን እንዳላቸው ይናገራል። (ማቴ. 19፡28 አንብብ።) ስለሆነም አሁን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዳችን በሌላችን ላይ የመፍረድ ብቃት አለን። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች በዓለማውያን ላይ እንዲፈርዱ ሥልጣን አይሰጣቸውም። ይህ የእግዚአብሔር ኃላፊነት ሲሆን፥ በመጨረሻው ዘመን ዓለማውያንን በዘላለማዊ ሞት ይቀጣቸዋል። (ራእይ 20፡11-16 አንብብ።)

ክርስቲያኖች ክርስቶስ በማቴዎስ 7፡1-5 ያስተማረውን አሳብ ጳውሎስ በዚህ አሳብ ከገለጸው ጋር ለማስታረቅ ይቸገራሉ። ክርስቶስ በማቴዎስ 7፡15-20 ተከታዮች ሰዎች በአኗኗራቸው (በፍሬአቸው እንዲፈርዱ እንዲገመግሙ) ነግሮአቸዋል። ክርስቶስና ጳውሎስ ሁለት ዓይነት ፍርድ እንዳለ እያስተማሩ ነበር። ለክርስቲያኖች ያልተፈቀደው የመጀመሪያው ዓይነት ፍርድ የሌላውን ክርስቲያን ስውር አመለካከቶችን እና የመነሻሻ ዓላማዎችን መገምገም ነው። ለምሳሌ ያህል «እገሌና እገሌ መንፈሳዊ አይደሉም። መዝሙር በሚዘምርበት ጊዜ አያጨበጭብም። እገሌና እገሌ የእኔን ጎሳ አይወዱም። እገሊት የራሷ ዘር የሆነውን ሰው ዬ ምሳ ስትጋብዝ እኔን ግን አልጋበዘችኝም» የሚሉ ዓይነት ፍርዶችንና አሳቦችን መስጠት ለክርስቲያኖች አልተፈቀደም።

ለክርስቲያኖች የተፈቀደው ሁለተኛው ዓይነት ፍርድ የእግዚአብሔርን ቃል በግልጽ የሚጥሱትን ክርስቲያኖች ተግባራትና የአኗኗር ስልቶች መመዘን ነው። የእግዚአብሔር ቃል «አታመንዝር» ሲል በግልጽ ተናግሯል። ጳውሎስ ክርስቲያኖች ይህን ትእዛዝ በሚጥሱበት ጊዜ ይህንኑ ኃጢአት የመቃወምና በቤተ ክርስቲያን የቅጣት ደንብ መሠረት ፍርድ የመስጠት ኃላፊነት እንዳለብን ያስረዳል። እንደ መዋሸት፥ መስረቅ፥ መስገብገብና

የመሳሰሉት ኃጢአቶችም በሌላው ክርስቲያን ላይ ፍርድን የሚያስጡ ናቸው።

> 28ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ክርስቲያኖች ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ባልፈቀደላቸው መንገድ በሌሎች ክርስቲያኖች ላይ እንደሚፈርዱ የሚያሳዩ አምስት ምሳሌዎችን ስጥ። ለ) እግዚአብሔር ክርስቲያኖች በሌሎች ክርስቲያኖች ላይ እንዲፈርዱ የሚጠብቅባቸውን አምስት ምሳሌዎች ስጥ።

ጳውሎስ እርስ በርሳችን የመፍረድ ኃላፊነት እንዳለብን ማብራራቱን የቋጨው፥ «ክፉውን ግለሰብ)» ከመካከላችሁ አውጡት» የሚል ፍርድ በመስጠት ነው። ከአያሌ ወራት በኋላ ጳውሎስ ይህ በኃጢአተኛው ግለሰብ ላይ የተሰጠው ቅጣት ፍሬ ማስገኘቱን ሰምቷል። በ2ኛ ቆሮንቶስ፥ ጳውሎስ ከኃጢአቱ ንስሐ የገባውን ክርስቲያን ወደ ኅብረቱ እንዲመልሱ ጠይቋል (2ኛ ቆሮ. 2፡6-11)። ይህም የመፍረድና ከኅብረት የማስወጣት (የመገዛት) ዓላማው ክርስቲያኖች ንስሐ ገብተው ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመለሱና የተቀደሰ ሕይወት ለመምራት ከቁርጥ ውሳኔ ላይ እንዲደረሱ ለማገዝ ነው።

## ሦስተኛው ችግር፡ ክርስቲያኖች በፍርድ ቤት ይካሰሱ ነበር (1ኛ ቆሮ. 6፡1-8)

ከጳውሎስ ልማዶች አንዱ ስለ አንድ ጉዳይ እየጻፈ ሳለ ሌላ ነገር ሲነገረው ርእሰ ጉዳዩን ወደ አዲሱ መረጃ የማዞር ነበር። ለምሳሌ ያህል፥ በኤፌሶን 3፡1 ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች ስለ መጸለዩ የሚናገር ይመስላል። ነገር ግን ለአሕዛብ መታሰሩን ማስታወሱ አሳቡን ስላላስለወጠው ለኤፌሶን ክርስቲያኖች ስለ መጸለይ ያነሣውን ጉዳይ ከማብራራቱ በፊት (ኤፌ. 3፡14) ወንጌል ለአሕዛብ ስለ መሰበኩ ብዙ ማብራሪያ ሰጥቷል። በዚህ ስፍራም ጳውሎስ የጀመረውን የዝሙት ጉዳይ አቋርጦ (በ1ኛ ቆሮ. 6፡9-20 የሚቀጥል) ክርስቲያኖች በሌሎች ክርስቲያኖች ላይ በመፍረድ ኃላፊነታቸውን አለመወጣታቸውን ያስረዳል።

ጳውሎስ አንዳንድ ክርስቲያኖች በሀብት ጉዳይ ሌሎች ክርስቲያኖችን ፍርድ ቤት እንደሚያቆሟቸው የሰማ ይመስላል። ምናልባት አንድ ክርስቲያን ለሌላው አንድ ንብረት ወይም ክብት ከሸጠለት በኋላ ገርው የተታለለ መስሎ ሳይሰማው አልቀረም። ስለዚህም እንደ ዓለማውያን ክርክራቸውን በፍርድ ቤት ለመቋጨት ፈለጉ። ክርስቲያኖች ችግሮቻቸውን ለመፍታት ክርስቲያን ባልሆነ ዳኛ ፊት መቆማቸው ጳውሎስን አስቆጣው። ይህ ክርስቲያኖች የመፍረድ ሥልጣናቸውን እንዳልተጠቀሙበት የሚያሳይ ነበር። ጳውሎስ እንዲህ ዓይነቱን ጉዳይ የማያምኑ ሰዎች ወደሚገኙበት ችሎት መውሰድ እንደሌለባቸው በመግለጽ የሚከተለውን ብሏል።

1. ክርክሮችን ወደማያምኑ ዳኞች (ችሎት ወይም የጎሳ ሽማግሌዎች) የሚወስዱ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የሰጠንን ሥልጣን አልተገነዘቡም። በመጨረሻ ከክርስቶስ ጋር በማያምኑ ሰዎች ላይ እንፈርዳለን። (ማቴ. 19፡28፤ 2ኛ ጢሞ 2፡12፤ ራእይ 20፡4 አንብብ።) በመላእክትም ላይ እንፈርዳለን። ይህ ምናልባትም በወደቁትና አሁን የሰይጣን መላእክትና አጋንንት ሆነው በሚሠሩት መላእክት ላይ ክርስቶስ ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ

እኛም እንደምንሳተፍ የሚያሳይ ይሆናል። (2ኛ ጴጥ. 2፡4-9፤ ይሁዳ 6 አንብብ።) እግዚአብሔር ወደ ፊት ለክርስቲያኖች እንዲህ ዓይነት ሥልጣን የሚሰጣቸው ከሆነ፥ አሁን እንደ ንብረት ያሉትን ጥቃቅን ጉዳዮች የመዳኘት ሥልጣን እንዳለን ግልጽ ነው። ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመዳኘት ሥራ የሚሠሩትን ሰዎች መምረጡ ቀላል እንደሆነ በምፀታዊ ድምፀት ይናገራል። ጳውሎስ ይህን ሲል፥ «ትምህርትና ስጦታ ያላቸውን ሽማግሌዎች ተዉአቸው። ትምህርት የሌላቸውን ሽማግሌዎች ውሰዱ። እነዚህ ሰዎች በኋላ በታላላቅ ጉዳዮች ላይ ፍርድ የሚሰጡ የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆኑ ችግሮችን ለማስተካከል ይችላሉ» ማለቱ ነበር። እንዲህ ዓይነቱን ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤት መውሰድ በክርስቲያኖች መካከል የሚነሣውን አለመግባባት የሚፈታ አስተዋይ ሰው የለም እንደ ማለት ነበር።

2. ክርስቲያኖች ችግሮቻችንን ወደ ዓለማውያን መውሰዳችን እርስ በርሳችን ለመዳኘት አለመቻላችንን ያሳያል። ይህም ምስክርነታችንን ከማበላሸቱም በላይ የክርስቶስን ስም ያስነቅፋል። ይህም በዋናው ጉዳይ ላይ ሽንፈት እንደገጠመን ያሳያል። ክርስቲያናዊ ስማችንና የክርስቶስ ስም ከየትኛውም የግል ጉዳይ የበለጠ ነው።

3. በጠብና ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት በመውሰድ የክርስቶስንና የክርስቲያኖችን ስም ከማጉደፍ ይልቅ ተበዳዩ በድሎም እንኳ ቢሆን ጉዳዩን መተው ነበረበት። የራሳችን ለሆነው ንብረት በመፋለም የክርስቶስንና የቤተ ክርስቲያንን ስም ከማጉደፍ ይልቅ መበደሉ የተሻለ ነው።

29ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ክርስቲያኖች ችግሮቻቸውን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊፈቱ ሲችሉ እንዴት ወደ ዓለማውያን እንደሚወስዱ ግለጽ። ለ) ከእነዚህ ልምምዶች የሚመነጩ አሉታዊ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ሐ) በክርስቲያኖች መካከል ስለተፈጸመ አንድ ክፍፍል ግለጽ። ጳውሎስ ባስተማረው መሠረት እግዚአብሔር ክርስቲያኖች ችግሮቻቸውን እንዴት አድርገው እንዲፈቱ የሚፈልግ ይመስልሃል?

## ጳውሎስ ስለ ዝሙት ተጨማሪ ትምህርት ሰጠ (1ኛ ቆሮ. 6፡9-20)

ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ስለተከሰተው የዝሙት ኃጢአት ያቀረበውን ገለጻ ከፈጸመ በኋላ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የትኛውንም ዓይነት ወሲባዊ ኃጢአት ማድረግ ስሕተት የሆነባቸውን ምክንያቶች ያብራራል።

ሀ. በማያቋርጥ ወሲባዊ ኃጢአት የሚኖሩ ሰዎች እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች አለመሆናቸውን ስለሚያሳዩ፥ ወደ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር መንግሥት ሊገቡ አይችሉም። በክርስቶስ በምናምንበት ጊዜ አሮጌው ሕይወታችን ተለውጦ አዲስ ሕይወት እንጀምራለን። ወሲባዊ ሕይወታችን ስለሚለወጥ ዝሙት፥ ሴተኛ አዳሪነትና ግብረ ሰዶማዊነት ከመፈጸም እንቆጠባለን። አምልኳችን ስለሚለወጥ እንደ ቀድሞው ጣዖት አናመልክም። (በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከእግዚአብሔር በላይ የምንወደው ነገር ሁሉ ጣዖታችን እንደሆነ ተገልጾአል። ቆላ. 3፡5 አንብብ።) ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት ይለወጣል። ሌሎች ሰዎችን በመስረቅ

ወይም በማታለል (በመንጠቅ) ለመክበር አንፈልግም። በተጨማሪም፥ ሌሎችን ከመርዳት ይልቅ ነገሮችን ለራስ ማግበስበሱ የራስ ወዳድነት ኃጢአት ነው። የሰዎችን ስም በማጉደፍ ዝናቸውን ለማክሰም አንፈልግም። ከራሳችን ጋር ያለ ግንኙነትም ስለሚለወጥ ከእንግዲህ የመጠጥ ባሪያዎች አንሆንም። ምንም እንኳ ከማመናቸው በፊት በዚህ ዓይነት ላይኖሩ ቢችሉም፥ ጳውሎስ የቀድሞው አኗኗር እንዳበቃ ገልጾላቸዋል። በክርስቶስ ባመኑበት ወቅት የክርስቶስ ደም ከእነዚህ ኃጢአቶች አጥቧቸዋል። እናም በደሙ ተዋጅተዋል። ደሙ ለአዲስ ሕይወት ለይቷቸዋል (ቀድሷቸዋል)። ጥፋተኛ አይደላችሁም ተብለዋል (ጸድቀዋል)። እነዚህ ሦስቱ የክርስቶስና የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ሕይወታቸውን ሙሉ በሙሉ ለውጠዋል።

ለ. ኃጢአትን የሚፈጽሙ ሰዎች ስለሚቆጣጠራቸው ነገር የተለያየ አመለካከት ይኖራቸዋል። ምናልባትም ጳውሎስ በኃጢአት እየተመላለሱ «ሁሉም ተፈቅዶልኛል» የሚሉትን አንዳንድ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች አባባል ጠቅሶ እየተናገረ ይሆናል። «እኛ በክርስቶስ ነፃ ነን። ከሕግ በታች ስላልሆንን እንደፈለግን ልንኖር እንችላለን» ሲሉ ተሟገቱ። ጳውሎስ ለዚህ ክርክር በተለያዩ መንገዶች ምላሽ ሰጥቷል።

1. መጠየቅ ያለብን ጥያቄ «የተፈቀደልኝ ምንድን ነው?» የሚል ሳይሆን የሚጠቅመው የቱ ነው የሚለውን ነው። በሙያዊ ይዘታቸው ኃጢአት ያልሆኑና ለእኛ የማይጠቅሙ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ስለሆነም፥ ለእኛ መልካም ያልሆኑትንና ክርስቲያናዊ ምስክርነታችንን የሚያጠፉትን ነገሮች ከመፈጸም መቆጠብ ይኖርብናል። እንደ ክርስቲያኖች እንድናድግ በሚረዱንና ለክርስቶስ ክብርን በሚያመጡ ነገሮች ነጻነታችን ሊገደብ ይገባል።

2. ምንም ነገር ሰውነታችንን እንዲቆጣጠር መፍቀድ የለብንም። ሰውነታችን ለእግዚአብሔር ክብር የተሠራ መሆኑን መገንዘብ አለብን። በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በመተባበራችን ከሥጋ ፍላጎት ቁጥጥር ነፃ ወጥተናል። ስለሆነም፥ እነዚህ ክፉ ፍላጎቶች ሊቆጣጠሩን አይገባም። ሆዳምነት (የምግብ ፍቅር)፥ ወሲብ፥ ዕፅ፥ መጠጥ፥ ገንዘብ፥ ትምህርትን በመሳሰሉት ቁጥጥር ሥር መዋሉ ትክክል አይደለም። ከእነዚህ ነገሮች አንዱም እንኳ ቢቆጣጠረን ኃጢአት ነው። አንድ ቀን ሰውነታችን ፈርሶ ሌላ አካል ይሰጠናል። ስለሆነም፥ ወደ ኃጢአት የሚመሩ ወይም እግዚአብሔርን የማያስከብሩ ነገሮችን በማድረግ ለጊዜው ፍላጎቶቻችንን ከምናሟላ ይልቅ ዘላለማዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ነገሮች ልንፈጽም ይገባል።

3. ክርስቲያኖች የክርስቶስ አካል የራሱ ክፍሎች ናቸው። ስለሆነም፥ አንድን ተግባር በምንፈጽምበት ጊዜ ክርስቶስንም የዚያ ድርጊት ተሳታፊ እናደርገዋለን። ለእግዚአብሔር ምስጋናን ስንዘምር፥ ይህ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ምስጋናን የሚዘምርበት ዓይነት ነው። ስንመሰክር ክርስቶስ እንደሚመሰክር ነው፥ ለድሀ ስንመጸውት ይህ ክርስቶስ ለድሃ እንደሚመጸውት ያህል ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ ወሲባዊ ኃጢአት መፈጸማችን ክርስቶስን ወደዚሁ ተግባር እንደ መምራት ነው። ጳውሎስ እንደሚለው፥ ከክርስቶስ ጋር ስለተባበርን የምናደርገው ክፉም ሆነ ደግ

ተግባር ክርስቶስን ያሳትፈዋል (በሐዋርያት ሥራ 9፡4 ክርስቶስ ክርስቲያኖችን ማሳደድ እርሱን እንደ ማሳደድ መሆኑን በገለጸበት መልኩ ይህንኑ እውነት እንመለከታለን።)

4. ጳውሎስ ወሲባዊ ኃጢአት ለፈጻሚው እንደ ውሸት ካሉት ሌሎች ኃጢአቶች የከፋ መዘዝ እንደሚያስከትል አመልክቷል። ጳውሎስ ይህን ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ እርግጠኞች አይደለንም። ምናልባትም ወሲባዊ ኃጢአት ከሌሎች ኃጢአቶች በበለጠ ባሕሪያችንን፥ ቤተሰባችንና ጤንነታችንን እንደሚጎዳ መግለጹ ይሆናል። ዛሬ ሰዎችን የሚያሠቃዩ እንደ ኤድስ ያሉ በሽታዎች የወሲባዊ ኃጢአት ውጤቶች ናቸው።

5. ወሲባዊ ኃጢአት የመንፈስ ቅዱስን ቤተ መቅደስ ያረክሰዋል። በቆሮንቶስ አረማዊ አምልኮ ወሲባዊ ኃጢአት የጣዖት አምልኮ አካል ነበር። ለክርስቲያኖች ግን እውነቱ የተገላቢጦሽ ነበር። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን በመገናኛው ድንኳንና በቤተ መቅደስ ውስጥ ይኖር እንደነበረ ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ እንደሚኖር እያንዳንዱ አማኝ መገንዘብ አለበት። ክርስቲያኖች ሁሉ ይህንን ሊያውቁ ይገባል። የአማኞች ኅብረት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ስለመሆኑ ከሚናገረው 1ኛ ቆሮ. 3፡16 በተለየ መንገድ፥ ይህ ምንባብ እያንዳንዱ አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ቤተመቅደስ በመሆኑ ላይ ያተኩራል። ለዚህም ምክንያቱ ኃጢአት ቢሠሩም እንኳ መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ የሚኖር መሆኑ ነው። እግዚአብሔር ቅዱስ አምላክ ስለሆነ፥ ማደሪያዎቹ የሆኑት ክርስቲያኖች እንዲቀደሱለት ይፈልጋል። ይህም በብሉይ ኪዳን ዘመን ሕዝቡ በተቀደሰ ሕይወት እንዲያመልከው ከተጠየቀበት ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ነው።

6. ወሲባዊ ኃጢአት የማን መሆናችንን እንድንዘነጋ ያደርጋል። ጳውሎስ እንደሚለው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን በራሳችን ሕይወት ላይ መብት አይኖረንም። ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞት ገዝቶናል። ስለሆነም ክርስቶስ በሕይወታችን ላይ መብት ስላለው እርሱ የሚፈልገውን ማድረግ አለብን። ሰውነታችንንና ሰውነታችንን የምንጠቀምበትን ሁኔታ ሊቆጣጠር የሚገባው በባለቤትነት የሚያስተዳድረን ክርስቶስ ነው። የክርስቶስ ትልቁ ፍላጎት እግዚአብሔርን ማስከበር ስለሆነና ሰውነታችንን ለእግዚአብሔር ክብር ለመጠቀም ስለሚፈልግ፥ ተግባራችን ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብርን ማምጣት አለበት። ወሲባዊ ኃጢአት እግዚአብሔርን አያስከብርም። ስለሆነም፥ የክርስቶስ የሆነውን ሰውነታችንን እርሱ ለማይፈልገው ተግባር መጠቀሙ ትክክል አይሆንም።

30ኛ ጥያቄ፡- ሁለት ወጣቶች ወደ አንተ መጥተው፥ «እርስ በርሳችን እንፋቀራለን» በሚቀጥሉት ሦስት ወራት ውስጥ ጋብቻችንን ስለምንፈጽም አብረን መተኛት ብንጀምር ምን ይመስልሃል? ይሄ ማንንም አይጎዳም» ቢሉህ፥ ጳውሎስ ስለ ወሲባዊ ኃጢአት ካስተማረው በመነሣት ምን ብለህ ትመክራቸዋለህ?

**አምስተኛ ቀን፡** ለሳምንታዊ ስብሰባ በመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ

## ሳምንታዊ ስብሰባ

*የመወያያ ጥያቄዎች፡-*

ሀ. 1) ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ጉባዔ ሲጽፍ እግዚአብሔር ለሐዋርያነት እንደመረጠው አጽንኦት ሰጥቶ ያብራራው ለምንድን ነው? 2) አንዳንድ ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ቃል ከመገዛት ይልቅ ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር በማይጣጣሙ አስደናቂ ነገሮች የተወሰዱት እንዴት ነው? ይህ ለቤተ ክርስቲያን አደገኛ የሚሆነው እንዴት ነው? 3) ከእግዚአብሔር ቃል ግልጽ አስተምህሮ ውጭ የሆኑና ሰዎችን ወደ ጥፋት እየመሩ ስላሉ፥ የአንዳንድ ክርስቲያኖች ድርጊቶች ግለጽ? 4) ብዙ ክርስቲያኖች ስለ አንድ ነገር እውነት መሆን ወይም አለመሆን የማይጨነቁት ለምን ይመስልሃል?

ለ. 1) ጳውሎስ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን የገለጸው እንዴት ነው? 2) ከዚህ ገለጻ ስለ ራሳችንና ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ምን እንማራለን? 3) ብዙ ኢትዮጵያውያን ጥሩ የማምለኪያ ሕንፃ መገንባት ወይም መሥራት አለብን ብለው የሚያስቡት ለምንድን ነው? 4) ይህንን አመለካከት በአዲስ ኪዳን ዘመን ከነበረው ሁኔታ ጋር አነጻጽር። ትልቅ የማምለኪያ ሕንጻ መፈለጋችን ጥሩ ይመስልሃል ወይስ መጥፎ? መልስህን አብራራ። 5) ብዙውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ሳትሆን የእኛ ናት ብለን የምናስበው ለምንድን ነው? 6) የየትኛውም ቤተ እምነት ቤተ ክርስቲያን በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብትሆንም እንኳን የእግዚአብሔር እንደሆነች ብናስብ አመራራችን እንዴት ይለወጣል? 7) እግዚአብሔር ክርስቲያኖችን ከጠራባቸውና ካዳናቸው ምክንያቶች አንዱ እርሱን እንዲመስሉና እንዲቀደሱ ነበር። አማኝ ከሆንህ በኋላ በሕይወትህ ውስጥ የተለወጡና ክርስቶስን በመምሰል እንድትቀደስ ያደረጉህ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ብዙ ክርስቲያኖች ለመቀደስ የሚቸገሩባቸው የሕይወት ክፍሎች ምን ምንድን ናቸው?

ሐ) 1) ጳውሎስ 1ኛ ቆሮንቶስን የጻፈበት ዓላማ ምን ነበር? 2) ዛሬ ምን ያህል ክርስቲያኖች በልሳን እንደ መናገር ያሉት መንፈሳዊ ስጦታዎች የመንፈሳዊ ብስለት ምልክቶች ናቸው ብለው እንደሚያስቡና አንድነት፥ ፍቅር፥ ንጽሕና ለመሳሰሉት መንፈሳዊ ባሕርያት ትኩረት እንደማይሰጡ አስረዳ። 3) በተወሰኑ መንፈሳዊ ስጦታዎች ላይ ማተኮር ቤተ ክርስቲያን በአንድነት፥ ፍቅር፥ ንጽሕና፥ መንፈሳዊነትና ቅድስና እንድታድግ ያደረገ ይመስልሃል? ለምን? 4) በ1ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ ከቀረቡት ስድስት ችግሮች ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት የትኞቹ ናቸው? 5) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የጳውሎስን መልስ መረዳት ለምን የሚጠቅማቸው ይመስልሃል።

መ. 1) ጳውሎስ የጠቀሰውና በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረው የመጀመሪያው ችግር ምን ነበር? 2) በኢትዮጵያ አንዳንድ ክርስቲያኖች ክርስቶስን ከመከተል ይልቅ በሰብአዊ መሪ ላይ ትኩረት ሲያደርጉ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ። 3) ዛሬ ክርስቲያኖች በዚህ ዓለማዊ ጥበብን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመጠቀሙ ወጥመድ ውስጥ የሚወድቁት እንዴት ነው? 4) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሰው የእግዚአብሔር ጥበብ ይልቅ ዓለማዊ ጥበብን የተግባራችንና የአስተሳሰባችን መሠረት በምናደርግበት ጊዜ

ችግሮች ስለሚከሰቱበት ሁኔታ ምን እንማራለን? 5) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ስለሚገኙ ችግሮች የጻፍኸውን ዝርዝር ተመልሰህ ክልስ (17ኛ ጥያቄ)። እያንዳንዱ ችግር በመለኮታዊ ሳይሆን ዓለማዊ ጥበብ ላይ እንዴት እንደተመሠረተ አሳይ። 6) እግዚአብሔር ስለሰጣችሁ ስጦታዎችና ኃላፊነቶች አንዳችሁ ለሌላችሁ ተናገሩ። እነዚህ ስጦታዎችና ኃላፊነቶች እንዴት «እንጨት፥ ሣርና ገለባ» ወይም «ወርቅ፥ ብርና የከበሩ ማዕድናት» ሊሆኑ ይችላሉ? በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? 7) የተመሰገነ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ብትሆን፥ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 2-4 ስለ መሪነት የገለጻቸውን እውነቶች በመጠቀም እንዴት ትመክረዋለህ?

ሠ. 1) ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደሚገኝ የጠቀሰው ሁለተኛው ችግር ምንድን ነው? 2) የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ጨምሮ ክርስቲያኖች ብዙ የወሲብ ኃጢአት የሚፈጽሙት ለምን ይመስልሃል? ይህ ስለ መንፈሳዊ ጤንነታችንና ስለ አማኞች የደቀ መዝሙርነት ደረጃ ምን ያሳያል? 3) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ጳውሎስ የገለጸው ዓይነት ይፋዊ ፍርድ ሲሰጥ አይተህ ታውቃለህ? ይህ ከሆነ፥ የተከሰተውን ሁኔታ አብራራ። 4) ቤተ ክርስቲያን ስለ ዓመፅ ኃጢአት ብዙም ይፋዊ ፍርድ የማትሰጠው ለምን ይመስልሃል? ይህ ጉዳይ፥ ኃጢአት በቤተ ክርስቲያን እንዲስፋፋ ያደረገው እንዴት ነው? 5) የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ሆነህ ስታገለግል ሁለት የኳየር መዘምራን ዝሙት እንደሚፈጽሙ ሰማህ እንበል። ማቴዎስ 18፡15-17ንና ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የሰጠውን ትእዛዝ በመከተል፥ ለዚህ ኃጢአት መፍትሔ የምትሰጠው እንዴት ነው? 6) «ይህን ካደረግን፥ እነርሱና ቤተሰቦቻቸው ትተውን ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ። ሰዎቹ ጠቃሚዎቻችን ስለሆኑ በዚህ ዓይነት ልናሳፍራቸው አንችልም።» የሚል ምክንያት ለሚያቀርብ ሌላ ሽማግሌ ምን ምላሽ ትሰጠዋለህ?

ረ. 1) ጳውሎስ ለክርስቲያኖች በፍርድ ቤት መካሰስ ትክክል አይደለም ያለው ለምንድን ነው? 2) ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ባልፈቀደላቸው መንገድ በሌሎች ክርስቲያኖች ላይ የሚፈርዱባቸውን ሁኔታዎች ለማሳየት አምስት ምሳሌዎችን ስጥ። 3) እግዚአብሔር ክርስቲያኖች በሌሎች ክርስቲያኖች ላይ እንዲፈርዱ የሚጠብቅባቸውን ሁኔታዎች ለማሳየት አምስት ምሳሌዎችን ስጥ። 4) ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊፈቱ የሚችሏቸውን ችግሮች ወደ ዓለማውያን ስለሚወስዱባቸው ሁኔታዎች የሚያስረዱ ጥቂት ምሳሌዎችን ስጥ። ከእነዚህ ልምምዶች የመነጩት አሉታዊ ነገሮች ምንድን ናቸው? 5) በክርስቲያኖች መካከል ከሚከሰቱ ክፍፍሎች አንድ ምሳሌ ውሰድና ጳውሎስ ባስተማረው መሠረት ክርስቲያኖች ልዩነቶቻቸውን እንዴት መፍታት እንዳለባቸው ግለጽ።